አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# የአርጐባ ማኅበረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና

በ

አዲሱ ጴጥሮስ

ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የአርጐባ ማኅበረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

አህመድ ሀሰን (ዶ/ር)

በ

አዲሱ ጴጥሮስ

ሰኔ 2005 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# የአርጐባ ማኅበረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና

በ

አዲሱ ጴጥሮስ

2005 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኞች | ፊርማ |

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ILS LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ........................................................................................................ I
የአማራ ክልል ካርታ እና ጥናቱ ትኩረት ያደረገበት አካባቢ ካርታዎች ................................ II
አጠቃሎ ........................................................................................................ III
1.መግቢያ ........................................................................................................ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................................ 2
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................................ 4
1.3 የጥናቱ ዓላማዎች .................................................................................... 5
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታዎች ................................................................................ 5
1.5 የጥናቱ ወሠን ........................................................................................ 6
1.6 የአጠናን ዘዴ ........................................................................................ 7
1.7 የመረጃ አተናተን ዘዴ ................................................................................ 8
1.8 የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ ............................................................ 8
1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ............................................................ 9
2.የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ ምልከታ ...................................................................... 11
2.1 የአርጐባ ማኅበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ .......................................................... 11
2.2. የአርጐባ ማኅበረሰብ መልክዓ ምድራዊ ስርጭት .................................................. 12
2.3. የአርጐባ ቋንቋ .................................................................................... 13
2.4. የአርጐባ ማኅበረሰብ የኢኮኖሚ ሁኔታ .......................................................... 14
2.5. የአርጐባ ማኅበረሰብ የጋብቻ ስርዓት ............................................................ 15
2.6.የአርጐባ ማኅበረሰብ የሃዘን ስርዓት .............................................................. 16
3.ክለሳ ድርሳን ...................................................................................... 18
3.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት .............................................................................. 18
3.1.1. ቃላዊ ዝርው ተረክ /Oral prose narrative/ ................................................ 18
3.1.2. ማንነት/Identity/ ............................................................................ 19
3.1.3. ማንነትና ተረክ/Identity and narrative/ .................................................. 20
3.1.4. ተግባራዊ ሥነ-ዘዴ /Functional Approach/ ................................................ 21
3.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................................................ 24
3.2.1.በአርጐባ ማኅበረሰብ ላይ የተሰሩ ጥናቶች ቅኝት .................................................. 24

3.2.2.በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ የተሰሩ ጥናቶች ቅኝት ........ 26
4.ከአርጐባ ማኅበረሰብ ማንነት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ትንተና ........ 34
4.1. ከአርጐባ ስያሜ፣ አመጣጥ፣ ከትውልድ ሐረግ እና ከሕዝቡ አሰፋፈር ጋር የሚገናኙ ተረኮች ........ 34
4.1.1.ከአርጐባ ስያሜ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ........ 34
4.1.2. ከአርጐባ አመጣጥና የትውልድ ሐረግ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ........ 38
4.1.3. ከአርጐባ ሕዝብ አሠፋፈር ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ........ 43
4.2. ከጋብቻ፣ ከሽምግልና እና ከእደ ጥበብ ሙያ ጋር የተገናኙ ተረኮች ........ 50
4.2.1. ከጋብቻ አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ........ 50
4.2.2. ከሽምግልና ስርዓት ጋር ተያይዞ የሚነገሩ ተረኮች ........ 51
4.2.3. ከእደጥበብ ሙያ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ........ 54
4.3.ከጀግንነት ጋር የሚገናኙ ተረኮች ........ 58
4.3.1. ከሼህ ጠለሃ ጃእፈር ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ........ 58
5.ማጠቃለያ ........ 67
6.ዋቢ ጽሁፎች ........ 70
7.አባሪ 1፡- የፎቶ ግራፍ ዝርዝር ........ 76
8.አባሪ 2፡- የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ........ 78
9.አባሪ 3፡- ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች ........ 80
10.አባሪ4፡-ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን ........ 84
11.አባሪ 5፡-የተረኮች ስብስብ ........ 89
11.1. ከአርጐባ ስያሚ ጋር የተያያዙ ........ 89
11.2. ከአርጐቦች አመጣጥ ጋር የተያያዘ ........ 91
11.3. ከአርጐብኛ ቋንቋ አመጣጥ ጋር የተያያዙ ........ 92
11.4. ከአርጐቦች አሠፋፈር ጋር የተያያዙ ........ 93
11.5. አርጐቦች የባሪያ ንግድ ከማካሄዳቸው ጋር የተያያዘ ........ 94
11.6. አርጐቦች እስልምናን ስለመመስረታቸውና ስለማስፋፋታቸው ........ 95
11.7. አርጐቦች ዘመናዊ ትምህርት ካለመማራቸው ጋር የተያያዘ ........ 95
11.8. አርጐቦች ከተበደሩት እህል ላይ ቀንሰው ስለመስጠታቸው ........ 95
11.9. ከዚያራ በዓል አከባበርን ጋር የተያያዘ ........ 96
11.10. አርጐቦች ኢትዮጵያን ከ700 ዓመት በላይ ስለማስተዳደራቸው ........ 97
11.11 አርጐቦች በተለያዩ ስያሜ ከመጠራታቸው ጋር የተያያዙ ........ 98

11.12. አህመድ ግራኝ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጅ ስለመሆናቸው .......... 100
11:13. ከሼህ ጦለሃ ጃእፈር ጋር የተያያዙ .......... 102
11.14. የጦለሃ አያት የአፄ ምኒልክን የእህት ልጅን ስለማግባታቸው .......... 106
11.15. የራስ መኰንን እናት የአርጐባ ተወላጅ ስለመሆናቸው .......... 107
11.16. ወላስማ አበጋዝ አፄ ምኒልክን ከእስር እንዲያመልጡ ስለማድረጋቸው .......... 107
11.17. አፄ ምኒልክ ወላስማ አበጋዝን ስለማስገደላቸው .......... 108
11.18 አርጐቦች ተራራ ላይ ከመስፈራቸው ጋር የተያያዙ .......... 109
11.19. አርጐቦች የብረታ ብረትና የሸክላ ሥራ ስለአለመስራታቸው .......... 110
11.20. የእደ ጥበብ ሙያተኞች የአርጐባ ማኅበረሰብ አባል ስለመሆናቸው .......... 111
11.21. አርጐቦች ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር ስለአለመጋባታቸው .......... 111
11.22. ከአርጐቦች የምግብ አዘገጃጀት ጋር የተያያዘ .......... 112
11.23. ከአርጐቦች የግርዘት ስርዓት ጋር የተያያዘ .......... 113
11.24. ከመውሊድ በዓል አከባበር ጋር የተያያዘ .......... 113
11.25. አርጐቦች ቡዳ ከመባላቸው ጋር የተያያዘ .......... 114
11.26. አርጐቦች ሰይድ አሊይን የገደሉ ከመባላቸው ጋር የተያያዘ .......... 115
11.27. አርጐቦች እስላም አይደሉም ከመባላቸው ጋር የተያያዘ .......... 115
11.28. ከረከቦት ስርዓትን ጋር የተያያዙ .......... 116
11.29. ከወቃሊሞ አጀማመርን ጋር የተያያዙ .......... 118

## ምስጋና

ይህ ጥናት እዚህ ደረጃ እንዲደርስ በቅንነት ለረዱኝ ውድ አማካሪዬ ዶ/ር አህመድ ሀሰን ላደረጉልኝ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በአባሪ ሁለት ላይ የሰፈራችሁ መረጃ አቀባዮቼ በሙሉ ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች ባትሰጡኝ ኖሮ ይህ የጥናት ስራ እዚህ ደረጃ ላይ አይደርስም ነበር፤ ስለዚህ ሁላችሁንም አመሰግናለሁ፡፡

አቶ አብርሃም አለሙ እና ዶ/ር ሀሰን ሰይድ ለዚህ ጥናት ተገቢነት ያላቸውን መጻህፍት እና የተለያዩ ማቴሪያሎችን በማዋስ ስለተባበራችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

አቶ ጌታቸው ተስፋ እና አቶ ሞገስ ጀንበር እንደ ሁለተኛ አማካሪ በመሆን ስላደረጋችሁልን ድጋፍ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ይህን ጥናት በማዘጋጅበት ጊዜ ላፕቶፕ (Laptop) በማዋስ ለተባበረከኝ ወንድሜ አለም አንተ ጴጥሮስ እና በገንዘብ ለረዳኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በከሚሴ፣ በመዲና፣ በሸዋ ሮቢትና በአንኮበር ከተማ ውስጥ የምትገኙ የተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤት ኃላፊዎችና ሰራተኞች ላደረጋችሁልኝ መልካም አቀባበል እና ትብብር ምስጋና ይገባችኋል፡፡

## የአማራ ክልል እና ጥናቱ ትኩረት ያደረገበት አካባቢ ካርታዎች






ምንጭ ዶ/ር ሀሰን ሰይድ ስለ አርጎባ ታሪክ በሶፍት ኮፒ ከሰጡኝ የተወሰደ

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በአማራ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋና በኦሮሚያ ልዩ ዞን ሰፍረው የሚገኙ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የሚናገሯቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማንነታቸውን ለመገንባት ያላቸውን ፋይዳ ለማሳየት የተካሄደ ነው፡፡ በጥናቱ ከቤተመጻህፍት የሚገኙ መረጃዎችን ከመሰብሰብ ጀምሮ ጥናቱ ስለሚካሄድበት አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ፣ በማኅበረሰቡ ስለሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በቃለመጠይቅና በምልከታ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎች በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶ ካሜራ እና በእጅ ማስታወሻ ተይዘዋል፡፡ እነዚህን መረጃዎችም በገላጭ (Descriptive) የምርምር ዘዴና በተግባራዊ ሥነ- ዘዴ (Functional Approach) ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ከጥናቱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው አንድ የመጀመሪያ ዲግሪ እና አስራ ሦስት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎችም ተቃኝተዋል፡፡

በጥናቱ ትንታኔ ውጤት መሠረት በአርጐባ ማኅበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የማኅበረሰቡን ማንነት ምንጩ የአረብ ምድርና እስልምና መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ አርጐቦች የነብዩ መሐመድ ተከታይ ስደተኛ አድርገው በመቁጠር በእንግድነት በገቡባት የሐበሻ አገር እስልምናን ለማስፋት የበቁበትን ጠንካራ እንቅስቃሴ ይተርካሉ፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ በርካታ ጀግኖች እንዳላቸው የሚገልጹት አርጐቦች ጀግኖቻቸው በክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ተገቢውን ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ከመረጃዎቹ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ ሁኔታ ማኅበረሰቡ በቃላዊ ዝርው ተረኮቹ አማካይነት የዘር ሐረጉን ከነብዩ መሐመድ በመምዘዝ ምርጥነቱን፣ በኢትዮጵያ እስልምናን በማስፋፋት እየተጠቀሙባቸው መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡

በማኅበረሰቡ የጀግንነት ታሪክ ጐልተው የሚጠቀሱት ሼህ ጠልሃ ጃእፈርና ሌሎች የኃይማኖት መሪዎች የማኅበረሰቡን የማንነት ተረክ በዚህ ትውልድም ዘንድ ቀጣይነት እንዲኖረው አድርገዋል፡፡ ማኅበረሰቡ ራሱን ከጥቃት ለመከላከል በተራራ አካባቢ መሰባሰብን መርጧል፡፡ የቤት አሠራሩም ይህንኑ ከአደጋ ተጋላጭነት ራስን የመጠበቅ ዝንባሌ የሚያሳይ ሲሆን፣ ማንነቱ የሚገለጽበት ሌላው ማኅበረ ባህላዊ ገጽታም ለብረታብረትና ሸክላ ዕደ ጥበባት ባለው ጥላቻ ሲገለጽ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህ ዕደ ጥበባት ዐይነ ወጊ? በሚሏቸው የተገለሉ ቡድኖች ማሠራትን ይመርጣሉ፡፡ የጋብቻ ትስስሩ በቅርብ

ዘመዳሞች መካከል የሚፈጸምበት ሥርዓትና ሌሎች ባህላዊ እንቅስቃሴዎቹ ከእስልምና ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን የሚገልጹ ሲሆኑ፣ በአጠቃላይ ተረኮቹ የማኅበረሰቡን ቀዳሚ ማንነት በዚህ ዘመን ላይም የማስረጽ ኃይላቸው ከፍ ያለ ነው ማለት ይቻላል፡፡

# ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በአርጐባ ማኅበረሰብ[1] ዝርው የቃል ተረክ ትንተና ላይ ነው፡፡ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በአፋርና በሐረሪ ብሔራዊ ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን፣ ይህ ጥናት የሚያተኩረው በአማራ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋና በኦሮሞ ልዩ ዞን ሰፍረው በሚገኙ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ላይ ነው፡፡

ለዚህ ጥናት ከተመረጠው የአርጐባ ማኅበረሰብ ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍል ትምህርት በቁሳዊ ባህልና በቋንቋ ላይ ያጠነጠኑ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ የማኅበረሰቡን ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶችን በመመርመር የሚኖራቸውን ማህበራዊ ፋይዳ በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶችን ግን አላገኘሁም። ስለዚህ ይህ ጥናት በተረኮች ዙሪያ ትኩረት በማድረግ የአርጐባ ማኅበረሰብ የሚናገሯቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማንነታቸውን ለመገንባት ያላቸውን ፋይዳ ለመተንተን ይሞክራል፡፡

የማኅበረሰቡ ማንነት ጐልቶ ከሚንጸባረቅባቸው ጉዳዮች መካከል የዘር ሐረጋቸውንና የአሰፋፈር ሁኔታቸውን በሚመለከት የሚቀርቡ ተረኮች ትኩረት ተደርጐባቸዋል፡፡ ይህም ማለት ከማኅበረሰቡ ስያሜ፣ የትውልድ ሐረግ ከሚመዘዝበት ታሪክ፣ እንዲሁም ከመኖሪያ አካባቢያቸው ጋር የተያያዙ ተረኮች ያላቸው ፋይዳ ተፈትሿል፡፡ በተጨማሪም የማኅበረሰቡ ማኅበረ ባህላዊ እሴቶች፣ በተለይም የጋብቻ አፈፃፀም፣ የሽምግልና ሥርዓትና የዕደ ጥበብ ሙያ ልምዶቻቸው ለማንነት ግንባታቸው የሚኖራቸው ጠቀሜታ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች የተደራጀ ነው፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱን አጠቃላይ አቅጣጫ የሚያስተዋውቁ ዘጠኝ ንዑሳን ርዕሶች ተካትተዋል፡፡

---

[1]አርጐቦች እራሳቸውን የአርጐባ "ብሔረሰብ" በማለት የሚጠሩ ሲሆን፣ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ብሔረሰብ ለሚለው ቃል "ከደም አጥንት ይልቅ በክልል፣ በቋንቋና በባህል አንድነት ላይ የተመሰረተ የተለያዩ ነገዶች የተዋሀዱበት ማኅበረሰብ" (1993፣ 243) በማለት ይተረጉመዋል። ማኅበረሰብን ደግሞ "(ማኅበራዊ ትስስር ያለው) በተወሰነ አካባቢ ወይም ቦታ የሚኖር ህዝብ" (1993፣ 70) ይለዋል። በዚህ ትርጉም መሠረት ማኅበረሰብ የሚለው ቃል ለጥናቱ ተስማሚ በመሆኑ አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል።

በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ጥናቱ የተካሄደበት ማኅበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ፣ መልክዓ ምድራዊ ስርጭት፣ ቋንቋ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ተዳስሰዋል፡፡

በምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ክለሳ ድርሳን ቅኝት ተደርጎበታል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሁለት ንዑሳን ርዕሶች ተካተዋል፡፡ እነዚህም ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝትና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ናቸው፡፡ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት በሚለው ስር ተረክንና ማንነትን በሚመለከት ማጣቀሻ መጻህፍትን መሰረት በማድረግ ገለፃ የተደረገበት ነው፡፡ በመቀጠልም ይህንን ጥናት ለመተንተን የሚመሰረትበትን ሥነ-ዘዴ /approach/ ምን እንደሚመስል በማሳየት ይጠናቀቃል፡፡ በዚሁ ምዕራፍ ሁለተኛ ክፍል ላይ ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡

አራተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከአርጎባ ማኅበረሰብ ማንነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተተንትነው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ በመጨረሻው ምዕራፍም የጥናቱ ማጠቃለያ ሀሳብ ቀርቦበታል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ዋቢ መጻህፍትና የተለያዩ አባሪዎች ተካትተዋል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ፎክሎር ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መጠናት የተጀመረው በ19ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ነው። የጀርመን ፊሎሎጅስት ጃኮብ ግሪም ከወንድማቸው ዊሊልም ጋር በመሆን እ.አ.አ. ከ1812-1814 ስነቃሎችን ሰብስበው "Kindex und Haus Marchen" በሚል ርዕስ አሳትመዋል። ይህ ጥናት "Girmm's Fairy tales" በሚል ርዕስ ተተርጉሞ ለአለም ማስተዋወቅ ተችሏል። ይህ የመጀመሪያ ሥራ ሲሆን፣ ጃኮብ ግሪም ስነቃል የመሰብሰቡን ሥራ ቀጥለውበት እ.አ.አ.በ1835 "Deutche Mythologic" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ጊዜ አሳትመዋል። የዚህ ሥራቸው አራተኛ እትም "Teutonic Mythology" በሚል ርዕስ ወደ እንግሊዘኛ ተመልሷል። የፎክሎር ጥናት በዚህ ወቅት ይጀመር እንጂ፣ ፎክሎር (Folklore) የሚለውን ስያሜ አላገኘም ነበር። ፎክሎር (Folklore) የተሰኘውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙትና ለአለም ያስተዋወቁት እንግሊዛዊው የጥንታዊ ቅርሳቅርስ ተመራማሪ ዊልያም ጆን ቶምስ እ.ኤ.አ.በ1846 እንደሆነ (አብርሃም፣ 1995፣ 2፣ ወልደስላሴ፣ 1972፣ 6) ያስረዳሉ።

የፎክሎር ጥናት በአፍሪካ የተጀመረው በ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ ነው፡፡ ፈቃደ (1991፣ 27) Finneganን ጠቅሰው እንዳሰፈሩት ጥናቱን የጀመሩት አውሮፓዊያን

ናቸው፡፡ አጀማመራቸውም ከቅኝ ግዛትና ከሚሲዮናዊያን ሐይማኖታዊ ተልዕኮ ጋር የተቆራኘ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ስነቃልን ሰብስቦ የማሳተም ሙከራዎች እንደነበሩም ይገልጻሉ። እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ አውሮፓውያን አፍሪካ ምንም አይነት የሥነ-ጽሁፍ ቅርስ እንደሌላት ያምኑ ነበር፡፡ ይህ እምነታቸው ከ1850ዎቹ ጀምሮ የአፍሪካን ቋንቋዎች ጥናት እንደ አንድ የምርምር መስክ ማጥናት በመጀመራቸው እየተለወጠ ሂዷል፡፡ የአውሮፓ ምሁራን ለአፍሪካዊያን ስነቃል የነበራቸው አመለካከት በሂደት እየተለወጠ በመሄዱ ለአፍሪካ ባህልና ሥነቃላት ዋጋ መስጠት ጀመሩ፡፡ በዚህም የህዝቡን ልዩ ልዩ የህይወት ዘርፎች ለማወቅ በሚደረጉ ጥናቶች ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን እንደ አንድ የምርምር ርዕሰ ጉዳይ መውሰድ ተገቢ መሆኑን ተረዱት (አብርሃም፣ 1995፣ 3)፡፡

በሀገራችን የስነቃል ሥራ ተሰባስበውና በመጽሐፍ መልክ ታትመው የምናገኘው በ1894 እ.ኤ.አ. የታተመው የኦነስሞ ነሲብ "የኦሮሞ ንባብ ማስተማሪያ" /ጀልቀበ በርሲሳ/ እንደሆነ ይገመታል (አብርሃም፣ 1995፣ 14)፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በመጽሐፍ መልክ ታትመው የምናገኛቸው የስነቃል ሥራዎች በ1918 ዓ.ም. የታተመው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ መጽሐፈ ቅኔ፣ በ1942 የወጡት የሐጂ ዩሱፍ አብድራህማን ያማርኛ ተረትና ምሳሌ እና የባላምባራስ ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል ዝክረ ነገር ናቸው። በ1940ዎቹ ዓመታት ታትመው የወጡት ሌሎች መጻህፍት የባላምባራስ ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል ያባቶች ቅርስ (1943) እና የአማርኛ ቅኔ፣ የአበበ አይቼህ ቢልጮ-ጉራማዊ የሆኑ ተረቶችና ምሳሌዎች (1948) እና ጉራማይሌ- ግሩማዊ የሆኑ ተረቶችና ምሳሌዎች (1948) ይገኙባቸዋል (ፈቃደ 1996፣ 3)።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ተማሪዎች በልዩ ልዩ ማኅበረሰቦች ስነቃላዊ ቅርጾች ላይ በመሥራት ለፎክሎር ጥናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ። ከ1958 እስከ 1998 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ሠላሳ ሁለት ዓመታት ውስጥ ከ243 የማያንሱ ዲግጾች በስነቃል ነክ ርዕሶች ዙሪያ ተሰርተዋል (ፈቃደ፣ 1991፣ 44)። እነዚህ ጥናቶች በተሰሩባቸው ቋንቋዎች መሠረት ሲከፋፈሉ 109 አማርኛ፣ 39 ኦሮምኛ፣ 16 በተለያዩ የጉራጌ ዘዬዎች (ቸሃ፣ ሰባት ቤት፣ ጌቶ፣ ክስታኔ፣ መስቃንና ሰዶ)፣ 15 ትግርኛ፣ 10 ሲዳምኛ፣ 6 ሐድይኛ፣ 5 ወላይተኛ፣ 4 አደርኛ፣ 3 ከምባትኛ፣ ሁለት ሁለት ከፍኛ፣ ጋሞኛ፣ ጉጂኛ፣ ሶማልኛ እና ስልጥኛ፣ አንድ አንድ አገውኛ፣ አሪኛ፣ ቡርጂኛ፣ ጌዲዎኛ፣ አዙርነት በርበሬኛ፣ ጐፋኛ፣ አላብኛ እና የምኛ ቋንቋዎች ላይ በስነ ቃላዊ

ጉዳዮች ዙሪያ ሲያጠነጥኑ(ፈ.ቃደ፣ 1991፣ 44-45) የአርጐብኛ ስነ ቃሎች ትኩረት ያገኙበት ሁኔታ አልነበረም።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለመጀመሪያ ጊዜ በአርጐባ ማኅበረሰብ ላይ የተሠራ ጥናት የምናገኘው ነጋሽ መሀመድ በ1981ዓ.ም. "አርጐብኛና የአርጐቦች ህይወት በሁለት (አልዩ አምባና አዋሽ) ከተሞች" ውስጥ በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበው እና በ2000 ዓ.ም. "የአርጐባ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች" በሚል ዐቢዩ አስማማው ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ያጠናው ጥናት ነው። እነዚህን ጥናቶች ስንመለከት ትኩረታቸው በአርጐባ ማኅበረሰብ ቋንቋና በቁሳዊ ባህል ላይ ያጠነጠኑ ናቸው። በአርጐባ ስነቃሎች ላይ የተደረጉ ሌሎች አካዳሚያዊ ጥናቶችን አላገኘሁም። ስለዚህ ይህ ጥናት በአርጐባ ማኅበረሰብ ከስነቃል ክፍሎቹ ውስጥ በተለይ በተረኮች ዙሪያ ትኩረት ስለሚያደርግ ያለውን ክፍተት በተወሰነ ደረጃ ይሞላል የሚል እምነት አለኝ።

የዚህ ጥናት ትኩረት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ በደቡብ ወሎ ዞን፣ በአርጐባ ልዩ ወረዳ (መዲና) ፣ በሰሜን ሸዋ ዞን አንኮበር፣ አልዩ አምባና ሸዋ ሮቢት ከተማ አካባቢ፣ በኦሮሞ ልዩ ዞን በደዌ ጨፋ ወረዳ በከሚሴና ሾንኬ በሚኖሩ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ላይ ያተኩራል፡፡ ጥናቱ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ማንነታቸውን በሚያሳዩ ተረኮች ላይ ምርመራ ያደርጋል፡፡ ተረኮች ለአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ያላቸውን ፋይዳ በአንፃራዊ መልኩ ይመረምራል፡፡ ከነዚህ አካባቢዎች የተሰበሰቡ ተረኮች የአቀራረብ ስልታቸው ይለያይ እንጂ፣ የማኅበረሰቡን ልማድ፣ ባህል፣ አመለካከትና እምነት በማስተላለፍ በኩል ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ለዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት የሆነኝ በፎክሎር ትምህርት ወቅት "የማንነት ተረኮች" ትኩረት እንዳላገኙ በተደጋጋሚ ሲጠቀስ መስማቴ ነው፡፡ ጥናቱን በየትኛው ማኅበረሰብና በምን ቦታ ላድርግ እያልኩ በማስብበት ወቅት በአጋጣሚ ለሥራ ጉዳይ ወደ ሸዋ ሮቢት ከተማ ሄድኩ፡፡ በሸዋ ሮቢት ቆይታዬ ስለ አርጐባ ማኅበረሰብ አመጣጥ የተለያዩ ተረኮችን ሰማሁ፡፡ አርጐቦች ከአረብ ፈልሰው እንደመጡ የሚናገሩ የመኖራቸውን ያህል፣ አርጐቦች ቀያይና የእስልምና እምነት ተከታዮች በመሆናቸው፣ ራሳቸውን ከአረብ ዝርያ ጋር ለማዛመድ ስለሚፈልጉ እንጂ ከኢትዮጵያ ምድር የፈለቁ

ናቸው የሚሉም አሉ፡፡ ይህ የተለያየ ሀሳብ በአርጐባ ማኅበረሰብ ላይ ትኩረቴን እንዳደርግ አነሳስቶኛል ማለት እችላለሁ፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማራ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋና በኦሮሞ ልዩ ዞን ሰፍረው የሚገኙ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የሚናገሯቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማንነታቸውን ለመገንባት ያላቸውን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡

ከዚህ ዓላማ የወጡ ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በአማራ ክልላዊ መንግሥት በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋና በኦሮሞ ልዩ ዞኖች ሰፍረው የሚገኙ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ማንነታቸውን እንዴት እንደሚገልጹ በተረኮቻቸው ውስጥ መመርመር፣
2. በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚነገሩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች የማኅበረሰቡ ስያሜ፣ አመጣጥና የትውልድ ሐረግ እንዴት እንደተገለፀ ማመላከት፣
3. ማንነታቸውን በሚያንፀባርቁበት ተረኮች የሚተላለፈው መልዕክት ምን እንደሆነ መተንተን የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህን ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች ይዞ የተነሳው ይህ ጥናት በጥናቱ መጨረሻ ላይ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ምን ተረኮች አሏቸው?
2. አርጐቦች በቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው አማካይነት ማንነታቸውን እንዴት ይገልጻሉ?
3. በማኅበረሰቡ የሚነገሩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ለማኅበረሰቡ ማህበራዊ ህይወት ያላቸው ፋይዳ ምን ይመስላል?
4. የማኅበረሰቡ አባላት በተረኮቻቸው አማካይነት ምን አይነት መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ? ለምንስ ያስተላልፋሉ?

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታዎች

1. የተለያዩ የማኅበረሰብ አካላት ማንነታቸውን (Identity) በተለያዩ ተረኮች አማካይነት ይመሰርታሉ፡፡ በመሆኑም ማንነታቸውን በሚገነቡባቸው ተረኮች ላይ ትኩረት በማድረግ ማጥናት በተወሰነ ደረጃ እየተለመደ የመጣ ቢሆንም ይህ

ርዕሰ ጉዳይ አሁንም ገና በስፋት ያልተጠና በመሆኑ ይህ ጥናት መደረጉ ለአንባቢያን ተጨማሪ ግንዛቤን ይፈጥራል፡፡

2. ይህ ጥናት ሰዎች ማንነታቸውን የሚመሰርቱባቸውን (Identity forms የሚያደርጉባቸውን) ተረኮች ለማጥናት እንደ አነሳሽ ምክንያት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡
3. ተረኮች ሰዎች ማንነታቸውን የሚገነቡባቸው መንገዶች በመሆናቸው፣ የሚፈጥሩትን ማኅበራዊ ተጽዕኖ ለማጥናት ለሚሞክር ተመራማሪ በተወሰነ ደረጃ ጠቀሜታ አለው፡፡
4. የማኅበረሰቡ አባላት ማንነታቸውን በተረኮቻቸው እንዴት እንደሚገነቡ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡
5. ከአርጎባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ጋር ተያያዥነት ባለው ጉዳይ ላይ ታሪክ ለመፃፍ ለሚነሳሳ ማንኛውም የታሪክ ተመራማሪ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

የአርጎባ ማኅበረሰብ አባላት በተለያየና በተበታተነ አካባቢ ይኖራሉ፡፡ ቀደም ያሉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የአርጎባን ማኅበረሰብ መልክዓ ምድራዊ አሠፋፈር “ሰሜንና ደቡብ” በማለት ይከፍሉታል፡፡ በዚህ አከፋፈል በሰሜን ክፍል የሚገኙት ከከሰም ወንዝ ዳርቻ ጀምሮ እስከ ኮምቦልቻ ድረስ ያሉትን የአርጎቦች መኖሪያ አካባቢዎችን ይይዛል፡፡ በደቡብ የሚገኙት ደግሞ አዋሽና ሐረር አካባቢ ያሉትን ያመላክታል (Weeks, 1984: 51)፡፡ በዚህ አከፋፈል መሰረት ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል በሚገኙ የአርጎባ ማኅበረሰብ አባላት ላይ ይሆናል፡፡ በዚህ ክፍል ከሚገኙት መካከልም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በደቡብ ወሎ አስተዳደር ዞን በአርጎባ ልዩ ወረዳ መዲና፣ በሰሜን ሸዋ አስተዳደር ዞን አንኮበር፣ አልዩ አምባና ሸዋ ሮቢት ከተማ አካባቢ፣ በኦሮሞ ዞን በደዌ ጨፋ ወረዳ በከሚሴ ከተማ እና በሾንኬ መንደር በሚኖሩ የአርጎባ ማኅበረሰብ አባላት ላይ ያተኩራል፡፡ ጥናቱ የአርጎባ ማኅበረሰብ ተወላጆችን ማንነት በሚያሳዩ ተረኮች ላይ ይመሠረታል፡፡ ከተረኩ ውጭ የሆኑ ሌሎች የአርጎባ ማኅበረሰብ ፎክሎሮች በዚህ ጥናት ውስጥ የሚዳሰሱ አይሆንም፡፡

## 1.6. የአጠናን ዘዴ

የዚህን ጥናት ዓላማ ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች መካከል ለዚህ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች ለመሰብሰብ ቃለመጠይቅ (Interview)፣ እና ምልከታ (Observation) ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ከካልዓይ ምንጮች መካከል ደግሞ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የታተሙና ያልታተሙ ጽሁፎች እና ጥናቶች ከቤተ መፃህፍት እንዲሁም ከኢንተርኔት ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል።

ለጥናቱ የሚያግዙ መጠይቆችን በማዘጋጅበት ወቅት የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎችን ለማንበብ ሞክሬያለሁ። ከአርጎባ የልማት ማህበር አመራር አባላትና በፎክሎር የጥናት መስክ እውቀት ካላቸው ምሁራን ጋር ተወያይቻለሁ። በዚህ መልኩ ካገኘሁት ሀሳብ በመነሳት መጠይቆችን አዘጋጅቻለሁ።

በመቀጠልም ጥናቱ በተመሰረተበት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በደቡብ ወሎ አስተዳደር ዞን በአርጎባ ልዩ ወረዳ መዲና፣ በሰሜን ሸዋ አስተዳደር ዞን አንከበር፣ አልዩ አምባና ሸዋ ሮቢት ከተማ አካባቢ፣ በኦሮሞ ዞን በደዌ ጨፋ ወረዳ በከሚሴ ከተማ እና በሾንኬ መንደር ከሚኖሩ የአርጎባ ማኅበረሰብ አባላት ጋር በመገናኘት ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በምልከታ (Observation) ሰብስቤያለሁ። ከዚህም ውስጥ ከግንቦት 6 እስከ 23 ቀን 2004 ዓ.ም እና ከየካቲት 13 እስከ 17 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ ለ24 ቀናት አርጎቦች በሚገኙባቸው የተለያዩ መንደሮች ቆይታ አድርጌአለሁ። በእነዚህ ቀናት አርጎቦች የሚኖሩባቸውን ቤቶች፣ መስጊዶች፣ ልዩ ልዩ ቦታዎችንና አኗኗራቸውን ተመልክቻለሁ። አስፈላጊ የመሰሉኝን መረጃዎች ፎቶ ግራፍ በማንሳትና በማስታወሻ ደብተር ላይ በመመዝገብ መረጃ ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ።

እንዲሁም የጥናቱን ማዕከላዊ ሀሳብ ለይቶ ለማውጣት የሚያስችሉና ከተለያዩ አቅጣጫ ምርምር ለማድረግ የሚረዱ መጠይቆችን በመጠቀም ቃለመጠይቅ (Interview) አድርጌአለሁ። በዚህ መሠረት አስራ ስምንት መረጃ አቀባዮችን በመጠቀም ሃምሳ ስድስት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ሰብስቤያለሁ፡፡ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቹ በአርጎባ ማኅበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው፣ ስለማኅበረሰቡ በቂ የሆነ የታሪክና የባህል ዕውቀት ያካበቱ ሰዎች እንዲመረጡ ጥንቃቄ አድርጌአለሁ፡፡ መረጃ አቀባዮቹን በመምረጡ ረገድ የአርጎባ ልማት ማህበር ከፍተኛ የሆነ ድጋፍ አድርጎልኛል። የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነት ለመመዘን ከአንድ የአርጎባ መንደር የተገኘውን

መረጃ ሌላ መንደር ለሚኖሩ መረጃ አቀባዮቹ በቴፕ በማሰማት ስለተረኩ ትክክለኛነት ለማጣራት ሞክሬአለሁ፡፡ የተገኙ ማስተካከያዎችን መሠረት በማድረግ እርማት አድርጌአለሁ፡፡

## 1.7. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በመስክ ቆይታ ወቅት ጥሬ መረጃውን ለማደራጀትና ለመተንተን ሙከራ ተደርጓል፡፡ ይህም መሆኑ በተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ የታዩትን ክፍተቶች እዚያው መስክ ላይ እያለሁ ለመሙላት አስችሎኛል፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከቃለ መጠይቅ፣ ከምልከታና ከታተሙ ጽሁፎች ከተሰበሰቡ በኋላ ትንታኔ ተሰጥቷል፡፡

ትንተናውን ለማካሄድ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የመስኩ ምሁራን የሰጧቸውን ሀሳቦች በመስክ ከተገኙ መረጃዎች ጋር በማዛመድ ለመተንተን ተችሏል፡፡ ይህን ጥናት ለመተንተን ጥቅም ላይ የዋለው ገላጭ (Descriptive) የምርምር ዘዴ ነው፡፡ እንዲሁም የአርጎባ ማኅበረሰብ ተረኮች ያላቸውን ፋይዳ ለመመርመር ተግባራዊ ሥነ-ዘዴ (Functional Approach) እገዛ ያደርግልኛል የሚል እምነት ስላደረብኝ ይህን ዘዴ እንደተጨማሪ መተንተኛ ለመጠቀም ጥረት አድርጌአለሁ፡፡

## 1.8. የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃ አቀባዮች የተመረጡት በአላማ የናሙና አመራረጥ ዘዴ (purposive sampling method) ነው፡፡ ስለአርጎባ ማኅበረሰብ ባህልና ታሪክ በቂ እውቀት አላቸው ተብሎ ከሚታመንባቸው ሰዎች፣ ከአርጎባ ልማት ማህበር አባላት፣ መረጃዎች ከተሰበሰቡባቸው ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሠራተኞች መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል፡፡ በዚህ መልኩ የተመረጡ መረጃ አቀባዮች በዕድሜ፣ በትምህርት፣ በኢኮኖሚ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ማህበራዊ ደረጃ አማካይነት ለማሰባጠር ጥረት ተደርጓል፡፡

መረጃ አቀባዮቹ በጾታ ሲገለጹ ሁሉም ወንዶች ናቸው፡፡ ይህም የሆነው በማኅበረሰቡ ባህላዊ ስርዓት መሠረት እንግዳ ሰው ሴቶችን ማነጋገር ስለማይፈቅድ ነው፡፡ የመረጃ አቀባዮች ዕድሜ አዛውንት፣ ጐልማሳ እና ወጣት በሚለው ምድብ ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን፣ የትምህርት ደረጃቸው ደግሞ ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ፣ የኃይማኖት ትምህርት ያላቸው እና ምንም ትምህርት የሌላቸው በሚለው ይመደባሉ፡፡ በማህበረሰቡ

ውስጥ ያላቸውን ማህበራዊ ደረጃና በመንግስት አወቃቀር ያላቸውን ኃላፊነት ስናይ የመንግስት መስሪያ ቤት ኃላፊዎች፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና በማኅበረሰቡ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው አዛውንቶች የተካተቱበት ነው፡፡ ከሚተዳደሩበት ሙያ አንፃር ሲታዩ ደግሞ የመንግስት ሰራተኞች፣ የኃይማኖት ትምህርት አስተማሪዎች፣ ነጋዴዎች እና የእደጥበብ ባለሙያዎች ናቸው፡፡

በዚህ መልኩ ከተመረጡት መረጃ አቀባዮቹ መካከል አስራ አንዱ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ሲሆኑ ሰባቱ ደግሞ አጋዥ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ስለማኅበረሰቡ በቂ የሆነ የታሪክና የባህል ዕውቀት ያላቸው ሆነው በርካታ መረጃዎችን የሠጡኝ ናቸው፡፡ የተቀሩት ግን ክፍተቶችን ለመሙላትና ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት የረዱኝ ናቸው፡፡

## 1.9. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በመስክ ቆይታዬ ወቅት መረጃ ለመሰብሰብ ባደረግኩት እንቅስቃሴ የተለያዩ ችግሮች አጋጥመውኛል። ይሁን እንጂ አቅም በፈቀደ መጠን የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በመጠቀም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በተሳካ ሁኔታ ለመሰብሰብ የሚያስችለኝን ጥረት አድርጌአለሁ፡፡

ካጋጠሙኝ ችግሮች መካከል የመጀመሪያው አብዛኛው የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ሰፍረው የሚገኙት ከከተማ ወጣ ብለው በኰረብታማና በተራራማ ቦታዎች ላይ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ትራንስፖርት እንደልብ አይገኝም፡፡ የቦታው አቀማመጥም እንደ ልብ ተንቀሳቅሶ መረጃ ለመሰብሰብ አድካሚ ስለሆነ የማኅበረሰቡ አባላት ካደረጉልኝ ድጋፍ በተጨማሪ በእግሬ ተጓጉዤ መሥራት ባልችል ኖሮ አላማዬን ማሳካት አልችልም ነበር፡፡

እንደ ሁለተኛ ችግር የሚጠቀሰው ስለ አርጐባ ታሪክና ባህል ያውቃሉ የተባሉ ሰዎች መረጃ ለመስጠት መፍራት፣ መጠራጠር ወይም ከወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ፈቃድ እንዳገኝ ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ የነበረ ሲሆን፣ አስቀድሜ ከአንዳንድ የማኅበረሰቡ ተወላጆች ጋር በስልክ የፈጠርኩት መግባባት በቆይታዬ ጥሩ ግንኙነት መስርቼ መረጃዎችን እንድሰበስብ አስችሎኛል፡፡

እንደ ሦስተኛው ችግር የሚነሳው የአርጐባ ማኅበረሰብ የእስልምና እምነት ተከታዮች በመሆናቸው ሴቶቻቸው ከወንድ ጋር እንዲወያዩ ፈቃደኛ አለመሆን ነው። ወላጆቻቸው

ወይም ባሎቻቸው ሳይፈቅዱ ከሴቶች ጋር መገኘት ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በመፍራት ሴቶችን በመረጃ አቀባይነት ለመጠቀም ያልቻልኩ ሲሆን፣ ተፈላጊውን መረጃ ከወንዶች ለመሰብሰብና የተሟላ ለማድረግ ጥረት አድርጌአለሁ፡፡

በመጨረሻ ሊነሳ የሚችለው በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ መረጃ አቀባዮችን በሥራ ላይ እያሉ አግኝቼ መረጃ ለመሰበሰብ አስቸጋሪ ሁኔታ የገጠመኝ ሲሆን፣ ከአርጐቦች ጋር ውዬ በማደር መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የጥናቱ አካባቢ ዳራዊ ምልከታ

### 2.1. የአርጐባ ማኅበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ

የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ከየትና መቼ መጡ? በምን ምክንያት መጡ? የሚሉና እነዚህን የመሳሰሉት ጥያቄዎች ሲነሱ አንዳንድ የጽሁፍ ማስረጃዎችና የማኅበረሰቡ ተወላጆች የተለያዩ ምላሾችን ይሠጣሉ፡፡ አርጐቦች ራሳቸውን ከእስልምና ኃይማኖት መምጣት ጋር አያይዘው ስለሚተርኩ "አረብ ነን" ይላሉ፡፡ ዝርያቸውንም ከቁራይሽ ነገድ ተወላጅ ከነብዩ መሀመድ ጋር ያገናኙታል፡፡

የአርጐባ ማኅበረሰብ መሠረተ አመጣጥን በሚመለከት ሦስት የተለያዩ አመለካከቶች እንዳሉ (Weeks, 1984, 50-51፣ ተስፋዬ፣ 1991:3- 4) ያስረዳሉ፡፡ የመጀመሪያው ከዛሬ ስምንት መቶ ዓመት በፊት በኒ ኡመያ የተባለ የአረብ ጐሳ የፖለቲካ ሥልጣኑን በሌላ ጐሳ ሲነጠቅና በፍልሰት በዓለም ላይ ሲሠራጭ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ይነገራል፡፡

ሁለተኛው በነብዩ መሀመድ ዘመን በነብዩና በሌሎች የሐይማኖቱ መሪዎች መካከል በተከሰተው ግጭት ምክንያት ሠማንያ ሁለት የነብዩ ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በአፈታሪክ እንደተነገረው ለንጉሥ አህመድ ነጃሺ የእስልምና ኃይማኖትን እንዲቀበሉ የተፃፈውን ደብዳቤ ካደረሱ በኋላ ይፋት[2] አካባቢ ስለመስፈራቸው የሚነገረው ነው፡፡

ሦስተኛውና የመጨረሻው አርጐቦች ከውጪ የመጡ ሳይሆኑ ቀደምትነት ያላቸው በኢትዮጵያ የነበሩ ተወላጆች እንደሆኑ የሚገልፀው ነው፡፡ ይህም አርጐቦች ከአረቢያ የመጡ የእስልምና ኃይማኖት መሪዎችን ትምህርት በቀዳሚነት ተቀብለው ሐይማኖቱን ያደራጁና የተከተሉ መሆኑን ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩልም አርጐቦች መጀመሪያ በሰሜን ኢትዮጵያ የንግድ በር በሆነችው ምጽዋ በኩል አድርገው ወደ ማዕከላዊ ሸዋ ደጋማ ክፍል በኋላም ወደ ደቡብ ክፍለ ሀገር የገቡ እንደሆነ (Taddesse, 1972, 51; Aklilu 2000, 174) ሲያስረዱ፤ Sergaw በበኩላቸው በምስራቅ ኢትዮጵያ የንግድ ወደብ በነበረችው ዘይላ አድርገው ቆላ ቆላውን የአፋር መሬትን መያዛቸውን፣ በኋላም የሸዋን

[2] በአሁኑ ሰዓት ሰሜን ሸዋ ተብሎ የሚታወቀው አካባቢ በሙሉ ቀደም ሲል ይፋት እንደሚባል ሼህ መሐመድ አወል (አንኮበር፣ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም) ይገልፃሉ፡፡

ደጋማ ቦታዎች አልፈው ወደ ደቡብ ምስራቅ ክፍለ አገር እስከ ባሌ መድረሳቸውን ያስረዳሉ (1972፣ 223)፡፡

## 2.2. የአርጐባ ማኅበረሰብ መልክዓ ምድራዊ ስርጭት

የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት በተለያዩ ምክንያቶች በመበታተን በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የአርጐባ ብሔረሰብ ልዩ ወረዳ በማለት በአማራ ክልል ምክር ቤት አዋጅ ቁጥር 130/98 ሰኔ 10 ቀን 1998 ዓ.ም የራሳቸውን ልዩ ወረዳ አቋቁመዋል። ወረዳው ከደቡብ ወሎ ዞን አምስት ቀበሌዎችንና ከኦሮሞ ዞን ሁለት ቀበሌዎችን በድምሩ ሰባት ቀበሌዎችን አካትቶ በመያዝ የተመሰረተ ነው። ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በተገኘው መረጃ መሠረት የአርጐባ ብሔረሰብ ልዩ ወረዳ አስተዳደር ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል በጊዜያዊነት በሃርቡ ከተማ ቆይቷል። ከሚያዝያ ወር 2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጥር ወር 2001 ዓ.ም ድረስ በ2.5 ሚሊዮን ብር የተለያዩ ቢሮዎችንና ህንፃዎችን በማስገንባት የወረዳዋ ዋና ማዕከል የሆነችው መዲና ተከተመች።

የወረዳው ዋና ከተማ የሆነችው መዲና ከአዲስ አበባ ደሴ በሚወስደው መንገድ ከከሚሴ በስተምስራቅ ገባ ብላ በ50 ኪሎ ሜትር ወይም ከአዲስ አበባ በ375 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። የወረዳዋ የቆዳ ስፋት 27 ሺ.ህ 800 ሄክታር ሲሆን የመሬት አቀማመጡም 5 በመቶ ሜዳማ፣ 80 በመቶ ተራራማ፣ 5 በመቶ ወጣ ገባ፣ ቀሪው 10 በመቶ ረባዳ (ሸለቆ) አለው። 95 በመቶ የሚሆነው የወረዳዋ ህዝብ ዋነኛ መተዳደሪያው የእርሻ ሥራ ሲሆን፣ ካለው የቆዳ ስፋት 6 ሺ.ህ 265 ሄክታር መሬት በመታረስ ላይ ይገኛል። ከአየር ንብረት አንፃር ስንመለከት ቆላማ 65 በመቶ፣ ወይናደጋ 30 በመቶ፣ እና ደጋ 5 በመቶ የሆነ የአየር ንብረት አለው (አህመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም.)። ከ"Federal Democratic of Ethiopia Population Census Commission Cenetral Statistical Agenecy" በተገኘ መረጃ መሠረት በ2007 በተካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ የወረዳዋ ህዝብ ቁጥር 17 ሺ.ህ 998 ወንድ፣ 17 ሺ.ህ 288 ሴት በድምሩ 34 ሺ.ህ 998 ህዝብ ይደርሳል፡፡ በአማራ ክልል በተለያዩ ዞኖች የሚኖሩት የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ብዛት ደግሞ 35 ሺ.ህ 469 ወንድ፣ 34 ሺ.ህ 543 ሴት በድምሩ 70 ሺ.ህ 12 ህዝብ ይኖራል፡፡

የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በአፋርና በሐረሪ ብሔራዊ ክልሎች ውስጥ ተሰራጭተው ይኖራሉ፡፡ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ በሦስት

ዞኖች ውስጥ ሠፍረው ይገኛሉ፡፡ በደቡብ ወሎ ዞን በአርጎባ ብሔረሰብ ልዩ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ፈጠቆማ፣ አሬራ ነችሮ፣ ጮምዬ፣ አምዬ ሠርጤ፣ ኪልኪሎ፣ መዲናና አፋሶ መንደሮች፤ በኦሮሞ ልዩ ዞን በአሡኔ አገር፣ ጉበራ፣ ሸንኬ፣ ጦለሃ፣ ጅሌና ጥሙጋ፣ አርጡማ፣ ፋርሲ፣ እስዬ ጉላ፣ ጨፋ ጉላና ደዌ መንደሮች፤ በሰሜን ሸዋ ዞን በቀወት ወረዳ ሸዋ ሮቢት አካባቢ፣ ጉዜ፣ ራሳ ጉባ፣ ማፉድ ሲገኙ ከአንኮበር በታች ደግሞ አልዩ አምባ እና አብዱረሱል ይገኛሉ (አህመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም፤ ሙሉጌታ፣ አንኮበር፣ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም፤ ተስፋዬ፣ 1991፣ 1፤ ዐቢዩ፣ 2000፣ 39)፡፡

አርጎቦች በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሁለት ዞኖችና በአራት ወረዳዎች ይገኛሉ፡፡ በምስራቅ ሐረርጌ ዞን በፈዲስ ወረዳ በጉረአጣሬ፣ አፌይዘር፣ ኢሳቆይ፣ እሺዩ፣ ገንዳ አደም፣ አተር፣ ኡርዴ፣ አዳሻ፣ ቃልያ፣ አዳዲ፣ ሻንቆ፣ ዑመሬ፣ ሐጂ ሹዓ፣ በሮፍሬ፣ አሬዳ፣ ገንዳጋራ፣ ጉተሸ፣ ኑሬ፣ ክሊጨ፣ አረር ሐመሮ፣ ፈካቲ፣ ሳዲቆ በርበሬ፣ ሮሪሶ፣ ቀላድ፣ ቁሉሊት፣ ጦውኮ፣ አደምራሬ፣ ዑመርኩሌ፣ በሬዳ፣ አዳም ሐኮላ፣ ቁማሽ ሲገኙ፣ በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ደግሞ በሚኢሶ ወረዳ በቦርደዴ፣ በአሥቦት፣ በሚኢሶ ከተሞች፤ በጭሮ ወረዳ በለጋ አርባ ቀበሌ፤ በአንጫራና ጉርባ ቆርቻ ወረዳ በጨለቅለቃ፣ ፈራ በበሴ፣ በአዳኤሊ፣ በገዳ አምባ፣ በቦራዲያ፣ በጮሮራና በበዴሳ አካባቢዎች እንደሚገኙ (Tesfaye, 2000, 196፤ ተስፋዬ፣1991፣ 1-2) ይገልፃሉ፡፡

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ደግሞ በጋቸኔ ልዩ ወረዳ በሱፍ አገር፣ በአባሌ፣ በላይ መጠቅለያ፣ በታች መጠቅለያ፣ በቢሉ፣ በጪሳ፣ በወርክ አምባ፣ በማት አምባ፣ በጨኖ፣ በኬይራምባ፣ በቆራሬ፣ በአረፍ ልቤ እና በመልከ ሰዲ መንደሮች ሲገኙ፤ በፈንታሌ ወረዳ ደግሞ በአዋሽና በመተሀራ ከተሞች ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በአሚባራ ወረዳ ውስጥ በመልካ ወረር በስፋት ሠፍረው ይገኛሉ (Tesfaye, 2000, 196፤ ተስፋዬ፣ 1991፣ 1)፡፡ ማኅበረሰቡ በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥም በሁንዳኔ ወረዳ፣ ውስጥ በሚገኙት ኮረሚ፣ ኡመርዲን፣ ሐልሎ፣ ኤሊዲ፣ ወርራአዋ፣ አለላ፣ አፈር ደባ፣ ቃቂ በሚባሉት መንደሮች ሠፍረው ይገኛሉ፡፡

## 2.3. የአርጎብኛ ቋንቋ

የአርጎባ ማኅበረሰብ አባላት የሚናገሩት ቋንቋ "አርጎብኛ" ይባላል (Aklilu 2000, 175፤ Tesfaye, 2000, 197)፡፡ አርጎብኛ ቋንቋ ከኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋ ቤተሰብ ከግእዝ፣ ትግረ፣ ትግርኛ፣ አማርኛ፣ ሐረሪና ከተለያዩ የጉራጌ ቋንቋዎች ጋር ይመደባል፡፡

(Bender 1976፣ 30፤ ጌታሁን፣ 1996፣ iv) የአርጐብኛ ቋንቋ እንደ አማርኛ ዘዬ እንደሚቆጠር እና ቋንቋውም ወደ አማርኛ መቀየሩን ያስረዳሉ፡፡ Stitz የአርጐብኛ ቋንቋ ከሌሎች የሴም ቋንቋዎች ጋር ሲነፃፀር እምብዛም አይታወቅም ይላሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ እንደ ጋፋተኛ ጭራሽ የጠፋ ቋንቋ አይደለም፡፡ በምስራቅ ሸዋና በወሎ አካባቢ የተካሄዱ ጥናቶችን መሠረት በማድረግ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ተናጋሪዎች እንዳሉት (1973፣ 185) ያስረዳሉ፡፡ ቋንቋው ፊደል ያልተቀረፀለትና በሥነ-ጽሁፍ ላይ ያልዋለ ነው (Tesfaye, 2000: 197)፡፡ የአርጐባ ማኅበረሰብ አሰፋፈር ከአማራ፣ ከአፋር፣ ከኦሮሞ ማኅበረሰብ ጋር የተሰበጣጠረ በመሆኑ፤ ልሳነ ብዙ (ከአንድ በላይ ቋንቋ ተናጋሪ) መሆን ችለዋል (Aklilu, 2000: 174)፡፡

የአርጐብኛ ቋንቋ በስፋት የሚነገርባቸው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በኦሮሞ ልዩ ዞን ውስጥ በሚገኙት በሸንኬና በጦለሃ መንደሮች ሲሆን፣ በሌሎች ክልሎችም ውስጥ በሚገኙት አንዳንድ መንደሮች ውስጥ ቋንቋው በአመዛኙ በሴቶችና በወጣቶች ይነገራል፡፡ ቋንቋው በጊዜ ብዛት በሌሎች ቋንቋዎች እየተዋጠ መሆኑን (Tesfaye, 2000: 197) ያስረዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ሰዓት በአፍ መፍቻነት እየተገለገሉበት ሲሆን፣ ለመጀመሪያ ሳይክል ተማሪዎች እንደ አንድ የትምህርት አይነት በሳባ ግእዝ ፊደል እየተሰጠ መሆኑን የዚህ ጥናት ጽሁፍ ተመራማሪ በመስክ ቆይታው ተረድቶታል፡፡

የአርጐብኛ ቋንቋ በሁለት ዘዬዎች የተከፈለ ነው፡፡ እነዚህም የሸንኬ እና የሸዋ ሮቢት ዘዬ በመባል ይታወቃሉ፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከህፃን እስከ አዋቂዎች ቋንቋውን በአፍ መፍቻነት የሚገለገሉት በደዌ ጨፋ ወረዳ በሕጅሮታ ቀበሌ በሸንኬ፣ በጦለሃ፣ በቁኒ፣ በፈረጃና በመጋረጃ የሚገኙ ማኅበረሰቦች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በአርጐባ ብሔረሰብ ልዩ ወረዳ በሚገኙ ወበራና ሐሰኜ ቀበሌዎች የሚገለገሉበት ሲሆን፣ በሸዋ ሮቢት ዘዬ ደግሞ በቀወት ወረዳ ወስጥ እየተነገረ ይገኛል፡፡

## 2.4. የአርጐባ ማኅበረሰብ የኢኮኖሚ ሁኔታ

የአርጐባ ማኅበረሰብ አሠፋፈር በኮረብታማና በተራራማ ቦታዎች ላይ ቢሆንም አብዛኛው ኅብረተሰብ ተሰማርቶ የሚገኘው በግብርና ሥራ ላይ ነው። ከእርሻ ሥራ በተጨማሪ በሽመና በንግድ ሥራ እና በእደ ጥበብ ሙያዎች ላይም ተሰማርተው ይገኛሉ።

አርጐቦች በአብዛኛው የሚያመርቱት የማሽላ ሰብል ሲሆን፣ ገብስ፣ ዘንጋዳ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ምስር፣ ተልባ፣ ሽንብራ፣ ሰሊጥ፣ ኑግ፣ በርበሬ፣ ቡና፣ ለውዝ፣ ጥጥና ፍራፍሬዎችንም በብዛት ያመርታሉ። እነዚህን ምርቶች በአብዛኛው ለራሳቸው ፍጆታ የሚጠቀሙባቸው ሲሆን፣ አስፈላጊ የሆኑ ቁሶችን ለመግዛት ሲባል ለገበያም ያቀርቧቸዋል (አብዱሰላም፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም.፤ ተስፋዬ፣ 1991፣ 24)።

የአርጐቦች ሌላ መተዳደሪያ ሥራ ንግድ ነው። የንግድ ሥራ ከማኅበረሰቡ ታሪካዊ አመጣጥ ጋር የተያያዘ መሆኑ በተወላጆች ይገለጻል። አርጐቦች የመጀመሪያዎቹ የአገሪቱ የእስልምና እምነት ተከታይ መሆናቸውን ሲገልጹ ከዚህ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ እና የአረብ ንግድ መስመርን ተከትለው ንግድን የመሠረቱ ጥንታዊያን ህዝቦች እንደሆኑ ይነገራል።

በአርጐባ ማኅበረሰብ ዘንድ የእደ ጥበባት ሙያ ዘርፎች ተዘውትረው ይከናወናሉ፡፡ በስፋት ከሚታወቁት መካከል የቆዳ፣ የእንጨት፣ የስፌትና የሽማ ሥራዎች ይገኙባቸዋል፡፡ ጥጥ በብዛት የሚመረት ሲሆን፣ ሴቶች ፈትለው ካዘጋጁ በኋላ ወንዶች የተለያዩ የወንድና የሴት ልብሶችን በመሥራት ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸውና ለገበያም አገልግሎት ያውላሉ፡፡ በተለይ መሬት ወይም ሌላ መተዳደሪያ የሌላቸው አርጐቦች ከጥጥ ፈትል፣ የሚሠሩትን ልብስ ወደ ገበያ አውጥተው በመሸጥ ኑሮአቸውን ይመራሉ (ተስፋዬ፣ 1991፣ 25)፡፡

የብረታ ብረትና የሸክላ ሥራ ውጤቶችን ገንዘብ ወይም እህል እየሰጡ ያሠራሉ፡፡ እነዚህን ሥራዎች እራሳቸው አይሰሯቸውም ምክንያቱም "ነውር" ነው የሚል አስተሳሰብ በማኅበረሰቡ አባላት ዘንድ በመኖሩ ነው፡፡ በተለይም የብረት ሥራ የሚሠራ ሰው "ቡዳ" ነው የሚል አመለካከት አላቸው (አሚኑ፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም.፤ ሼህ መሀመድ፣ አንኮበር፣ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## 2.5. የአርጐባ ማኅበረሰብ የጋብቻ ስርዓት

የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡ በማኅበረሰቡ የሸሪዓ ህግ በስፋት ተቀባይነት ስላለው አንድ ወንድ አቅሙ ከፈቀደ እስከ አራት ሚስት ድረስ ማግባት ይችላል (ነጋሽ፣ 1981፣ 17)፤ ወንድሙ ከሞተ የወንድሙን ሚስት መውረስ ይችላል፡፡ በማኅበረሰቡ ባህል መሠረት ወንዱም ሆነ ሴቷ ከአጐቱ(ቷ) ወይም ከአክስቱ (ቷ) ልጅ ጋር ወይም ከዚያ መለስ ካሉ ዘመዶች ጋር እንዲጋቡ ይፈቀዳል፡፡

የአርጐባ ማኅበረሰብ ጋብቻ የሚፈጽሙት ከራሳቸው ጐሳ/ነገድ/ ጋር ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት የራሳቸውን ባህልና ታሪክ በአግባቡ ለመጠበቅና ለመንከባከብ እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር የሚያደርጉት ጥረት እንደሆነ (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም) ይገልፃሉ፡፡

## 2.6. የአርጐባ ማኅበረሰብ የሐዘን ስርዓት

በአርጐባ ማኅበረሰብ ወንድ ሲሞት እንደሌላው የአገሪቱ ሙስሊም ማኅበረሰብ ሁሉ አስከሬኑ ይታጠብና በፍጥነት ወደ መስጊድ ይወሰዳል፡፡ ሟቿ ሴት ከሆነች ግን አስከሬኗ ታጥቦ የሴት ጠባቂዎች ከአጠገቧ ተቀምጠው እንክብካቤ[3] ያደርጉላታል፡፡ የወንድም ሆነ የሴት አስከሬን ውሎ አያድርም፡፡ በሞቱበት ዕለት ይቀበራል፡፡ የቀብሩ አፈፃፀም በቅድሚያ በሟች ቁመት ልክ ወደ ውስጥ ጉድጓድ ይቆፈርና እንደ ገና ወደ ጐን ይማሳል፡፡ ወደ ጐን የሚማሰው ለአስከሬኑ ማስቀመጫ የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ቦታ አፈሩ በሚመለስበት ጊዜ አስከሬኑን አፈር እንዳይነካው በጥርብ ድንጋይ ይዘጋል (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡ አስከሬኑ ወደ መስጊድ ሆነ ወደ ቀብር ቦታ ሲሄድ ሴቶች አይከተሉም፡፡ ፀጥታ በተላበሰ ሁኔታ የፀሎትም ሆነ የቀብሩ ሥነ-ስርዓት ይከናወናል፡፡

ከቀብሩ በኋላ የሐዘኑ ሥነ-ስርዓት የሚካሄደው በመስጊድ ነው፡፡ ለቅሶ ደራሽ ወንዶችና ሴቶች ተለያይተው በመቀመጥ ሐዘናቸውን ይገልፃሉ፡፡ የሐዘኑ ቀን የሚወሰነው በሟቹ(ቿ) ዕድሜ መሠረት ነው፡፡ ሟቹ(ቿ) ትልቅ ከሆነ(ች) ለሰባት ቀን፣ ህፃን ከሆነ(ች) ደግሞ ለሦስት ቀን የሐዘን ጊዜው ይቆያል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ቤተ ዘመድና ጐረቤቶች ምግብ በማዘጋጀትና በማጽናናት አብረው ያሳልፋሉ፡፡ የቀብር ሥነ-ስርዓት በተፈፀመ በ7ኛው ወይም በሦስተኛው ቀን የመቃብሩ ዙሪያ በድንጋይ ይካባል፡፡ በመቀጠልም በመቃብሩ ላይ ለሟቹ(ቿ) ዱአ በማድረግና የሟች ቤተሰቦች እንዲጽናኑ ሐይማኖታዊ ምክር በመለገስ የሐዘኑ ሥነ-ስርዓት ይፈፀማል፡፡ በማኅበረሰቡ ባህል መሰረት አንድ ሰው ሲሞት ኡኡ ብሎ ደረትን በመምታት ማልቀስም ሆነ ራስን መላጨት አይፈቀድም፡፡ በተለይ ወንድ ልጅ ድምጽ እያሰማ አያለቅስም፡፡ ሴቶች ግን መጠነኛ ድምጽ እያሰሙ ሊያለቅሱ ይችላሉ፡፡ አንዳንዴ ግን ለሟች ቅርበት ያላቸው ወንዶች

[3] እንክብካቤ ማለት አስከሬኑን በመገነዝ ጢስ በማጢስ እና ሽቶ በመቀባት ጥሩ ማዕዛ እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡

ድምጽ እያሰሙ የሚያለቅሱበት ሁኔታ እንዳለ (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.) ገልፀዋል፡፡

በማኅበረሰቡ ባህል መሰረት ባሏ የሞተባት ሴት ለአራት ወር ከአስር ቀን ቅቤ አትቀባም፡፡ ሐዘኗን ለመግለጽ "ሙሀሙዲ"ን የተባለ ልቅ፣ ሰፊ ነጭ ቀሚስ ትለብሳለች፡፡ ወንዶች ለሐዘን ተብሎ የሚለብሱት የተለዩ ልብስ የለም፡፡ ለሟች ከተቻለ በዓመት ሁለት ጊዜ ካልተቻለ ግን አንድ ጊዜ ሰደቃ[4] ይወጣል፡፡

---

[4] ሰደቃ የሚች ቤተሰቦች አርደውና ደግሰው ዘመድ አዝማድን፣ የአካባቢ ሰዎችንና ድሃዎችን መጋበዝ ማለት ነው፡፡ በዚህ ሥነ-ስርዓት ላይ የሃይማኖት መጽሃፍ በማንበብ የሚቹ ህይወት በገነት ተቀምጣ ምህረት እንድታገኝ ብሎም የሚች ቤተሰቦች እንዲጽናኑ ዱአ (ፀሎት) ይደረጋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. ክለሳ ድርሳን

የዚህ ክፍል የትኩረት ነጥብ ጥናቱ የተመሠረተበትን ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት እና ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናቶች መከለስ ነው፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ ጥናቱ የተመሰረተበት ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ምን እንደሚመስል እንመልከት፡፡

### 3.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

#### 3.1.1. ቃላዊ ዝርው ተረክ (Oral prose narrative)

ተረክ ማለት አንድን ልምድ/ተሞክሮ/ በቃል ማስተላለፍ ነው፡፡ ተረክ ሙሉ ለሙሉ የአንድ ማኅበረሰብ መረጃ /ልምድ/ የመለዋወጫ መሳሪያ ነው (Oring, 1986:122)፡፡ በተረክ ውስጥ ድርጊትና ሁነት የግድ የማይቀሩ ሁለት ነገሮች ናቸው፡፡ የድርጊቱና የሁነቱ ባለቤት ገጸባህርያት፣ ድርጊቱንና ሁነቱ የሚፈፀምበትን ስፍራና ጊዜ ይዘው አብረው ይመጣሉ ማለት ነው፡፡ ተረክ "ታሪኩን፣ ትረካውን እና የሚቀርብበትን መንገድ (ሁኔታ) አጠቃሎ ይይዛል፡፡ ተረክ በቃል አልያም በጽሁፍ ሊቀርብ እንዲሁም በግጥም ወይም በዝርው ሊተረክ ይችላል፡፡ ከዚህም አልፎ ሊዘፈን፣ ሊተወን፣ ሊደነስ፣ ሊሳል፣ ሊቀረጽ፣ በተለያዩ መንገዶች ሊከወን የሚችል ቅርጽ ነው" (ቴዎድሮስ፣ 2001፣ 259-260)፡፡ ተረክ የያዘው ጽንሠ ሀሳብ በጣም ሠፊ ሲሆን፣ ለዚህ ጥናት እንዲያመች በማለት ግን "ቃላዊ ዝርው ተረኮች" በማለት ለማጥበብ ተሞክሯል፡፡ ይህም ማለት ይህ ጥናት በቃል የሚተላለፉትንና በዝርው የሚቀርቡትን ተረኮች ብቻ የሚመለከት ይሆናል ማለት ነው፡፡

ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር የጠበቀ ትስስር ያላቸውና በዕለታዊ ሕይወት ውስጥ በተለያየ መልኩ የሚከወኑ ታሪኮች ናቸው፡፡ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተከታታይነት ያላቸው ድርጊቶች ወይም ሁነቶች፣ የሚፈፀሙበትን፣ ጊዜና ቦታ እንዲሁም የድርጊቱ ተሳታፊ ባለታሪኮችን ይይዛሉ፡፡ የአንድን ማኅበረሰብ ባህል ለማስተላለፍ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ፈቃደ (1991፡52) ቃላዊ ዝርው ተረኮች በማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ በዕለታዊ ሕይወት በተለያየ መልክ የሚከወኑ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይ Degh ቃላዊ ዝርው ተረኮች በማንኛውም ማኅበረሰብ እንደሚነገሩት ሁሉ በየትኛውም አካባቢና ማኅበራዊ ሁኔታ ሊቀርቡ እንደሚችሉ ይገልፃሉ (1972: 54)፡፡

ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከሰው ወደ ሰው በቃል የሚተላለፉ እንደሆነና የቆይታ ጊዜያቸውም ከአንድ ትውልድ በላይ ሊዘልቁ እንደሚችሉ (Vansina, 1985:101) ያስረዳሉ፡፡ Finnegan በበኩላቸው በማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ህልውናቸው ተጠብቆ የሚቆየው፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ባለው ክዋኔና ከትውልድ ትውልድ በሚደረገው ቃላዊ ተስተላልፎ እንደሆነ (1970: 380) ይገልፃሉ፡፡

Degh በዝርው መልክ የሚቀርቡ ማንኛውም የስነ-ቃል አይነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ይባላሉ (1972፡58) ሲሉ፡፡ Bascom (1996: 3) ደግሞ ቃላዊ ዝርው ተረክ አፈ ታሪክን፣ ተረትንና ሚትን አካቶ የያዘ የስነ ቃል ዘርፍ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

አንድ ማኅበረሰብ ከየት እንደመጣና ወደ የት እንደሚሄድ እንደራሱ የእውቀትና የአረዳድ ደረጃ መግለጹ አይቀርም፡፡ ዓለምን የሚመለከትበት፣ የሚረዳበትና የሚያስረዳበት የራሱ መንገድም ይኖረዋል፡፡ ሰዎች ህይወታቸውን በተቃና ሁኔታ መምራት እንዲችሉ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የተፈለገውን መልእክት በቀላሉ ያስተላልፋሉ። ሚት(Myth) እና አፈ ታረኮች(Legend) "እውነት ናቸው" የሚባሉትን መረጃዎች ስለሚይዙ በማኅበረሰቡ ውስጥ ጥርጣሬና ቅሬታዎችን ያስወግዳሉ። ስለዓለም፣ ስለሰዎች፣ ስለእንስሳትና ስለእጽዋት አፈጣጠር ምላሽ ይሰጣሉ። እነዚህ ሁሉ የተፈጠሩት በመለኮታዊ ኃይል (Super Natural Power) አማካይነት መሆኑን ወልደስላሴ (1972፣ 13) ይገልፃሉ።

በአጠቃላይ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በቋንቋ የሚገለጹ፣ በቃል የሚተላለፉ፣ በጊዜ ቅደም ተከተል የተዋቀሩ ታሪክ ያላቸው፣ በታሪኩ ውስጥ ያለውን ድርጊት የሚፈጽሙ ገጸባህሪያት ያሏቸው የድርጊቶችና ሁነቶች ትረካ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

### 3.1.2. ማንንት (Identity)

Dundes ማንነት ሰው ብቻውን ወይም ከሌሎች ጋር አብሮ በመኖር የሚመጣ ባህርይ ነው፡፡ አንድ ሰው መልኩን ለማወቅ መስታወት መመልከት እንደሚያስፈልገው ሁሉ የሰዎችን ማንነት ለማወቅ ደግሞ ከሌሎች ጋር አብሮ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ሰው ማንነቱን ማወቅ የሚችለው እራሱን በሌሎች ሰዎች ማንነት ውስጥ ማየት ሲችል ነው (1996፣ 5-6) ይላሉ፡፡ ማንነት የሚገለጸው ስለ እራሳችን በምንተርካቸው ተረኮች አማካይነት ሲሆን፣ የምናውቀው ደግሞ እኛ ማን ነን? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ከሆነ ነው (Lwis & Sandra, 2001:17)፡፡

አንድ ማኅበረሰብ ሰዋዊ ግንኙነቱን የሚያከናውነው በቋንቋ አማካኝነት ነው፡፡ እንደ ማኅበረሰቡ አመለካከት ማንነታቸውን በቋንቋቸው ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ምክንያት አንድ ማኅበረሰብ ከሌላው ማኅበረሰብ የሚለይበት የራሱ የሆነ ማንነት አለው፡፡ ማንነት በቋንቋ አማካይነት የሚፈጠር ሲሆን፣ የሰውን ጠላትነት፣ ወዳጅነትና የሰውን አስተሳሰብ ሁሉ በተረኮቻቸው አማካይነት ይፈጥራሉ፡፡ እነዚህ በፎክሎር ከተፈጠሩ ፎክሎር ደግሞ ማኅበረሰቡን ይፈጥራል፡፡ ማኅበረሰቡ ደግሞ ፎክሎርን ይፈጥራል፡፡ በዚህ መልኩ ማንነት በፎክሎር ይገለፃል፡፡ የአንድ ማኅበረሰብ ማንነት በድንገት የሚከሰት ሳይሆን የማኅበረሰቡ የረጅም ጊዜ ታሪክ ውጤት ነው (Henchman, 2001:162) ፡፡

ማንነት አንድ ነገር የያዘውን ሀሳብ ይዞ መዝለቁን ወይም ከሌሎች የተለዩ መሆኑን የሚያሳይ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ይህም ሁለት የማይነጣጠሉ ነገር ግን የሚቃረኑ ቡድኖችን ይመለከታል፡፡ ይህ እኛ እንበልጣለን እናንተ ታንሳላችሁ በሚሉ ሀሳቦች ሊገለጽ ይችላል፡፡ እነዚህ የልዩነት መከሰቻዎች ወይም የእኛ/የእነሱ የሚባሉት ባህል፣ ኃይማኖት፣ ፖለቲካ፣ ዘር፣ ቋንቋ፣ ወዘተ... ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሰዎች እነዚህን በመሳሰሉ የጋራ እሴቶች ላይ በሚደራጁበት ወቅት ብዙ ጊዜ እሴቶቻቸውን የሚመለከቱት ከራሳቸው አንጻር ነው፡፡ በመሆኑም አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት እኛ ትክክል ወይም የተሻልን ነን እናንተ ደግሞ ስህተት ወይም ከእኛ ያልተሻላችሁ ናችሁ በሚል ውሳኔ ላይ ያርፋሉ (Mathisen, 1993: 35-37)፡፡

### 3.1.3. ማንነትና ተረክ (Identity and narrative)

ማንነት እንደ ሥነ- ውበት በሥራ የሚገለጽ እና የሚገነባ ነው፡፡ ለመልካም ሆነ ለተበላሸ ማንነት መገለጫው ከዚህ በፊት የተከናወኑ እና የምንተርካቸው ተረኮች ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ አመንጭ የሆነው ማኅበረሰብ ማንነት መገለጫ እንደሆኑ (Sims, 2001: 121) ይገልጻሉ፡፡ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ በማንነት መገለጫዎች አማካይነት እራሳቸውን ከሌላው ይለያሉ ወይም አንድ ያደርጋሉ፡፡ እኛ እንዲህ ነን ወይም እንዲህ አይደለንም እያሉ እራሳቸውን ከሌላው ይለያሉ፡፡ ይህንንም የሚያከናውኑት በተረኮቻቸው አማካይነት ነው፡፡ አንዳንድ ምሁራን የአንድ ግለሰብ ህይወት ከሌላው የተሻለ ወይም እውነተኛ ነው ብለው አያምኑም፡፡ ሌሎች ግን የተሻለ ወይም እውነተኛ ህይወት የመሆን መለኪያው እራሱ ነዋሪው ግለሰብ የሚሰጠው ብያኔ ነው ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የግለሰባዊ ማንነት ትክክለኛ መገለጫው ተራኪዎች እንደሆኑ የሚያስረዱ

አሉ(Sims, 2001: 120)፡፡ ከዚህ አንጻር የአንድን ማኅበረሰብ ማንነት ራሳቸው ከሚሰጡት ብያኔ በመነሳት መግለጽ እንችላለን ማለት ነው፡፡

የማንነትና የተረክ ግንኙነት በሦስት መልኩ ሊገለጽ እንደሚችል De Finna አስፍረው እናገኛለን፡፡ የመጀመሪያው ተራኪው ተረኩን በሚያቀርብበት ጊዜ ቋንቋውን እና የአገላለጽ ዘዬውን በማጤን ከሌላ ማኅበረሰብ በምን እንደሚለይ መገንዘብ እንደሚያስችል ይገልጻሉ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ተራኪዎች ማኅበራዊ ግንኙነታቸውን በተረኮቻቸው አማካይነት የሚገልጹበት ሲሆን፣ በዚህም ባህላቸውን ያወድሳሉ ወይም ይኮንናሉ፡፡ ሦስተኛውና የመጨረሻው ተራኪው ማኅበረሰብ ከሌሎች አንፃር ሲታይ ምን እንደሚመስል ያሳያሉ(2003:19)፡፡ ከዚህ አንጻር የአርጐባን ማኅበረሰብ ማኅበራዊ ሁኔታ የሰዎች ማንነት በተለያየ መልኩ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ከእነዚህ መካከል የሚኖሩበት አካባቢ፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎቻቸው፣ የሚናገሩት ቋንቋ፣ የሚጨፍሩት ጭፈራና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ጨዋታ ዳንስ ስንል ደግሞ ፎክሎር ማለታችን ነው (Dundes, 1996: 7)፡፡

ማንነት በፎክሎር አማካኝነት ከተፈጠረ፣ የአርጐባን ማኅበረሰብ ከሌሎች ማኅበረሰቦች የተለየ (unique) መሆኑን በቃላዊ ዝርው ተረኮች አማካይነት ማየት ያስችለናል የሚል እምነት አለኝ፡፡ በአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ በመመስረት ይህ ጥናት ተካሂዷል፡፡ ጥናቱ የእነዚህን ማኅበረሰብ ታሪክ፣ አመለካከት፣ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ባህላዊ ስርዓትና የመሳሰሉትን በመረጃዎች አስደግፎ በማጥናት ያቀርባል፡፡

### 3.1.4. ተግባራዊ ሥነ-ዘዴ /Functional Approach/

በአርጐባ ማኅበረሰብ ላይ ትኩረቱን ያደረገው ይህ ጥናት የሚመሰረትበት ሥነ-ዘዴ ተግባራዊ /Functional/ ሥነ-ዘዴ ነው፡፡

ተግባራዊ ሥነ-ዘዴ የዚህ ጥናት ማጠንጠኛ እንዲሆን ምክንያት የሆነኝ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ማንነታቸውን እንዴት ይገነቡታል? ያላቸውን ታሪክ፣ ባህልና ልምድ እንዴት ያስተላልፉታል? እነዚህ ታሪኮች፣ ባህልና ልምዶች ለወጣቱ ትውልድ ምን ፋይዳ አላቸው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ከተግባራዊ /Functional/ አንፃር መመርመሩ የተሻለ ነው የሚል እምነት ስላሳደረብኝ ነው፡፡ ስለሆነም ተግባራዊ /Functional/ ሥነ-ዘዴን ቀጥለን እንመልከት፡፡

ተግባራዊ /Functional/ ሥነ-ዘዴ ቃላዊ፣ ልማዳዊና ቁሳዊ ስብስቦችን የያዙ ፎክሎሮች ለማኅበረሰቡ ለምን እና እንዴት ይጠቅማሉ የሚለውን የሚያጠና ነው፡፡ እንደ (Sims et al.,2005, 175) ገለፃ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ የአንድን ቡድን ቃላዊ፣ ተለምዷዊና ጽሁፋዊ ሰነዶች በመመርመር ሰዎች እነዚህን ጉዳዮች ለመጋራት ካላቸው ጥቅም አንፃር ለምንና እንዴት በሚሉ ጥያቄዎች አማካይነት ፈትሾ ተግባራቸውን የሚያሳይ ሥነ-ዘዴ ነው፡፡ ፎክሎርን ስለመተንተን ስንናገር ሰዎች ብዙ ጊዜ "ፎክሎር ለቡድኑ አባላት ምን ያስተላልፋል? ይህንን የሚጋራውስ ማን ነው?" የሚሉ ጥያቂዎች ይጠይቃሉ፡፡ የፎክሎር ባለሙያዎች ትርጉም (Meaning) ፎክሎር በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን ተግባር (ሙ.ያ) መመርመሪያ መንገድ መሆኑን ትኩረት ማድረግ አለባቸው፡፡

ተግባራዊ /Functional/ ሥነ-ዘዴ የፎክሎሩን ይዘት ከፎክሎሩ ባለቤት ጋር አጣምሮ ፎክሎር ባለው ትርጉም ላይ በመመስረት ተግባሩን ለመተንተን የሚያስችል ሥነ-ዘዴ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ፎክሎር ለቡድኑ አባላት የሚያስተላልፈው ትርጉም ምንድን ነው? እነማን ናቸው ይህንን ትርጉም የሚጋሩት? የሚሉትን ጥያቄዎች እያነሳ ፎክሎር ለአንድ ማኅበረሰብ ወይም ቡድን ያለውን ተግባር ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ ተግባራዊ ሥነ-ዘዴ የአንድ ማኅበረሰብ ስርዓት ፣ ወግና ልማድ ባላቸው ትርጉም መነሻነት ለዚያ ማኅበረሰብ የሚሰጡትን አገልግሎት ተንትኖ የሚያቀርብ ነው፡፡

የጥንታዊ ተግባራዊ /Functionalism/ ሥነ-ዘዴ አራማጅ Bascom ፎክሎር አራት ጥቅሞች እንዳሉት ይገልፃሉ፡፡ የመጀመሪያው የማስተማር ተግባር ነው (Sims et al.,2005, 175፣ ፈቃደ፣ 1991፣ 20)፡፡ የማኅበረሰቡ ሀብት የሆኑት ፎክሎሮች ማኅበረሰቡ የሚከተለውን ስርዓት፣ ህይወቱን የሚመራበትን መንገድ፣ መልካም የሚባሉና የሚመሰገኑ ምግባራትን ያስተምራሉ፣ ያንፃሉ፡፡ ይህንን በሚመለከት ስነቃሎች የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ የአለባበስ፣ የአቀማመጥ፣ የአነጋገር፣ የአካሄድ ስርዓትን ያሳውቃሉ፡፡ በህይወት ውስጥ የትጋትን፣ የለጋስነትን የህብረትን፣ ጥቅም አጥብቀው ይሰብካሉ በማለት ፈቃደ (1991፣ 20) አስፍረዋል፡፡

Bascom በሁለተኛ ደረጃ የገለጹት የፎክሎር ተግባር የማምለጥ ተግባር ነው፡፡ ፎክሎር ከውሱንና በባህል ስም ከተጫኑብን ስርዓቶች ማምለጫ ነው(Sims et al.,2005, 176)፡፡ ፎክሎር ከአሰልችና ከተደጋጋሚ የህይወት ክስቶች እንድንወጣ ያደርገናል፡፡ ይህም ደስታንና ፈንጠዝያን ይፈጥርልናል (ፈቃደ፣ 1991፣ 18)፣ በመሆኑም ሰው በፎክሎር እየተዝናና የሚያስበውን ነገር ሁሉ ከኅብረተሰቡ ህግ አፈንግጦ በመግለጽ ያመልጣል፡፡

ለምሳሌ ተራቹ የራሱን የፈጠራ ሀሳብ እንዲጨምር እድል የሚፈጥርለት ሲሆን አድማጩም በተራቹ የፈጠራ ችሎታ እየተዝናና ለተወሰነ ጊዜ የሆነውና የተደረገው ነገር ሁሉ እንዳልሆነና እንዳልተደረገ፣ ያልሆነውንና ያልተደረገውን ጉዳይ እንደሆነና እንደተደረገ አድርጎ እንዲያስብ ስለሚያስችል ከመደበኛው ህይወት ወጥቶ አዲስ ህይወት ውስጥ እንዳለ አድርጎ በመቁጠር የተወሰነ እረፍት ያገኝበታል ማለት ይቻላል፡፡

ሦስተኛው በBascom የተጠቀሰው የፎክሎር ተግባር የመጠበቅ ወይም የመቆጣጠር ተግባር ነው፡፡ ፎክሎር በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያገኙ ተመሳሳይ ባህርያትን የመጠበቅ ወይም የመቆጣጠር ተግባር አለው፡፡ ባህል በተፈለገ ጊዜ አንድን ሰው ወደተረጋገጠ የባህርይ መስመር ይመልሳል (Sims et al.,2005: 176)፡፡ ይህም ማኅበሩ ምስጉንና ድንቅ ከሚላቸው እሴቶች የሚያፈነግጡትን ወይም ለማፈንገጥ ገና ዳር ዳር የሚሉትን በ"አረፌ-ሀ-ተቀመጥ" ግሳጼ ወደ ብዙሀኑ አስተሳሰብ መመለስ ነው (ፈ.ቃደ፣ 1991፣ 20)፡፡ ማኅበረሰቡ ትክክል አይደሉም የሚላቸውን ስነምግባሮች እንዳይደረጉ፣ እንዳይስፋፉ በመጠበቅ የማህበሩን ደህንነት ለመቆጣጠር ጥረት ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ፎክሎሮች ማህበሩ ስህተት የሚላቸውን ባህርያት በማረም ትክክለኛ ነው በሚለው መስመር ውስጥ አባላቱ እንዲንቀሳቀሱ የመጠበቅ ተግባር አላቸው፡፡

አራተኛው የፎክሎር ተግባር የባህልን ትክክለኛነት /ምክንያታዊነት/ የማረጋገጥ ወይም የማጽደቅ ተግባር ነው፡፡ ስርዓትን በማክበር፣ እነዚህ ድርጊቶችና ሁነቶች በማኅበረሰቡ ህይወት ውስጥ ቦታዎች እንዲኖራቸው በማድረግ ባህልን የማረጋገጥ ተግባር ይፈጽማል (Sims et al.,2005:176)፡፡ የአንድን ቡድን ፎክሎር በተለይ በሀተታ ተፈጥሮ አማካይነት እምነቶችን፣ ባህርያትንና ስርዓቶችን የማጽናት ተግባር አለው (Dorson, 1972: 22)፡፡ ፈቃደም ይህንን ሀሳብ በመደገፍ የቡድኑ አባላት በስነቃል አማካይነት ከልደት እስከሞት የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነትና ተገቢነት እያሳመኑ ክንዋኔዎቹ እንዳይከስሙ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ (ፈ.ቃደ፣ 1991፣18) ይላሉ፡፡ ይህ የፎክሎር ተግባር ማኅበረሰቡ በሚከተላቸውና በሚያከብራቸው እምነቶች፣ እሴቶችና ትውፊቶች ውስጥ ያሉ ጉዳዮች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ የማሳየት ወይም የማጽደቅ ተግባር አለው፡፡ በመሆኑም ፎክሎር እነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች እንዲቀጥሉ በተለያዩ ሁኔታዎች አማካይነት የማጠናከር ተግባር አለው ማለት ይቻላል፡፡

ፎክሎር የነበረውን ባህል ቀጣይነት እንዲጠበቅ የሚያደርግ ጠቃሚ መንገድ ነው የሚለው የባስኮም ድምዳሜ በእምነትና በአመለካከት ውስጥ ያለውን ለውጥ የማያካትት መሆኑ በተግባራዊ ሥነ-ዘዴ ላይ እንደ ድክመት የሚጠቀስ መሆኑንም ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ሌላም ይህ ሥነ-ዘዴ በራሱ ወግ አጥባቂና ለተለያየ አመለካከት እድል የማይሠጥ/ግትር/ ነው የሚል ትችት በብዙ ምሁራን እንደሚቀርብበት (Sims et al.,2005: 177) ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም ይህ ሥነ-ዘዴ ካሉት አዎንታዊ ገጽታዎች ውስጥ አንዱ ለፎክ ቡድኑ ትኩረት ያደረገ መሆኑና ፎክሎር በቡድኑ አባላት ትርጉም እንዳለው ተደርጎ እንዲታሰብ ማድረግ መቻሉ ትልቅ ግምት የሚሠጠው ነው፡፡

## 3.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል በአርጎባ ማኅበረሰብ ትኩረት ያደረጉ አንድ የመጀመሪያ ዲግሪና አንድ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ተዳስሰዋል፡፡ እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር፣ በውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ የትምህርት ክፍሎች በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ የተሰሩ አስራ ሁለት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶችን ለመቃኘት ሞክሬያለሁ፡፡

### 3.2.1. በአርጎባ ማኅበረሰብ ላይ የተሠሩ ጥናቶች ቅኝት

ነጋሽ (1981) "አርጎብኛና የአርጎቦች ህይወት በሁለት (አልዩ አምባና አዋሽ) ከተሞች ውስጥ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት አድርገዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የተለያዩ ምሁራን በተለይም ከውጪ የመጡ የስነ ልሳንና አልፎ አልፎ የታሪክ ሊቃውንት ለጥራዝ ባበቋቸው ጽሁፎች ላይ ስለ አርጎብኛ ቋንቋ የሰጧቸው አስተያየቶች ምን ያህል እውነታ እንዳላቸው ማረጋገጥ ነው፡፡ ቀደምት አጥኚዎች ስለ አርጎብኛ ቋንቋ የሠጡት ማጠቃለያ ወጥነት የጎደለውና በሀሳብ የሚስማማ ስላልሆነ ጥናቱ ለሌሎች አጥኚዎች መነሻ እንዲሆን ማድረግ ሌላው የጥናቱ ዓላማ እንደሆነ ገልጾዋል፡፡

የጥናቱ የትኩረት ነጥብ የአርጎብኛ ቋንቋ የሚገኝበትን ሁኔታ መቃኘት ይሁን እንጂ፣ እግረ መንገዳቸውን ስለ አርጎባ የትመጣነት፣ የማኅበረሰቡ አባላት ስለሚገኙባቸው ስፍራዎችና ስለባህላቸው በመጠኑ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

ነጋሽ ጥናቱን ባካሄዱበት አልዩ አምባና አዋሽ ከተሞች ውስጥ ከልጆች ይልቅ አዋቂዎች ብዙ ጊዜያቸውን ከሌሎች ብሔረሰብ አባላት ጋር ከሚያሳልፉት ይልቅ በመኖሪያ

አካባቢያቸው ተወስነው የሚኖሩት ቋንቋውን አዘውትረው እንደሚገለገሉበት አመልክተዋል፡፡ በአልዩ አምባ የሚኖሩ አርጐቦች ብዙዎቹ አፋቸውን በአርጐብኛ እንደፈቱ እና አሁንም አፋቸውን በአርጐብኛ የሚፈቱ ህፃናት እንዳሉ ገልጸው፤ አዋሽ አካባቢ የሚገኙት ግን አፋቸውን የሚፈቱት አማርኛን ከአርጐብኛ ጋር በማቀላቀል እንደሆነ አስፍረዋል፡፡ አጠቃላይ በሆነ መልኩ የአርጐብኛ ቋንቋ አሁንም ብዛት ባላቸው ተወላጆች የሚነገር መሆኑንና አገልግሎቱም ሠፊ እንደሆነ በመግለጽ ጥናቱን አጠቃለዋል፡፡

ዐቢዩ (2000) “የአርጐባ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፤ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ፣ አርጐባ ልዩ ወረዳ” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍል ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዓላማ የአርጐባን ማኅበረሰብ ማንነት፣ ከቁሳዊ ባህሎቻቸው አንፃር ማጥናት ነው፡፡ አርጐቦች ምን ምን የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች እንዳሏቸው መመርመር፤ ቁሶቹ በማን፣ ከምንና እንዴት እንደሚሠሩ፣ መቼ፣ ለምንና እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ፤ ምን አይነት ቅርጽ ለምን ምክንያት እንደተቀረፀባቸው ማሳየት ሌላው የጥናቱ ዓላማ ነው፡፡

አጥኚው አስራ አንድ ቁሶችን በናሙናነት መርጠው ተንትነው አቅርበዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አምስቱ የቤት ውስጥ ቁሶች ሲሆኑ ፣ ስድስቱ ደግሞ የማጌጫ ቁሶች ናቸው፡፡ ቁሶችን በ“Schelereth” ዘጠኝ ሞዴሎች መሠረት ከአገልግሎት ሰጭነት፣ ከመዋቅራዊነት፣ ከተምሳሌትነት፣ ከባህላዊነት፣ ከአካባቢያዊነት፣ ከባህርይ አመላካችነት እና ከማኅበራዊነት ሞዴሎች አንፃር ተንትነው አቅርበዋል፡፡

የጥናታቸው ትኩረት በአርጐባ ማኅበረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች ላይ ይሁን እንጂ፣ እግረ መንገዳቸውን ስለ አርጐባ ማኅበረሰብ አመጣጥ፣ ስለባህላዊና ሐይማኖታዊ ስርዓቶች ዳስሰዋል፡፡

የነጋሽና የዐቢዩ ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር አንድነት ባይኖራቸውም የጥናቶቹ ክልል በአርጐባ ማኅበረሰብ ላይ መሆኑ ያመሳስላቸዋል፡፡ ስለ አርጐባ ማኅበረሰብ አመጣጥ፣ ባህልና ሐይማኖታዊ ስርዓቶችን በተወሰነ መልኩም ቢሆን መዳሰሳቸው ሌላው ተመሳስሏቸው ነው፡፡

### 3.2.2. በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ የተሠሩ ጥናቶች ቅኝት

ከሁሉም (2004) "የነገደ ወይጦ ማኅበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍል ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናቱ ትኩረት የነገደ ወይጦ ማኅበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ለማኅበረሰቡ አባላት ያላቸውን ማኅበራዊ ፋይዳ መመርመር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚነገሩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች አማካይነት የማኅበረሰቡ ስያሜ፣ አመጣጥ፣ የሥራ ባህልና አምልኮ እንዴት እንደተገለጹ ማሳየት፣ ማኅበረሰቡ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹንና ባህላዊ ስርዓቶቹን ለአዲሱ ትውልድ የሚያስተላልፍበት ምክንያት ምን እንደሆነ መመርመር፣ በባህላዊ ስርዓቶቹ የሚተላለፉ ጉዳዮችንና የማኅበረሰቡ አባላት በባህላዊ ስርዓቶቹ ላይ ያላቸውን አመለካከት መፈተሽ ሌላው የጥናቱ ትኩረት መሆኑን አስፍረዋል፡፡

አጥኚዋ አርባ ስምንት ተረኮችን አሰባስበው ተረኮቹ እንደሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ተመሳሳይነት በይዘት መድበዋቸዋል፡፡ ባህላዊ ስርዓቶችን ደግሞ የአቢናዝ፣ የግርዛትና የሠርግ በማለት  በሦስት ከፍለው አቅርበዋል፡፡ የማኅበረሰቡ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የማኅበረሰቡን ስያሜ፣ አመጣጥ፣ አምልኮ፣ የሥራ ባህል እና ድህነታቸውን አስመልክቶ የአካባቢው ማኅበረሰብ ለሚያደርስባቸው ተጽዕኖ ወይም መገለል ምላሽ የሚሰጡ፣ የማኅበረሰቡ አባላት በማንነታቸው እንዲኮሩ እና በራሳቸው ጸንተው እንዲኖሩ የሚያደርጉ ሆነው መገኘታቸውን ገልጸዋል፡፡

ከሁሉም የነገደ ወይጦ ባህላዊ ስርዓቶች አምልኮን፣ ግርዛትንና ሠርግን የተመለከቱ መሆናቸውንና በአምልኮው የማኅበረሰቡ ኑሮ የተመሰረተው ከውሀ ጋር በመሆኑ፣ በውሀው ላይ እንደማይሰምጡ ከውሀው ጅን ጋር ስምምነት መደረሱን በመንገር ያለፍርሀት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ እንደሚያደርግ እንዲሁም ከአቢናዝ ድጋፍ ይደረግልናል ብለው እንደሚያምኑ አመላክተዋል፡፡

የማኅበረሰቡ የግርዛት ስርዓት የሚፈፀመው ተገራዡ ልጅ ጀግና፣ አዳኝ፣ መከታ ወይም ደም መላሽ  ይሆናል ከሚል አስተሳሰብ እና የሠርግ ስርዓቱ ደግሞ በማኅበረሰቡ መካከል መረዳዳት ወይም መተጋገዝ ባህላቸው እንደሆነ በመግለጽ ጥናቱን አጠቃለዋል፡፡

ምንዳ (2000) "የጌዴኦ ልማዳዊ ስርዓቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናቱ ዓላማ በማኅበረሰቡ ልማዳዊ ስርዓትና ዝርው ቃላዊ ተረኮቻቸው ውስጥ ምን ምን ግንኙነቶች እንዳሉ መመርመር ነው፡፡ የዝርው ቃል ተረኮቹን ከማኅበራዊ ግልጋሎቶች አንፃር ይዘቶቻቸው በምን ላይ እንደሚያተኩሩ ማሳየት፣ የተረኮቹን ጕሳዊ ምደባና አካባቢያዊ ስያሜዎቻቸውን መለየት ሌላው የዚህ ጥናት ዓላማም እንደሆነ አስፍረዋል፡፡

ምንዳ የጌዴኦን ማኅበረሰብ ባህላዊ ስርዓቶች ቄጠላ (አምልኮታዊ ጭፈራ)፣ ፋጬ (ጥፋትን አምኖ መናዘዝ)፣ ጕንደሮ (ሥርዓተ-እርቅ) እንዲሁም የጋብቻና ጥንታዊ የሐዘን ሥርዓት ክዋኔዎችን በመዳሰስ አቅርበዋል፡፡ ዝርው ቃል ተረኮቹን ጢንጐ /xingo/ እና መማሳ /mammassa/ በማለት በሁለት ከፍለው አንድነትና ልዩነታቸውን አሳይተዋል፡፡ እነዚህ ተረኮች እያንዳንዳቸው በአወቃቀር፣ በአቀራረብ፣ በታዳሚዎች እድሜና በመቼት እንደሚለያዩ ገልጸዋል፡፡ ሽማግሌዎችና አዛውንቶች ለወጣቱ ትውልድ ልምዶቻቸውንና ገጠመኞቻቸውን በልዩ ልዩ ሥነ-ቃሎቻቸው አማካይነት የሚነግሩበት አማካይ ስፍራም "ሶንጐ" እንደሚባል አመላክተዋል፡፡ የጌዴኦ ዝርው ተረኮች ይዘታቸው ሲመረመር የኅብረተሰቡን ልማዳዊ ስርዓቶች (እሴቶች) ለማጠናከርና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ እንደሚያገለግሉ ጠቅሰዋል፡፡

አብርሃም (2000) "Jimma Oromo Oral Prose Narrative: A Preliminary Descriptive Analysis" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የጅማ ኦሮሞ ማኅበራዊና ባህላዊ አውዶችን መሰረት በማድረግ ተረቶችን መለየትና መግለጽ ነው፡፡ በጅማ ኦሮሞዎች ተቀባይነት ያላቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች የትኞቹ እንደሆኑ መለየት፣ ማኅበረሰቡ ተረቶችን እንዴት እንደሚመድቧቸው መመርመር፣ የተረቶቹን ውስጣዊ ባህርያት፣ አጀማመርና አጨራረሱን ለይቶ ማመላከትና ተረቶቹ የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች መለየት የጥናቱ ሌላው ዓላማ እንደሆነ አስፍረዋል፡፡

አጥኚው የጅማና የአካባቢውን ሥነ-ምህዳር፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ገጽታዎችን በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ ዝርው ተረኮች ቡና ሲፈላ፣ ገበያ ሲቆም፣ በሐዘን ቤትና በጫት ስርዓት ላይ በሠፊው እንደሚቀርቡ ገልጸዋል፡፡ ዝርው ቃላዊ ተረኮች የማኅበረሰቡን አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ችግር፣ ፍርሀት፣ ምኞትና ተስፋ ለመረዳት

እንደሚያግዙ አስረድተዋል፡፡ የጅማ ኦሮሞ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በሦስት በመመደብ አቅርበዋል፡፡ እነሱም "ታሪክ" (Seenaa /Taarika)፣ "ተረት" (Oduu duri)፣ እና "ቀልድ" (Qoosaa) ናቸው፡፡ እነዚህም ለምን፣ ለምን ጉዳይ እንደሚተረኩ ዘርዝረዋል፡፡ የተጠኝ ማኅበረሰብ አባላት ተረኮችን በስማቸው፣ በውስጣቸው ባለው ነባራዊ እውነታና ፈጠራ፣ እንዲሁም በትረካው ዓላማ እንደሚለይዋቸው በመግለጽ ጥናቱን አጠቃለዋል፡፡

ባይለየኝ (1999) "Anyuaa Oral Prose Narratives: Ethnic Genres and Social Functions" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት አድርገዋል፡፡ የአኝዋክ ማኅበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የባህል ባለቤቶቹን የአመዳደብ ስርዓት እንደ ዋና መከፋፈያ ዘዴ በመጠቀም መለየትና ተረኮቹ ያላቸውን የጋራ ማኅበራዊ ተግባር ማሳየት የጥናቱ ዋና ዓላማ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በአካባቢው ቀጣይ ጥናት ለሚያደርጉ አጥኝዎች መነሻ መስጠትም ሌላው የዚህ ጥናት ዓላማ እንደሆነ አስፍረዋል፡፡ አንድ መቶ አስራ ስምንት ቃላዊ ዝርው ተረኮችን አሰባስበው "እውነተኛ ታሪክ" (the leere)፣ "ተረቶች" (the wae) እና "ምሳሌያዊ ታሪኮች" (the angade) በማለት በሦስት ምድብ ከፍለው ማኅበራዊ ፋይዳቸውን አሳይተዋል፡፡ "እውነተኛ ታሪክ" (the leere) ስለሞቱ ጀግኖች፣ ስለታሪካዊ ክንውኖችና ስለመሳሰሉት ይተርካል፡፡ ወጣቶችን እያዝናኑ ለማስተማሪያነት ያገለግላል፡፡ "ተረቶች" (the wae) ልዩ ልዩ የሰው ባህሪያትን የሚያሳዩ ሆነው በቀልድና በማዝናናት የተሞሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ተረኮች ታሪክን ለመመዝገብ፣ የሞቱ ጀግኖችን በማስታወሳቸው የባህል ማንፀባረቂያ ተደርገው ይታያሉ፡፡ "ምሳሌያዊ ታሪኮች" (the angade) ያለፉ ሁነቶችን፣ የእምነት ስርዓቶችን፣ ማኅበረሰቡ ስለአለም ያላቸውን አመለካከትና አስተሳሰብ እንደሚያሳዩ አስፍረዋል፡፡

ማንያለው (1999) "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማኅበራዊ ፋይዳቸው" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ትኩረት በቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማኅበራዊ ፋይዳ ላይ ገላጭ ትንተና ማድረግ ነው፡፡ የቤንች ማኅበረሰብ አባላት የቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች ናቸው ብለው የሚጠቅሷቸውን ለይቶ መግለጽ የጥናቱ ሌላው ዓላማ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡ ከመስክ የሰበሰቧቸውን ዘጠና ሰባት ተረኮች ተጠቅመው የቤንች ዝርው ተረኮችን ከክወና አውዳቸው፣ ከፈጠራነታቸው፣ ከታሪኩ እውነተኛነትና ከትረካው ግብ ዓላማ አንፃር "ቤንችቶስ" እና "ኤሸሽ" ተብለው እንደሚከፈሉ ያስረዳሉ፡፡ "ቤንችቶስ" የሚተረከው በቀን ሆኖ በአካባቢው የተነሱትን

ቃላዊ (ታሪካዊ) ሰዎችን የሚመለከቱ አፈ.ታሪኮችና የማኅበረሰቡን ባህላዊ እምነት፣ የአምልኮ ስርዓትና አሰራሮችን የሚመለከት ሲሆን፣ "ኤሽሽ" ደግሞ ተረኩ የፈጠራ ሆኖ ክወናውም በምሽት ጊዜ በአዋቂዎች አማካይነት ለሕፃናት የሚቀርብ እንደሆነ በመግለጽ ጥናቱን አጠቃለዋል፡፡

አማረ (1999) "የሽካቾ ብሄረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍል ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት አድረገዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የሸክቾን ሀገረሰባዊ ተረቶችን በመሰብሰብ መድቦ ከአከዋወን ስልትና ከይዘት አንፃር መተንተን ነው፡፡ ተረቶቹን ሰንዶ ለመጭው ትውልድ ቅርስ ማቆየት ሌላው የጥናቱ ዓላማ ነው፡፡

አጥኚው ሰባ አራት ያህል ተረቶችን ሰብስበው አካባቢ.ያዊ ምደባን ተከትለው የሸካቾ ተረቶች "ኬሞ" እና "ኤንጌሞ" ተብለው እንደሚመደቡ አስረድተዋል፡፡ "ኬሞ" አፈ. ታሪክ ሊባሉ የሚችሉ ይዘቶች ያላቸው ተረቶች እንደሆኑ ገልጸው፣ "ኤንጌሞ" ደግሞ ልዩ ልዩ ማኅበራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን የሚያመላክቱ ይዘቶች እንዳሉት አስፍረዋል። "ኤንጌሞ" በአንዳንድ ተመራማሪዎች ዘንድ "ፋቡላ" የሚባሉት አይነት እንደሆኑም ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም እንደ ሥነ-ቃል ተመራማሪዎች አከፋፈል የሸክቾ ማኅበረሰብ ተረቶች አፈ. ታሪክ (legend)፣ ገላጭ (explanatory) እና ፋቡላ (fable) እንደሆኑ አመልክተዋል።

አማረ ተረቶቹ ከይዘት አንፃር ብልህነትን፣ መጥፎ ባህሪያትን፣ ፍትሀዊነትን፣ ጓደኝነትን፣ ትዕግስትን እና ጣውንትነትን እንደሚያሳዩ አስፍረዋል፡፡

ለማ (1999) "በየም ብሔረሰብ ፆታ ተኮር ተረኮች የወንድና የሴት ምስል ትንተና" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍል ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ትኩረት በየም ወረዳ የሚተረኩ ተረቶችን በመሰብሰብ በተረቶቹ ውስጥ ወንዶችና ሴቶች እንዴት እንደተገለፁ መተንተን ነው፡፡ አንድ መቶ አራት ተረቶችን ሰብስበው ፆታዊ ስዕል ጐልቶ የሚታይባቸውን ስልሳ ስድስት ተረቶችን በመምረጥ ተንትነው አቅርበዋል፡፡ ከመስክ የሰበሰቧቸውን ስልሳ ስድስት ተረቶችን ተጠቅመው በአካባቢው አጠራር "ቶቾ" እና "ኤሻ" ተብለው እንደሚከፈሉ ገልጸዋል፡፡ "ቶቾ" እውነት ናቸው ተብለው

የሚታመንባቸው ታሪኮች የሚተረቱባቸው ሲሆኑ፣ "ኤሻ" ደግሞ ፈጠራ ተብለው የሚታመንባቸውና በአብዛኛው ለተዝናኖት የሚተረኩ ተረቶች እንደሆኑ አመላክተዋል፡፡

"ቶቾ" በምሁራኑ የተረት መመደቢያ ስልት መሠረት ታሪካዊ አፈ ታሪክ፣ ሚታዊ አፈ ታሪክና ገላጭ ተረቶች በሚል በሶስት ምድቦች ሊከፈል እንደሚችልና "ኤሻ" ግን ንዑስ ምድቦች እንደሌሉት አስፍረዋል፡፡

ለማ በማኅበረሰቡ ተረቶች ውስጥ ሁለቱም ፆታዎች በአሉታዊና በአዎንታዊ ገጽታ የተሳሉ ናቸው፡፡ በአፈ ታሪክና ገላጭ በሆኑ ተረቶች ውስጥ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች የጐደፉና የበታች ተደርገው መሳላቸውን አስፍረዋል፡፡ ይህን አመለካከት ለማስረጽ እምነትን ከለላ ያደረጉ ተረቶች መኖራቸውን አመልክተዋል፡፡ በማኅበረሰቡ ውስጥ በሥነ-ፆታ ላይ የሚሠሩ ማህበራትና ድርጅቶች በሴቶች ላይ ጫና የሚያሳድሩ ተረቶችን በመለየት ሐይማኖታዊ መሠረት እንደሌላቸው በማጋለጥ በሴቶች ላይ የሚፈጠረውን ጫና በመቀነስ እኩልነትን ለማምጣት ለሚደረገው ጥረት ጉልህ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ በመግለጽ ጥናቱን አጠናቀዋል፡፡

ሳህሉ (1996) ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት "Borana Oromo Prose Narratives: A Contextual Study" በሚል ርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የአጥኚው የጥናት ትኩረት ተረቶችን ከክዋኔ አውድ አንፃር መመርመር ነው፡፡ ተረቶቹ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙበትን ሁኔታ በመግለጽ አይነታቸውን (ethnic genres) ማመላከት እንደሆነ አስፍረዋል፡፡ ሰባ አራት ተረቶች በማሰባሰብ በሶስት ከፍለው "ዱሪ ዱሪ" (የልጆች ተረቶች)፣ "ማማክሳ" (የጐልማሶች ተረቶች) እና "አርጋጌቲ" (Myths and Legend) በማለት ተንትነው አቅርበዋል፡፡ የልጆች ተረቶች "ከብዙ ጊዜ በፊት ነው አሉ" በሚል ሐረግ የሚጀምሩ ናቸው፡፡ የጐልማሶች ተረቶች የኅብረተሰቡን እምነትና እሴቶች የያዙ ሲሆኑ፣ የማኅበረሰቡን ጥበቦች፣ ህጐችና ማኅበራዊ እውነታዎች እንደሚያስገነዝቡ አስረድተዋል፡፡ ሚቶችና አፈታሪኮች ደግሞ የኅብረተሰቡን ታሪክና ባህል የያዙ እንደሆኑ አሳይተዋል፡፡

በጥናቱ ማጠቃለያ ላይ ተረቶች እንደዊልያም ባስኮም አመዳደብ በሚት፣ በአፈታሪክና በህገረሰብ ተረቶች መክፈል ሲቻል፣ እንደ ኦክፔሁ አከፋፈል ደግሞ የልጆች ተረቶች፣ የጐልማሶች ተረቶችና በከፊል ፌብል (Fable) በማለት እንደሚመደቡ ገልጸዋል፡፡ ሚቶችና አፈታሪኮች ደግሞ ታሪካዊ አፈታሪኮችና ሮማንቲክ አፈታሪኮች በሚለው ሊካተቱ እንደሚችሉ አመላክተዋል፡፡

**ይሄነው** (1996) "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት በምዕራብ ጐጃም የሚገኙ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን መሰብሰብና መመደብ ነው፡፡ የአመዳደብ ስልታቸው ተረኮች ሲተረኩ ያለውን የክዋኔ ሁኔታ፣ ሰዎች ለተረኮች ያላቸውን አመለካከት፣ የተረኩን ዓላማ፣ የተረኩን ርዕሰ ጉዳይ፣ ጭብጥ፣ መዋቅር፣ የአተራረክ ዘዴና የገፀባህሪያቱን አሳሳል መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ተረኮችን ለመመደብ ወጥ የሆነ የመመደቢያ ዘዴ እንደሌለ ገልጸው፣ ያሰባሰቧቸውን አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት ተረኮችን በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች መድበው አቅርበዋል፡፡ እነሱም ሀገረሰባዊ ተረቶች(Folktales)፣ አፈ-ታሪኮች (Legends) እና ዘር ቆጠራዎች (genealogy) ናቸው፡፡ ሀገረሰብ ተረቶች በማንኛውም የዕድሜ ክልል በሚገኙ የማኅበረሰቡ አባላት ዘንድ ሲነገሩ፣ አፈ-ታሪኮችና ዘር ቆጠራዎች ደግሞ ብዙ ጊዜ በእድሜ ትልልቅ በሆኑ የማኅበረሰቡ አባላት የሚነገሩ ሲሆን፣ እንደ እውነተኛም ታሪክ እንደሚቆጠሩ አስፍረዋል፡፡ ሀገረሰብ ተረቶች የመክፈቻና የመዝጊያ ፎርሙላ እንዳላቸው በማመላከት ጥናቱን አጠቃለዋል፡፡

**መላክነህ** (1990) ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናቱ ትኩረት የደቡባዊ አገውን ሀገረሰባዊ ተረቶች በመሰብሰብ ማህበረ-ባህላዊ ጠቀሜታቸውን በጭብጥ ላይ በመመስረት ትንተና ማድረግ ነበር፡፡ የጥናቱ ዓላማም የደቡባዊ አጋው ሀገረሰብ ተረቶች ያላቸውን ስነጽሁፋዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ መመርመር፣ ተረቶቹ ለማኅበረሰቡ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ አካባቢ ያላቸውን ጠቀሜታ መመርመር እና የህዝቡን ሥነ-ልቡናዊና ሥነምግባራዊ አመለካከት ማመላከት ነው፡፡

አጥኚው በማኅበረሰቡ የሚነገሩ ስልሳ የደቡባዊ አገው ሀገረሰብ ተረቶችን ተንትነው ዋና ዋና የሚሏቸውን ጭብጦች በሁለት ክፍሎች በመመደብ ተንትነው አቅርበዋል፡፡ የመባያ ጉዳዮችን ደግሞ ብልህነት፣ ቂልነት፣.... በማለት በአስራ ሁለት ምድብ ክፍለው አስፍረዋል፡፡ መላክነህ ተረቶችን የመክፈል ሥራ አስቸጋሪ እንደሆነ አሳይተዋል፡፡ ማኅበረሰቡ ያለውን መልካም እሴት ለወጣቶቹን በማስተማር ረገድ ተረቶቹ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው በማመላከት ጥናቱን አጠናቀዋል፡፡

**ተስፋዬ** (1990) "A Study of Major Themes in Jabalwi Folktales" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ትምህርት ክፍል

ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አቅርበዋል፡፡ ጥናቱ የተረቶችን ማኅበረሰቡ በመተንተን ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የሀገረሰብ ተረቶችን አሳባስቦ የማኅበረሰቡን እምነት፣ ማኅበራዊ እሴት እና ለአለም ያላቸውን አመለካከት ማሳየት ላይ አነጣጥረዋል፡፡

ተስፋዬ ሰባ ሁለት ተረቶችን አሰባስበው በሃያ አምስት ጭብጦች መድበዋቸዋል፡፡ ጭብጦችም የነገሮች አመጣጥ፣ መጥፎ ምግባራትና ድክመቶች፣ ሰይጣናዊና መናፍስታዊ በማለት መድበው አቅርበዋል፡፡ በሥራቸውም ብቀላ፣ ቅናት፣ ስስታምነት፣ ምቀኝነት፣ ሞኝነት፣ ደደብነት፣ ስንፍና፣ ትዕግስት፣ ጨካኝነት፣ ኃይማኖት፣ ፍርሀት፣ ታማኝነት፣ አንድነት፣ ፍትህ እና እውነት በሚሉ ርዕሶች በመተንተን ጥናቱን አጠቃለዋል፡፡

አብዱልቃድር (1982) "Some Cultural Elements as Reflected in Somali Folktales" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት አድርገዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በተረቶቹ ላይ ተመስርቶ የሶማሌን ማኅበረሰብ ባህላዊና ሥነ-ልቡናዊ ገጽታዎችን መተንተን ነው፡፡

አብዱልቃድር ሰማንያ ሁለት ተረቶችን አሰባስበው ያላቸውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ በስምንት ክፍል መድበው ተንትነዋል፡፡ የተረቶቹ ይዘትም ብልህነትን (ጥበበኝነትን)፣ ፍትህን፣ ኃይማኖትንና ሥነ-ምግባርን፣ ጋብቻን፣ ሴቶችንና ቅናትን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ጥናቱ የሱማሌ ህዝብን ቋንቋ፣ ባህል፣ ኢኮኖሚንና ስነ-ምህዳርን የተመለከቱ መገለጫዎችን አካቷል፡፡

አጥኚው ለጥናቱ በተመረጡት ተረቶች አማካይነት የሶማሌን ማኅበረሰብ ባህላዊና ሥነ-ልቡናዊ ገጽታዎች ለማሳየት ጥረት አድርገዋል፡፡ በትንታኔው በእያንዳንዱ ምድብ ላይ የደረሱባቸውን ግኝቶች በማቅረብ ጥናቱን አጠቃለዋል፡፡

ከላይ ለመቃኘት የተሞከሩ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር አንድነት ባይኖራቸውም በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይነት አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ ጥናቶቹ በቃላዊ ዝርው ተረክ ዙሪያ መሰራታቸው አንዱ የሚያመሳስላቸው ጉዳይ ሲሆን የከሁሉም፣ የመላክነህ ፣የተስፋዬና የአብዱልቃድር ጥናቶች በተረኮች ይዘት ላይ ተመስርተው ለማኅበረሰቡ በሚሰጡት ፋይዳ ላይ ትኩረት ማድረጋቸው ሌላው ተመሳስሏቸው ነው፡፡ ይህ ጥናት የአርጐባ

ማኅበረሰብ ተወላጆች የሚናገሯቸው ተረኮች ማንነታቸውን ለመገንባት ያላቸውን ፋይዳ መመርመር በመሆኑ ከምንዳ፣ ከአብርሃም፣ ከባይለየኝ፣ ከማንያለው፣ ከአማረ፣ ከለማ፣ ከሳህሉ እና ከይሄነው ጥናቶች ጋር መጠነኛ የሆነ ዝምድና አለው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጥናቶች በተለያዩ ማኅበረሰቦች ተረኮች ላይ በማተኮር ተረኮቹን በአይነትና በአውዳዊ አገባባቸው በመመደብ ያጠኑ በመሆናቸው ከእኔ ጥናት ጋር ይለያሉ፡፡ በተጨማሪም የአጠናንና የአቀራረብ ስልታችን አንድ አይደለም።

# ክፍል አራት

## 4. ከአርጐባ ማኅበረሰብ ማንነት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ትንተና

ይህ ክፍል በአርጐባ ማኅበረሰብ ማንነት ዙሪያ የተሰበሰቡት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ይዘትና አንድምታ የሚብራራበት የትንተና ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም የማኅበረሰቡ አባላት በሚናገሯቸው ተረኮች ላይ ትኩረት በማድረግ ተረኮቹ ማንነታቸውን ለመገንባት ያላቸውን ፋይዳ ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ ለትንተናው የመረጃ ግብኣት የሆኑት የቃል ተረኮች የተሰበሰቡት የአርጐባ ማኅበረሰብ ዋነኛ የመኖሪያ አካባቢ በሆኑት በደቡብ ወሎ አስተዳደር ዞን በአርጐባ ልዩ ወረዳ መዲና፣ በሰሜን ሸዋ አስተዳደር ዞን አንኮበር፣ አልዩ አምባና ሸዋ ሮቢት ከተማ አካባቢ፣ በኦሮሞ ዞን በደዌ ጨፋ ወረዳ በከሚሴ ከተማ እና በሾንኬ መንደር ከሚኖሩ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ነው፡፡

የዚሁ ክፍል የትንተና አቀራረብ በሦስት ዋና ዋና ንዑሳን ክፍሎች ተዋቅሮ ከማህበረሰቡ የኋላ ታሪክና ከአኗኗር ዘይቤ አኳያ ተቃኝቷል፡፡ እያንዳንዱ ንዑስ ክፍል በየፈርጁ ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን፣ የመረጃ ምንጮቹ ተደጋጋፊና ተፃራሪ(የተራራቀ) መረጃዎች መስጠታቸው ግምት ውስጥ ገብቶ የሁሉንም መረጃ በማስተናገድ ሚዛን የሚደፋውን ከተጨማሪ የመረጃ ምንጮች ጋር ለማገናዘብም ተሞክሯል፡፡ በአጠቃላይ የተጠቀሱትን ርዕሰ ጉዳዮች መሠረት ያደረጉት የቃል ተረኮች በተለያዩ ማንፀሪያዎች አማካይነት ተተንትነው ነው የቀረቡት፡፡

### 4.1. ከአርጐባ ስያሜ፣ አመጣጥ፣ ከትውልድ ሐረግ እና ከሕዝቡ አሰፋፈር ጋር የሚገናኙ ተረኮች

#### 4.1.1. ከአርጐባ ስያሜ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች

የማኅረሰቡ መጠሪያ የሆነውን አርጐባ የሚለውን ቃል ጥንተ አመጣጥ አስመልክቶ የማኅበረሰቡ ተወላጆች የተለያዩ ተረኮችን ያቀርባሉ፡፡ ከሚነገሩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች መካከል አንዱ መነሻቸው ሳዑዲ አረቢያ ሆኖ ቁረይሽ በተባለው የራሳቸው ጐሳ ጠረኞች ከደረሰባቸው ጥቃት ለማምለጥ በነብዩ መሀመድ ትዕዛዝ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የነብዩ ተከታዮች (ባለቤታቸውን፣ ልጃቸውን ሩቅያንና ባለቤቷን፣ እንዲሁም የአጐቷን ልጅ ጨምሮ በርካታ ስደተኞች) በነባሩ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ "አረብ ገባ"

የሚል ስያሜ እንደተሰጣቸው የሚገልፀው ነው፡፡ አረብ ገባ የሚለው ሐረግም በጊዜ ሂደት አርጐባ ወደሚለው ስያሜ ተለወጠ ይላሉ (ሐጅ መሀመድ፣ ሸንኬ፣ ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓ.ም.፤ ወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድና ወላስማ ሐጅ ኑርሁሴን መሀመድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 እና 16 ቀን 2005 ዓ.ም.)፡፡ ይህን የቃል ተረክ ብዙዎቹ የማኅበረሰቡ ተወላጆችም ይጋሩታል፡፡ ይህንን የመጠሪያ ስያሜ አመጣጥ ተረክ የሚቀበሉት አሚኑ ኢድሪስ ደግሞ በ7ኛው ክፍለ ዘመን ከአረብ አገር በስደት ወደ ኢትዮጵያ ለመጡ ስደተኞች የተሰጣቸው ስያሜ እንደሆነ ይገልፃሉ (ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም.)።

አክሊሉ "አርጐባ" ማለት "አረብ-ገባ" መሆኑን አስፍረዋል፡፡ አንዳንዶቹ ግን ትንሽ ለወጥ አድርገው "ሀር-ጐባ" የሚሉ ሲሆን፣ ትርጉሙም በተራራ ላይ የሚታይ ሀር ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ይህን ስያሜ ያገኘው የመጀመሪያዎቹ አረቦች ሲመጡ ጉባ /ተራራ/ ላይ የሀር ድንኳን ስለተከሉ ነበር (1991፣ 4) ይላሉ፡፡ እንደ አህመዲን ጀበል ገለፃ የተለያዩ የአረብ ጐሳዎች ወደ ሀበሻ (ኢትዮጵያ) በተለያዩ ጊዜያት መጥተዋል፡፡ አረቦች ወደ ሀበሻ ሲገቡ "አረብ ገባ" እንደተባሉና ከጊዜ በኋላ "አርጐባ" የሚል መጠሪያ እንዳገኙ ጽፈዋል (2003፣ 80)፡፡ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች በዘውዳዊው ስርዓት ዘመን በባዕድነት ተፈርጀው አረብ-ገባ (አርጐባ) የሚለው መለያ ስያሜ እንደተሰጣቸውና ዛሬ አረብ ገባ (አርጐባ) የሚለው ስያሜ የህዝቡና የቋንቋው መጠሪያ ሆኖ እያገለገለ እንደሚገኝ አህመድ (1999፣ 11) ያስረዳሉ፡፡

ተረኩ አንድ አነስተኛ ቡድን ፈልሶ ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን ታሪካዊ አጋጣሚ ሊያመለክት ይችላል እንጂ፣ ስለ ማኅበረሰቡ ታሪካዊ የዘር ሐረግ አመጣጥ ሊጠቀስ የሚችል ማረጋገጫ ሆኖ የሚቀርብ አይመስልም፡፡ ምናልባትም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው እነዚሁ የነብዩ መሀመድ ተከታይ ስደተኞች ከነባሩ የአገሪቱ ኅብረተሰብ ጋር ሲዋሀዱና ሲበተኑ ተውጠው ይቀራሉ እንጂ አንድ ትልቅ ማኅበረሰብ ላይፈጥሩ ይችላሉ ብሎ ለመገመት ያስደፍራል፡፡ በሌላ በኩል የአርጐባ ሕዝብ ከዚያ የታሪክ ክስተት በፊትም ሳይኖሩ እንዳልቀሩ የሚገምቱ መረጃ ሰጪዎች ስላሉ የማኅበረሰቡን ስያሜ ከአረብ አገር ከመጡ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ጋር ማያያዛቸው ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡

እዚህ ላይ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የትውልድ ሐረጋቸውን ከአረቡ ዓለም ጋር ማስተሳሰራቸው ምን ፋይዳ ያስገኝላቸዋል? የሚል ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

እነዚህ ወገኖች መገኛ መሠረታቸውን ከአረቢያ ምድር ሲያደርጉ አረቦች ስለሆንን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን እንለያለን ማለታቸው ነው፡፡ ከዚህ ከፍ ሲል የአረብ ምድር ነብዩ መሀመድን ጨምሮ በርካታ ነብያትና ቅዱሳን የፈለቁበት (መሀመድ፣ 1982፣ 22-23)፡፡ እንደመሆኑ በእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ያለውን ተወዳጅነት ከማንነታቸው ጋር አቆራኝተው "የእኛ ነው" የሚል ስሜት ያሰርጹበታል ማለት ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም "እኛ አረብ ነን" ሲሉ፣ ከነብያትና ከቅዱሳን አገር የመጣን ነን ወይም የቅዱሳን የስጋ ዘመዶች ነን የሚል አንድምታ ስለሚፈጥር "የእኛ ዘር የተለየ ነው" በማለት ሥነ-ልቡናቸውን ለመገንባት ያስችላቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ስያሜው አርጎባ ሳይሆን ኸርጎባ እንደሚባልም የሚናገሩ የማኅበረሰቡ ተወላጆች አሉ፡፡ የአርጐብኛውን ጥምር ቃል መነሻ በማድረግ በሚመሰርተው ትርጉማቸው እንደሚያስረዱት ኸር ማለት ሀር ወይም ደማቅ ቀለም ያለው ጠንካራ ክር ሲሆን፣ ጐባ ማለት ደግሞ መቀመጥ (ተቀማጭ) ማለት ነው፡፡ ኸርጐባ ማለት በሀር ላይ የሚቀመጡ (ከሀር የተሰራ ልብስ የሚለብሱ) ሰዎች እንደማለት ነው ይላሉ፡፡ ስያሜውን ከባህላዊ አለባበሳቸውና ከአኗኗራቸው ወስደው ሌሎች ማኅበረሰቦች የሰጧቸው ስም እንደሆነ (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም. ፤ አብዱልሰላም፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም) ያስረዳሉ፡፡

በ13ኛው ክፍለ ዘመን ከሸዋ ተነስቶ ወደ ኤደን ባሕረሰላጤና ሕንድ ውቅያኖስ ተዘርግቶ የነበረው ዋነኛው የንግድ መስመር በሸዋ ሙስሊሞች (ይፋቶች) እጅ ተይዞ እንደነበር (Taddsse; 1984፣ 9) ያስረዳሉ። ይህ ደግሞ ከዘርፉ በሚገኝ ጥቅም የተሻለ የአኗኗር ሁኔታን እንዲከተሉ በማድረግ ምናልባትም ሀር እስከመልበስ የሚያደርስ ዕድል እንደፈጠረላቸው መገመት ይቻላል፡፡ የማኅበረሰቡ አባላት ቀደም ሲል የነበራቸውን አኗኗር መሰረት አድርገው በጣም ውድ ከሆነው ሀር የሚዘጋጀውን ልብስ ይለብሱ እንደነበር መተረክ፣ መናገራቸው በወጣቱ ትውልድ ላይ የሚያሳድረው አወንታዊ ተጽዕኖ ይኖራል፡፡ የቅድመ አያቶቻቸው የሀር ልብስ መልበስ የታሪክ ውርስ ሆኖ ለዚህ ትውልድ የማንነት ታሪክ መደርጀት አስተዋጽኦ ማበርከቱ አይቀርም፡፡ "እንዲህ ነበርን" ወይም "የእኛ ቅድመ አያቶች ከሀር የተዘጋጀ ልብስ" ይለብሱ ነበር የሚል መልእክት ያስተላልፋል፡፡ ከዚህም በመነሳት ቅድመ አያቶቻቸው ከሌሎች የተሻሉ ነበሩ የሚል ሀሳብ ለማስተላለፍ እንደተፈለገ መገመት ይቻላል፡፡

በዚሁ የማኀበረሰቡ ስያሜ አመጣጥ ዙሪያ ከላይ ከተገለጹት ለየት ባለ መልኩ የሚተርኩ የማኀበረሰቡ አባላትም ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች አርጎቦች የመጡት ከየመን ነው ብለው ያምናሉ፡፡ የመን ውስጥ የእርስ በርስ ግጭት ሲነሳ የተሸነፈው ወገን አባላት ወደ ኢትዮጵያ ሸሽተው ይመጡ ነበር፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገሮች በተሻለ ለየመን ቅርብ ስለሆነች ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት በወቅቱ የክርስትናን ኃይማኖት ይከተል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ስደተኞችን ተቀብሎ በአገሩ እንዲኖሩ ፈቅዶላቸዋል፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ ክርስቲያኖች አማራ ተብለው ሲጠሩ ከየመን በስደት የመጡት የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ደግሞ አርጎባ መባላቸውን (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም) ያስረዳሉ፡፡

አርጎባ የሚለው ስያሜ የማኀበረሰቡ መጠሪያ ብቻ ሳይሆን የመሬቱና ቋንቋውም መታወቂያ ሆኗል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የአርጎባ ልዩ ወረዳ ከተማ በመሆን "መዲና" በመባል የምትጠራው ከተማ ሳትቀር በአካባቢው በሚኖሩ ማኀበረሰቦች ዘንድ አርጎባ በመባል ትታወቃለች፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አርጎባ ከኃይማኖት ጋር ተያይዞም ይነሳል፡፡ በይፋት ውስጥ የሚገኙ የክርስትና ኃይማኖት ተከታዮች አማራ ሲባሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች ደግሞ አርጎባ እንደሚባሉ (ሼህ አረቡ፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 8 ቀን 2004 ዓ.ም) ይገልፃሉ፡፡

አለቃ ታየ (1964፣ 68) በይፋት ወስጥ የሚኖሩ አርጎቦችን "ነገደ እስላም" ሲሏቸው አክሊሉ ደግሞ አርጎቦች ታሪካቸውን ከእስልምና ኃይማኖት ጋር አንድ አድርገው እንደሚያቀርቡ (1991፣ 4) ይገልፃሉ፡፡ በዚህ መሠረት መልክዓ ምድራዊ ወሰኑ ሠፊ አይሁን እንጂ እስልምናና አርጎባ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

በአጠቃላይ አርጎባ ለሚለው ስያሜ መነሻ ተደርጎ በማኀበረሰቡ አባላት ዘንድ የሚተረከው ከነብዩ መሀመድ ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ጋር በተያያዘ አርጎባ የሚለው ቃል "አረብ- ገባ" ከሚለው ሐረግ በጊዜ ሂደት ተሻሽሎ የተገኘ ስለመሆኑ አብዛኞቹ የማኀበረሰቡ ተወላጆች የሚስማሙበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አርጎባ የሚለው ቃል ከስፍራው፣ ከቋንቋው እና ከእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች መጠሪያ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ከተረኮቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እነዚህ ተረኮች ከአርጎባ ማኀበረሰብ ማንነት ጋር የተቆራኙ ከመሆናቸውም በላይ ከውጭ አገር የመጡ ባዕዳን እንደሆኑ የሚነገረውን ተገን በማድረግ የዘራቸውን ምርጥነት እየገለጹ የማኀበረሰቡን ሥነ-ልቡና በመገንባት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

### 4.1.2. ከአርጐባ አመጣጥና የትውልድ ሐረግ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች

የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ከየት መጡ? መቼ መጡ? እንዴት መጡ? ለምን መጡ? የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሱ የማኅበረሰቡ ተወላጆች የተለያዩ ተረኮችን ይተርካሉ፡፡ አብዛኛዎቹ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ግን ቅድመ አያቶቻቸው ከእስልምና መመስረት ጋር በተያያዘ ወደ ሀበሻ(ኢትዮጵያ) መግባታቸውን ይተርካሉ፡፡ ነብዩ መሀመድ እ.ኤ.አ. በ610 ነብይነትን ከፈጣሪ ተቀብለው በመካ የሚገኘው ህዝብ የእስልምናን ኃይማኖት እንዲከተል ጥሪ ማድረግ ጀመሩ፡፡ ጥሪውን መስማት ያልፈለጉት የመካ ቁረይሾች በሙስሊሞች ላይ የቅጣት በትራቸውን ያሳርፉባቸው ነበር፡፡ ነብዩ መሀመድም ቁረይሾች ከሚያደርሱባቸው ግፍና መከራ ተከታዮቻቸውን ለመታደግ ሲሉ ወደ ሀበሻ ምድር እንዲሰደዱ መከሯቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውን መረጃ አቀባዮቹ ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ፣ ሼህ መሀመድ ያሲን እና ሐጅ ኡመር መሀመድ ጠቁመው ዘርዘር በማድረግም የሚከተለውን አጫውተውኛል፤

> ነብዩ መሀመድ የእስልምናን ኃይማኖት ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ ሲመሰርቱ ቁረይሾች ነብያችንንና ተከታዮቻቸውን ያሳድዷቸው ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ ነብዩ መሀመድ በኢትዮጵያ ውስጥ እውነተኛ መሪ እንዳለ ያውቁ ነበርና ቤተሰቦቻቸውንና ተከታዮቻቸውን "ወደ ሀበሻ ሀገር ሂዱ" አሏቸው፡፡ ይህንን የሰሙ ቁረይሾች እስልምና ወደ ሌሎች አገሮች ከተዛመተ ሠፊ የሆነ ድጋፍና ተቀባይነት ያገኛል ብለው ሠጉ፡፡ በዚህ ምክንያት ገፀ በረከት በመያዝ በፈረስና በግመል ፈጥነው ወደ ሀበሻ መንግሥት መጡ፡፡ ከንጉሱ ነጃሺ /ነጋሲ/ ፊት ቀርበው እጅ በመንሳትም ያመጡትን ወርቅና የከበሩ ድንጋዮች በማቅረብ "እንዲህ አይነት ስደተኞች ወደ እናንተ አገር መጥተዋል፡፡ ሐይማኖታችሁን የሚያረክሱ ቤተ-ክርስቲያኖቻችሁንና ጽላቶቻችሁን የሚያዋርዱ ናቸው፤ እንዳትቀበሏቸው" በማለት ለነጃሺ ገለጹላቸው፡፡ ነጃሺም በወንጌል ያምኑ ነበር፡፡ ወንጌል ላይ ደግሞ መሀመድ የሚባል ነብይ በመጨረሻ እንደሚመጣ ስለሚገልጽ ጊዜውን ሲጠብቁ ቆይተዋል፡፡ በዚህን ጊዜ "ስደተኞችን እስኪ ጥሯቸው፤ እናነጋግራቸው" አሉ፡፡ ቀድመው የገቡት ቁረይሾች ግን "ኧረ እባክዎን እርስዎ ፊት የሚቀርቡ አይደሉም፡፡ በጣም የተጠሉ፣ ወራዳና ድሆች ናቸው፡፡ በእኛ አካባቢ እንደ ሰው የሚቆጠሩ ስላልሆኑ አይቅረቡ፤ ከፊትዎ ቢቀርቡ እንኳን እጅ አይነሱም፡፡ ለባለስልጣን ሆነ ለታቦቶች አይሰግዱም፤ አያመልኩም፤ ግትሮች ናቸው" አሏቸው፡፡
>
> እርሳቸው ግን "ይግቡና ምን እንደሆኑ እንያቸው" በማለት ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ስደተኞችም ከንጉሱ ፊት በመቅረብ ነብዩ መሀመድ የፃፉላቸውን ደብዳቤ ሰጧቸው፡፡ ነጃሺም ደብዳቤውን አነበቡና "ለመሆኑ ነብይ ለምትሉት እንደ ወንጌል ከፈጣሪ የወረደለት መጽሐፍ አለው ወይ?" በማለት ጠየቋቸው፡፡ የቡድኑ መሪ የነበረው ጃዕፈር ከፈጣሪ ለነብዩ መሀመድ የወረደላቸው መጽሐፍ እንዳላቸው ገልጾ ቁርዓን ቀራላቸው (አነበበላቸው)፡፡ በዚህን ጊዜ ንጉሱ ከአይናቸው ደም እስኪፈስ ድረስ ስቅስቅ ብለው

አለቀሱ፡፡ "ይህ ኢንጅልና ወንጌል ከአንድ ማንቆርቆሪያ (በራድ) የተቀዱ ናቸው፣ ምንም አይነት ለውጥ የላቸውም" አሉ፡፡ ከዚያም "ቁረይሾችን ያመጣችሁትን ገፀ-በረከት በመያዝ ወደ መጣችሁበት ተመለሱ" አሏቸው፡፡ "እናንተ ስደተኞች ግን ተቀብያችኋለሁና በአገሬ ላይ በፈለጋችሁበት ቦታ መኖር ትችላላችሁ" አሏቸው፡፡ በዚህ መልኩ የመጡት አረብ ገቦች የእስልምናን ኃይማኖት እያስተማሩ አሁን ያለንበት ደረጃ ደረሱ፡፡ የአርጐቦች አመጣጥ ይህን ይመስላል፡፡ (ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም፤ ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም፤ ወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)፡፡

ከቃል ተረኩ እንደምንረዳው አብዛኛዎቹ የማኅበረሰቡ ተወላጆች ከእስልምና ኃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ጋር አያይዘው ስለሚተርኩ የማኅበረሰቡ አባላትም አረብ ነን ብለው ያምናሉ፡፡ ዝርያቸውንም ከቁረይሽ ጐሳ ከነብዩ መሀመድ ጋር ያቆራኙታል፡፡ ይህም አርጐቦች እና ቁረይሾች አንድ የትውልድ ሐረግ እንዳላቸው የሚገልጽ የማንነት ተረክ ነው፡፡

አርጐቦች ስለአመጣጣቸው ሲተርኩ ከእስልምና ኃይማኖት መግባት ጋር ስለሚያያይዙት አንዱን ከሌላው መለየት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ እንደ አክሊሉ ገለፃ አርጐቦች በትክክል በዚህ ዘመን፣ በዚህ አቅጣጫ፣ በዚህ ምክንያት ከዚህ ቦታ መጡ ማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንያቶች ቀስ በቀስ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው እስልምናን መሠረት በማድረግ የመጀመሪያውን የወላስማ ስልጣኔ በተደራጀ መልኩ ይፋት ላይ በመዘርጋት በ13ኛው ክፍለ ዘመን እስላማዊ የፖለቲካ ኃይል ሆነው መውጣታቸውን (1991፣ 9) ያስረዳሉ፡፡ አርጐቦች ወደ ሀበሻ የመጡበት ዘመን ከእስልምና እምነት መመስረት በፊትና በኋላ መሆኑን የሚገልጹት አክሊሉ የመጡበት ዋነኛ ምክንያትም ለንግድ፣ ኃይማኖትን ለማስፋፋት፣ በጦርነት እና በስደት ነው ይላሉ፡፡

አህመዲን በበኩላቸው የተለያዩ የአረብ ጐሳዎች ወደ ሐበሻ በተለያዩ ጊዜያት እንደመጡ አስፍረዋል፡፡ ለአብነትም በ738 (121 ዓ.ሂ.[5]) ኢማም ዛይድ ቢን ዓሊይ ዘይነል ዓቢዲን ሲገደሉ ተከታዮቻቸው ተበታተኑ፡፡ በዚህ ምክንያትም ወደ የመን፣ ሀበሻ (ኢትዮጵያ) እና ሶማሊያ በስደት ገብተዋል ይላሉ (2003፣ 79- 80)፡፡

---

[5] ዓ.ሂ. ዓመተ ሂጅራ ለማለት ነው፡፡

አለቃ ታዬ ደግሞ በይፋት ያሉት የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የአሊ ገዳይ የአብዱረህማን ዘሮች ናቸው፤ አሊ ከሞተ በኋላ የእሱን ዘሮች ብቀላ በመፍራት በአረብ ለመኖር በመስጋታቸው ወደ ይፋት መጡ ይላሉ (1964፣ 68)፡፡ አክሊሉ በበኩላቸው ከሊፋ ዑስማን በ656 እንደተገደሉ በአሊ መተካታቸውን ይገልፃሉ፡፡ የዑስማንን ደም ለመበቀል አሊን በመቃወም በተነሳው ሁከት አረቦች ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል ይላሉ፡፡ ይህ የማውያን ሁከት በመባል የሚታወቀው የተቃውሞ እንቅስቃሴ፣ የተካሄደው ከ656 እስከ 661 ዓ.ም በአሊ ዘመን ነው፡፡ እነዚህ ማውያዎች በኋላ ላይ ወላስማ በመባል ይጠሩ ነበር፡፡ ማውያዎች መጀመሪያ ያረፉበት ቦታ ዶባ ስለነበር ወላስማዎች ዶባ በመባል እንደሚታወቁም (1991፣ 12) ያስረዳሉ፡፡ ተክለ ጻድቅ "የዐረቦች ንጉስ ከሊፋ ኡመር ከሞተ በኋላ በ644 ዓ.ም. ከሊፋ ኦትማን፣ ከኦትማን በኋላ በ661 ዓ.ም. ከሊፋ አሊ ነገሰ" ይላሉ፡፡ ተክለፃድቅ አሊ ነገሰ የሚሉበት ዘመን አክሊሉ የስልጣናቸው መጠናቀቂያ ያደረጉትን ነው፡፡ በዚህ መልኩ አርጐቦች ወደ ሀበሻ የመጡበትን ዘመን ስናሰላው በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህ Richard V. Week's ከገለጹት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ነው፡፡

እንደ Weeks (1984፣ 53) አገላለጽ የመጀመሪያዎቹ አረቦች በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የሰፈሩት ምናልባት ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ750 አካባቢ ሳይሆን አይቀርም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተስፋዬ (1991፣ 4) የአርጐባ ማኅበረሰብ አመጣጥን በሚመለከት ሦስት የተለያዩ መላምቶች እንዳሉ ይገልፃሉ፡፡ ከእነዚህ መላምቶች መካከል አንዱ የዛሬ ስምንት መቶ ዓመት በፊት በኒ ኡመያ የተባለ የአረብ ጐሳ የፖለቲካ ሥልጣኑን በሌላ ጐሳ ሲነጠቅና በፍልሰት በዓለም ላይ ሲሠራጭ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ በጥናቱ ዳራ የተገለጸው ነው፡፡

ከዚህ አንጻር የአርጐቦችን ታሪክ ከእስልምና ታሪክ ለይቶ ማየት ከባድ ቢሆንም፣ መረጃ አቀባዮቹ ከተረኩትና በታሪክ ማስረጃዎች መሠረት አርጐቦች ከቁረይሽ ጐሳ የሚመዘዝ የዘር ሐረግ እንዳላቸው እንዲሁም በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ መገመት ይቻላል፡፡

አርጐቦች ዝርያቸው ከአንድ የአረብ የዘር ግንድ የሚመዘዝ መሆኑን ይቀበሉና በመጠሪያ ላይ ግን የተለያየ አመለካከት እንዳላቸው ቀጥሎ ከሰፈረው ቃላዊ ዝርው ተረክ መረዳት ይቻላል፡፡ ዘራቸውን በተመለከተ ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ እንደሚከተለው ተርከውልኛል፤

የአርጎባ ማኅበረሰብ በሦስት ጐሳዎች የተከፈለ ነው፡፡ እነዚህ ጐሳዎችም በኒ ሐሽም፣ በኒ አቂል እና በኒ ሙጠሊብ ይባላሉ፡፡ ሦስቱም ጐሳዎች የነብዩ መሀመድ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ የስደት ታሪካቸው ወደ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም የአረቡ ዓለም ተሠራጭተው የሚገኙ የተበታተኑ ጐሳዎች አድርጓቸዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የእነዚህ ጐሳ አባላት በተለያየ አካባቢ በተለያየ ስም ይጠራሉ፡፡ ስያሚያው የተሰጣቸው እንደሚኖሩበት አካባቢ እና እንደ ስልጣን ደረጃቸው ነው፡፡

የመጀመሪያው አሲፋ በመባል ይታወቃል፡፡ በአርጐብኛ ቋንቋ አ ማለት "ይህ" ማለት ሲሆን ሲፋ ደግሞ "መድህኒት" ማለት ነው፡፡ ኢሲፋ ማለት ወደ አማርኛ ሲመለስ "ይህ መድህኒት" እንደማለት ይሁን እንጂ፣ በዚህ ስያሜ የሚታወቁት ባለስልጣኖችና ቤተሰቦቻቸው ናቸው፡፡ የአሲፋ ጐሳ ከተባለ የባለስልጣን ጐሳ ማለት ነው፡፡ ስልጣኑ በዘር የሚወረስ ሳይሆን በምርጫ የሚገኝ ነው፡፡ የአርጐባ ማኅበረሰቦች ተሰብስበው በአመራር ብቃቱ እና በአስተዳደር ችሎታው ይመጥናል ያሉትን ሰው ይመርጣሉ፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ በዘሩ ምክንያት በመሪነት ቦታ ላይ የሚቀመጥ ሰው የለም፡፡ ምክንያቱም ህግ አለን፡፡ ህጋችን ቁርዓን ነው፡፡ በቁርዓን ህግ መሰረት በአግባቡ የማይመራ መሪን ህዝቡ ከስልጣን ያነሳዋል፡፡ ከስልጣን በተነሳው መሪ ምትክ ሌላ ይመርጣሉ፡፡ በዚህ መልኩ በመሪነት ያገለገሉ ሰዎች ዝርያዎች አሲፋ በመባል ይጠራሉ፡፡

ሁለተኛው ዶባ ይባላል፡፡ ዶባ ማለት የበሰለ ብርቱካን ቀለም ያለው ማለት ነው፡፡ በዚህ ስም የሚጠሩትም በጣም ቀይ የሆኑትን ወይም የበሰለ ብርቱካን የሚመስሉትን የማኅበረሰቡን ተወላጆች ነው፡፡

ሶስተኛው ሙዝገዬ ይባላል፡፡ "ገዬ" ማለት በአርጐብኛ ቋንቋ ሀገር ማለት ሲሆን፣ ሙዝገዬ " የሙዝ ሀገር" እንደ ማለት ነው፡፡ በዚህ ስያሜ የሚታወቁት በብዛት አትክልትና ፍራፍሬ በሚገኝበት አካባቢ የሚኖሩ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ናቸው፡፡ በጣም ቀያዮች አይደሉም፡፡

አራተኛው አምባ አይፈራ በመባል ይታወቃል፡፡ አምባ አይፈራ ማለት የጦር ምሽግ የሆነ ተራራ የማይፈራ ወይም ጦር የማይፈራ ማለት ነው፡፡ በዚህ ስያሜ የምንጠራቸው ጀግኖችንና በጣም ተቀጊ የሆኑ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆችን ነው፡፡

አምስተኛው ኩላያ ይባላል፡፡ ኩላያዎች ማለት መልካቸው ጠይም የሆኑ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ናቸው፡፡ ጠያይም የሆኑ የማኅበረሰቡ ተወላጆች የኩላያ ቤተሰቦች በመባል ይጠራሉ፡፡

ስድስተኛው ሸጐሬ ይባላል፡፡ ሸጐሬ ማለት በአረብኛ የዋህ እንደማለት ነው፡፡ በዚህ ስያሜ የሚታወቁት በወይናደጋ አካባቢ የሚኖሩ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ሲሆኑ ቋንቋቸውም ከሌሎች የአርጐባ ተወላጆች ትንሽ ለየት ይላሉ፡፡

ሰባተኛውና የመጨረሻዎች ቀሪቦ ይባላሉ፡፡ ቀሪቦ በመባል የሚታወቁት ኃይማኖታቸውን በጣም የሚያጠብቁት ናቸው፡፡ እነዚህ የማኅበረሰቡ አባላት ለፈጣሪ በጣም የተጠጉ ናቸው ተብለው በአርጐቦች ዘንድ ይታመናል (ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

እንደ ተራኪዎቹ ገለፃ አርጐቦች ለብዙ ዘመናት የሀገር[6] እና የኃይማኖት መሪዎች ሆነው ቆይተዋል፡፡ በመሪነት ዘመናቸው በተለያዩ የአገሪቱ ክፍል ተሰራጭተው አስተዳድረዋል፡፡ ነገር ግን የመሪነት ስልጣናቸውን በሌሎች ገዥ መደቦች ሲነጠቁ ከፍተኛ የሆነ ጫናና መፈናቀል ሊደርስባቸው ችሏል፡፡ የአፄዎች[7] ክንድ ሲያርፍባቸው እና ጫናው እየበረታባቸው ሲመጣ ግን ማንነታቸውን ለመካድ ተገድደዋል፡፡ "እኔ አርጐባ ነኝ" ከማለት ይልቅ "እኔ አሲፋ ነኝ፣ እኔ ዶባ ነኝ፣ ሙዝገዬ ነኝ፣ አምባ አይፈራ ነኝ፣ ወዘተ." በማለት በተለያየ አካባቢ በተለያየ ስያሜ ሲጠሩ ቆይተዋል፡፡ በተለይም ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመን በፊት በነበሩት የአገዛዝ ዘመናት የማህበረሰባቸውን ስም ደብቀው ኖረዋል (ሼህ መሀመድ አወል፣ አንኮበር፣ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

አክሊሉ ግን ዶባና ሸጐሬ የአርጐባ ዘሮች ናቸው ብሎ ለመቀበል እንደሚቸገሩ ይገልፃሉ፡፡ ምክንያቱም ዶባ የወላስማ የዘር ምንጭ ያለው ነው፡፡ መሬት የእሱ በመሆኑ የእስልምና ተከታዮች መሪ ሊሆን መቻሉን ይጠቁማሉ፡፡ በወቅቱ በነበረው መንግሥት የተመረጠ በመሆኑ ለቃዲዎች መሬት የሚሰጥ እሱ ነው፡፡ ቃዲ የሚመረጠው ደግሞ ከአርጐቦች ሲሆን ወላስማ ያልሆነ ማለት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ሸጐሬ ደግሞ ቋንቋው አርጐብኛ ሆኖ ዘሩ ግን ይለያል፡፡ በመልክም ቢሆን ሸጐሬዎች ጠቆር ያሉ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ አርጐቦች ዶባና ሸጐሬ የእኛ ዘር ነው የሚሉ ከሆነ ዶባና ሸጐሬ መሠረታቸው ኢትዮጵያ (Indigenous) በመሆኑ አርጐቦች ከአረብ መምጣታቸውን ለመቀበል እንቸገራለን ይላሉ (1991፣ 15-16)፡፡

የቃል አቀባዮቹ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የአክሊሉን ሀሳብ የሚሞግቱ ናቸው፡፡ በታሪክ የወላስማ (የይፋት) ስርዎ መንግስት ተብሎ የሚታወቀው ዘመን የአርጐባ ተወላጆች ኢትዮጵያን ያስተዳደሩበት ጊዜ እንደሆነ ይተርካሉ፡፡ ስለዚህ ወላስማ ማለት አርጐባ ማለት ነው ይላሉ፡፡ አክሊሉ እንደሚሉት ደግሞ የሸጐሬዎች ቋንቋ ከሌላው አርጐብኛ ጋር ተመሳሳይ ሳይሆን ትንሽ ለየት ይላል፡፡ ይህም ከማኅበረሰቡ የተለዩ መሆናቸውን

---

[6] አርጐቦች ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ ከ7ኛው እስከ 13 ክፍለ ዘመን ድረስ እንዳስተዳደሩ (ሺ.ህ ዩሱፍ፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.) ይተርካሉ፡፡ ይህ ተረክ በ4.3.1.ላይ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

[7]አርጐቦች "የአጼው ስርዓት" ወይም "የዘውዳዊ ስርዓት" አራማጆች በማለት በአሉታ የሚያነሷቸው ከአጼ ምኒልክ በፊት ኢትዮጵያን የመሩ የክርስትና እምነት ተከታዮችን ነው፡፡ እነዚህ ነገስታት በሙስሊሞች ላይ ከፍተኛ የሆነ ግፍና ጭቆና እንዳደረሱ (ሼህ መሐመድ አወል፣ አንኮበር ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም) ያስረዳሉ፡፡ በተለይም አጼ አምደ ጽዮን፣ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ፣ አጼ ልብነ ድንግል እና አጼ ዮሃንስን በአርጐባ ማኅበረሰብ ላይ ያደረሱት ጭቆና መረጃ አቀባዮቹ ደጋግመው አንስተውታል፡፡

የሚያረጋግጥ አሊያም ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ተቀላቅለው በመኖራቸው የመጣ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡

ከላይ የተገለጹት የቃል ተረኮች የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት መጠሪያቸውን እንዴት እንዳገኙ፣ ከየትና መቼ እንደመጡ፣ ለምን እንደመጡ ያላቸውን አመለካከት የማሳየት ፋይዳ አላቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አርጐቦች ዘውዳዊው ስርዓት ያደርስባቸው ከነበረው ጫና ለማምለጥ በተለያዩ ስያሜዎች ይጠሩ እንደነበር የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡

### 4.1.3. ከአርጐባ ሕዝብ አሠፋፈር ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች

አርጐቦች ቤታቸውን የሚሰሩት በጉባ (ተራራ) ላይ ነው፡፡ በተራራ ላይ ለመኖር የመረጡበት ምክንያት ራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ተራራ በቀላሉ የማይደረስበትና የአምባውም መግቢያና መውጫ የጠላትን ጥቃት በቀላሉ ለመቆጣጠር የሚያመች ከመሆኑም በላይ ነፋሻማነቱ ለጤንነት ተስማሚ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ለመኖሪያነት እንደሚመርጡት (አክሊሉ፣ 1991፣ 18) ያስረዳሉ፡፡ ሼህ መሀመድ ያሲንም አባቶቻቸውን በዋቢነት በመጥቀስ እንደነገሩኝ አርጐቦች ሜዳ ሜዳውን ቢያርሱም ቤታቸውን የሚገነቡት በተራራ ላይ ነው፡፡ ተራራ ላይ የሚኖሩበት ምክንያትም በገብር አልገብርም ሰበብ ጦርነት ይበዛባቸው ስለነበር ራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል የተሻለ በመሆኑ ነው (ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡ አርጐቦች ለምን ጠላት እንደሚበዛባቸውም አሚኑ ኢድሪስ የሚከተለውን ነግረውኛል፤

> አርጐቦች በስደት ወደ ሀበሻ የመጡት ሠላምን ፈልገው ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ ግን ከፊሩ (ቁረቡ) በመባላቸው ሠላም ሊያገኙ አልቻሉም። በዚህ ምክንያት በየወቅቱ ከነበሩት አፄዎች ጋር ጦርነት ይገጥሙ ነበር። አፄዎቹ እናቁርባችሁ ሲሏቸው፣ እነሱ ደግሞ ማተባችሁን እናስበጥሳለን በማለት ለረጅም ጊዜ ጦርነት አካሂደዋል። ለጦርነት እንዲያመቻቸው ተራራማና ሠንሠለታማ ቦታዎች ላይ ሰፍረዋል። ሜዳውን የሚገለገሉበት ለእርሻ ነው (ሸዋ ሮቢት፣ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

ከቃል ተረኩ እንደምንረዳው አርጐቦች ሠላምን ፈልገው ወደ ሀበሻ ቢመጡም የፈለጉትን ሠላም ግን ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ በተለያዩ ዘመናት የተፈራረቁት የአጼው ስርዓት አራማጆች የክርስትና ኃይማኖትን እንዲቀበሉ ሲያስገድዷቸው እነርሱ ደግሞ "እናሰልማችኋለን" በማለታቸው ሰበብ ለረጅም ጊዜ ጦርነት ሲያካሂዱ ቆይተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ራሳቸውን ለመከላከል ተራራ አመች በመሆኑ ለመኖሪያነት መርጠውታል፡፡ ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድም እንዲሁ አርጐቦች ተራራ ላይ ለመኖር

የመረጡት አገር ለማስተዳደርና የእስልምናን ኃይማኖት ለማስፋፋት በነበራቸው ፍላጐት ከሌሎች ጋር ግጭት ይፈጥሩ ስለነበር እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

> አርጐቦች አገር ሲገዙና የእስልምናን ኃይማኖት ሲያስፋፉ ለረጅም ዘመናት ጦርነት አካሂደዋል፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት ጦርነት ይካሄድ የነበረው በፈረስ እና በእግረኛ ሰራዊት ነበር፡፡ ለጦርነት ተመራጭ የሚሆኑት ደግሞ ተራራማ ቦታዎች ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት አርጐቦች ራሳቸውን ከጠላት ለማዳን የሚሰፍሩት በተራራማ ቦታዎች ላይ ነው፡፡ (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም.)

አርጐቦች የአገር መሪና የኃይማኖት መምህር እንደሆኑ ተረኩ ያስገነዝበናል፡፡ አርጐቦች አገር ለመምራትና የእስልምና ሐይማኖታቸውን ለማስተማር በሚያደርጉት ጥረት ከሌሎች ወገኖች ተቃውሞ ይገጥማቸው ነበር፡፡ የሚገጥማቸውን ተቃውሞ ለመቋቋም ደግሞ አመች የሆነው ቦታ ተራራ ነው፤ ለዚህም ተራራ እንደሚመርጡ ያስረዳሉ፡፡

መረጃ ለመሰብሰብ የተንቀሳቀስኩባቸው ጥንታዊ የሆኑ የአርጐባ መንደሮች የተመሰረቱት በኮረብታዎች ላይ ነው፡፡ የቤቶቹ አሰራር በከተማ የሚታየው መኖሪያ አይነት ባህርይ ያለው ነው፡፡ በተራራው ዙሪያ የሚሰሩ ቤቶች ከውጭ በኩል ግድግዳቸው የተያያዙ ናቸው፡፡ በዚህ መልክ መሰራታቸው ውስጥ ያለውን ነዋሪ ከአጥቂዎች ለመከላከል ምቹ እንደሆነ የሚገልጸው ተረክ እውነታ ያለው ይመስላል፡፡ የቤቶቹ የውጭ ግድግዳዎች ሲገጣጠሙ የመንደሩ አጥር በመሆንም ያገለግላሉ፡፡ አንድ መንደር ሁለት የመግቢያ በሮች ብቻ ሲኖረው፣ በሮቹም በጣም ጠባቦች ከመሆናቸውም በላይ በመቃናቸው ላይ በጣም ቀጭን የሆነ ዘሃ (ክር) ይታሰራል፡፡ ዘሃው ከተበጠሰ እንግዳ የሆነ ሰው ወደ መንደሩ መግባቱን ያረጋግጣሉ፡፡ የገባውን ሰው ማንነት ካላጣሩ አይተኙም፤ ወይም ተረጋግተው አይቀመጡም፡፡ መንደሩ ለእያንዳንዱ አባወራ መኖሪያነት የተከፋፈለ ሲሆን፣ እያንዳንዱ መኖሪያ ቤት የራሱ ግቢ አለው፡፡ አንዱን ቤት ከሌላው ጋር የሚያገናኝ የውስጥ ለውስጥ መንገድም ተሰርቷል፡፡

ይህ አይነት የቤት አሰራር ጠላት በቀላሉ ወደ ውስጥ እንዳይገባ ለመከላከል የሚያስችል ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ የቤታቸውን አሠራር አስመልክተው ሼህ መሀመድ አወል የሚከተለውን ተርከውልኛል፡፡



የአርጐቦች መንደር (ሾንኬ)

አርጐቦች ቤታቸውን በተራራ ላይ በድንጋይ ይሰራሉ[8]፡፡ መንደራቸውንም ሁለት በር እንዲኖረው በማድረግ በድንጋይ ያጥሩታል፡፡ አንደኛው የውሀ በር ሲሆን ሌላው የገበያ በር ይባላል፡፡ ውሀ ለመቅዳት መውጫና መግቢያ የሚያገለግልና ለገበያ መተላለፊያ የሚሆን ማለት ነው፡፡ ቤታቸውን በዚህ መልኩ የሚሰሩት ከአደጋ ለመዳን ነው፡፡ ጠላት በቀላሉ ወደ ተራራ መውጣት አይችልም፡፡ ቤቶችን በሰደድ እሳት ማቃጠልም አይሆንለትም፡፡ ሌላው ቤታቸውን በድንጋይ የሚሰሩበት ምክንያት በቀዳሚው አገራቸው በሳውዲ አረቢያ እያሉ ቤታቸውን በድንጋይ ይሰሩ ስለነበር ከዚያ በለመዱት መሰረት በስደት ወደዚህ ከመጡ በኋላም በተመሳሳይ መልኩ ቤታቸውን የሚሰሩት በድንጋይ ነው፡፡ ድንጋዩ ከሙቀት ይከላከልላቸዋል (አንኮበር፣ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም.) ፡፡

ከተረኩ እንደምንረዳው አርጐቦች ጉባ ላይ የሚኖሩት ራሳቸውን ከጥቃት ለመከላከል ከመሆኑም በተጨማሪ ሙቀትን ለመቀነስ ጭምር ነው፡፡ የድንጋይ ግንባታው መነሻም የትውልድ አገራቸው እንደሆነ ከሚታመንበት ከሳዑዲ አረቢያ የተገኘ ልምድ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ይህን ሀሳብ ተስፋዬም ይጋሩታል፡፡ የአርጐቦች ቤት በአብዛኛው ከድንጋይና ከእንጨት የሚሠራ ግንብ ሲሆን፣ ይህም በጥንት ጊዜ ከየመን የመጡት ዓረቦች ቤታቸው ግንብ ስለነበረ ከዚያ የተወረሰ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው (ተስፋዬ፣1991፣ 22) አስፍረው እናገኛለን፡፡ የቤቶች ግድግዳ ከድንጋይ፣ ከእንጨትና ከጭቃ የሚሠሩ ሲሆን ጣሪያቸው ደግሞ ቀለጡ ከሚባል ወፍራም እንጨት፣ ማጊ ከሚባል ቀላልና ትንንሽ እንጨት ላይ ርጥብ ቅጠል ከተደረገ በኋላ ዝናብ ሲዘንብ ወይም ውሀ ሲነካው የማይፈርስ ጭቃ ከአፈር ተቦክቶ ይደረግበታል፡፡ በዚህ መልኩ የተሰራውን ጣሪያ ለእህል ማስጫ እና ለመስገጃነት ሲገለገሉበት ይስተዋላል፡፡

[8]ሼህ መሐመድ አወል እና ሌሎች መረጃ አቀባዮቹ የአርጐባ ተወላጅ ሆነው የሚተርኩት ግን እነሱ እያሉ ነው፤ ስለሆነም ተረኮቹ እነሱ በተረኩበት መንገድ እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡



የአርጐቦች ቤት (ሾንኬ)

በአርጐቦች መንደር አልፎ አልፎ ጣሪያቸው በሳር የተከደኑ ቤቶችም ይስተዋላሉ፡፡ እንደዚህ አይነት ቤቶች በሰላም መኖር ከጀመሩ በኋላ እንደተሰሩ ከመረጃ አቀባዮቼ መገንዘብ ችያለሁ፡፡ የቤታቸው አሰራር በአብዛኛው አዳራሽ ሆኖ ሦስት ክፍሎች አሉት፡፡ እነዚህ ክፍሎች መኝታ ቤት (ነደባ)፣ የምግብ ማብሰያ (ዴራ)፣ የከብቶች ቤት (ጐላ) በመባል ይታወቃሉ፡፡ በዚህ ክፍፍል መሠረት መኝታ ቤቱ የአዋቂ ሰዎች የእንግዳ መቀመጫና ማረፊያ (መኝታ) ሲሆን የሚገኘውም ከቤቱ ዋና በር ፊት ለፊት ነው፡፡ የምግብ ማብሰያው ደግሞ ልዩ ልዩ የመገልገያ ቁሳቁስና የበሰለ ምግብ የሚቀመጥበት፣ ሴቶች እና ዕድሜያቸው እስከ ስምንት ዓመት የሚደርስ ልጆች ለመኝታነት የሚገለገሉበት ነው፡፡ ይህ ክፍል የሚገኘው ከቤቱ በስተግራ በኩል ነው፡፡ ማንኛውም ቤት ሲሰራ በስተቀኝ በኩል የከብቶች ቤት እንዲኖረው ተደርጐ እንደሆነ ተስፋዬ (1991፣ 23) ይገልፃሉ፡፡ እኔም በመስክ ቆይታየ ይህንኑ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ከብቶች ከሰዎች ጋር የሚያድሩበት ምክንያትም ከጠላቶቻቸው ዘረፋ ለመጠበቅ መሆኑን (ሐጅ መሀመድ፣ ሾንኬ፣ ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓ.ም.) ያስረዳሉ፡፡

አርጐቦች ስለቤት አሠራራቸው መተረካቸው ለማኅበረሰቡ ምን ጥቅም ያስገኛል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ የቤት አሰራራቸውን ተገን በማድረግ የእስልምና ኃይማኖትን ያስፋፉትና ጠብቀው የኖሩት በሠላም ሳይሆን በጦርነት እንደሆነ ለማስገንዘብ ይመስላል፡፡ ይህም የማኅበረሰቡን ጀግንነትና አስተማሪነት የሚያስርጽ ነው ማለት ይቻላል፡፡ "እስልምናን አሁን ከደረሰበት ደረጃ ያደረስነው እኛ ነን" በማለት የራሳቸውን ማንነት ለመገንባት አስችሏቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ  የማኅበረሰቡን ታሪካዊ የመሪነት ሚና በመዘከር የበላይነት መንፈስ በሌሎች ላይ ለማስረጽ ይረዳቸዋል ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

ሼህ አህመድ አባቡሽ በበኩላቸው በተራራ ላይ የሚኖሩት ራሳቸውን ከኦሮሞች ጥቃት ለመከላከል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በርካታ የኦሮሞ ተወላጆችን የእስልምናን እምነት እንዲከተሉ ያደረጓቸው አርጐቦች በመሆናቸው ኦሮሞዎች እንደማይወዷቸው ይገልፃሉ፡፡

> የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የምንኖረው በተራራ ላይ ነው፡፡ በተራራ ላይ የምንኖረው ከኦሮሞዎች ጥቃት ራሳችንን ለመከላከል ነው፡፡ ኦሮሞዎች አርጐቦችን እየፈለጉ ይገድሏቸዋል፡፡ ምክንያቱም በርካታ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች የእስልምናን ኃይማኖት እንዲቀበሉ ያደረጉ አርጐቦች ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ኦሮሞዎች አይወዱንም፡፡ በተራራ ላይ የምንኖረውም ኦሮሞዎች ሊያጠቁን ሲመጡ በቀላሉ ለመከላከልና ድል ለማድረግ ስለሚያስችለን ነው፡፡ ኦሮሞዎች የሰፈሩት ሜዳ ሜዳውን ስለሆነ የሚያደርሱብንን ጥቃት በቀላሉ ለመከላከል ተራራ ላይ መስፈር ማለፊያ ነው፡፡ (ሼህ አህመድ አባቡሽ፣ ሾንኬ፣ ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

ከተረኩ እንደምንረዳው የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች በተራራ ላይ የሚኖሩት በአካባቢያቸው ከሚኖሩ የኦሮሞ ጥቃት ራሳቸውን ለመከላከል እንደሆነ ነው፡፡ አርጐቦች ከአካባቢያቸው ማኅበረሰብ ጋር የፈጠሩት ግጭት ዘመን ተሻግሮ እስካሁን ድረስ የዘለቀ ይመስላል፡፡ እንደ አክሊሉ ገለፃ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ከጥንት ጀምሮ "አረማውያን" ባሉበት አካባቢ ስለሚኖሩ ጥቃት ይደርስብናል ከሚል ፍርሀት የተነሳ ከመንደሩ ውጭ ያለውን ሁሉ በጥንቃቄ ይመለከታሉ፡፡ ሌላውን የማያምኑና በጣም ተጠራጣሪ እንደሆኑ (1991፣ 21) ያስረዳሉ፡፡ አርጐቦች በአካባቢያቸው ከሚኖሩ ሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር አልፎ አልፎ በእርሻ ቦታ መገፋፋት ምክንያት እንደሚጋጩም ከመረጃ አቀባዮች ተረድቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ አርጐቦች ሌሎች ከሚያደርሱባቸው ጥቃት እራሳቸውን ለመከላከል በተራራ ላይ እንደሰፈሩ መረዳት ይቻላል፡፡ የማኅበረሰቡ አባላት ስለአሰፋፈራቸው መተረካቸው ራሳቸውን ከጥቃት ለመከላከል እንጂ፣ በሌላው ላይ ጉዳት ለማድረስ እንዳልሆነ ለመግለጽ ይመስላል፡፡ ይህም አርጐቦች መልካም ስነምግባር የተላበሱ እንደሆኑ ለማስረጽ ያግዛቸዋል፡፡ በዚህም ሌላውን ተንኳሽ ራሳቸውን ተከላካይ አድርገው በማቅረብ ሰላማዊ መሆናቸውን በመግለጽ በአካባቢው የሚኖሩ ማኅበረሰቦች እንዳይደርሱባቸው (እንዳይተነኩሷቸው) የሚያሳስብ ይመስላል፡፡

በጥናቱ ዳራ እንደተገለጸው አርጐቦች በአማራ፣ በአፋር፣ በኦሮሚያና በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ ተሰራጭተው ይገኛሉ፡፡ ለመሰራጨታቸው አክሊሉ

በምክንያትነት የሚጠቅሱት ንግድን፣ መሬት ፍለጋን፣ ኃይማኖትን ማስፋፋት፣ ጋብቻ፣ ጦርነትና ችግርን ነው፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች አርጐቦች ከአንድ ቦታ ተነስተው ወደ ሌላ ቦታ ሂደው እንደሰፈሩ (1991፣ 21) ያስረዳሉ፡፡ ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ ግን አርጐቦች በተለያዩ ክልሎች ተበታትነው የሚኖሩት እስልምናን ለማስፋፋት እንደሆነ በመተረክ ምክንያቱን ያጠብቡታል፡፡

> አርጐቦች ከአረብ ሀገር ሲመጡ ይዘው የመጡት የእስልምናን ኃይማኖት ነው፡፡ ይህንን ሐይማኖታቸውን ለማስፋፋት ደግሞ ወደ ተለያዩ ቦታዎች መንቀሳቀስ የግድ ይላቸው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት አርጐቦች እስልምናን ለማስተማር በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡ በወቅቱ በትግራይ፣ በአማራ፣ በአፋር፣ በኦሮሞ፣ በደቡብና በተለያዩ አካባቢዎች ተንቀሳቅሰው እስልምናን አስተምረዋል፡፡ በመምህርነት የተንቀሳቀሱት የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች በየሔዱበት አካባቢ በመስፈር ሐይማኖታቸውንና ባህላቸውን አስፋፍተዋል (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የእስልምናን እምነት እንዳስፋፉ የሚናገሩት አርጐቦች በተለያዩ ቦታዎች ተሰራጭተው ለመኖራቸው ሼህ ዩሱፍ ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡት የኃይማኖት ትምህርት ማስተማርን ነው፡፡ የእስልምናን ኃይማኖት ለማስተማር ወደ ተለያዩ አካባቢዎች የተንቀሳቀሱት አርጐቦች ሐይማኖታቸውን ብቻ ሳይሆን ባህላቸውንም እንዳስፋፉ ያስረዳሉ፡፡ አሚኑ ኢድሪስ እና ሐጅ ኡመር በበኩላቸው የእንቅስቃሴያቸው ምክንያት ንግድ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

> አርጐቦች ከአረብ ሀገር እንደመጡ የሰፈሩት ሰሜን ሸዋ አካባቢ ነው፡፡ ሰሜን ሸዋን የመረጡትም ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት የአፋር ጠረፋማ አካባቢ ተጉራባች በመሆኑና ከበረሀው ይልቅ ለኑሮ አመቺ ስለሆነ ነው፡፡ በወቅቱ አርጐቦች ታዋቂ ነጋዴዎች ነበሩ፡፡ ከሶማሊያ፣ ከጅቡቲ፣ ከየመንና ከህንድ ሀገራት ጋር ጥሩ የሆነ የንግድ ግንኙነት ነበራቸው፡፡ ይፋት ደግሞ በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ ከተሞችና ከውጭ አገራት ጋር ለመገናኘት አማካይ ቦታ ነው፡፡ ይህ ቦታ ሸቀጦችን ከውጭ በማስገባት ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለማሠራጨትና ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ደግሞ የዝሆን ጥርስና ሌሎች ሸቀጦችን፣ እንዲሁም ባሪያዎችን አሰባስቦ ወደ ውጪ ለመላክ ምቹ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አርጐቦች ለመኖሪያነት ሰሜን ሸዋን መርጠዋል (አሚኑ ኢድሪስ፣ ሸዋ ሮቢት፣ ግንቦት 2004 ዓ.ም.፤ ሐጅ ኡመር መሀመድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)፡፡

ከተረኩ እንደምንረዳው አርጐቦች በንግድ እንቅስቃሴ የታወቁ ነበሩ፡፡ ከውጪው አለም ጋር በመገናኘት ረገድ ስማቸው ይነሳል፡፡ በተለይም ደግሞ ከሙስሊሙ ኅብረተሰብ ጋር በመገናኘት ረገድ ስማቸው ይነሳል፡፡ በተለይም ደግሞ ከሙስሊሙ ኅብረተሰብ ጋር በመገናኘት የተለያዩ ሸቀጦችን ወደ ውጭ በመላክና ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ ያስገቡትን ወደ

ተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በማሰራጨት ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተበታትነው ለመኖር እንደቻሉ መተረካቸው ለእውነታ የቀረበ ይመስላል፡፡ ሚሊዮን የእስልምና ኃይማኖትም በብዙ ቦታ ላይ ሊደርስ የቻለው በሙስሊም ነጋዴዎች አማካይነት እንደሆነ ይገልፃሉ (ከሚሴ፣ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡ በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ስማቸው ከሚነሳው የተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል አርጐቦች ይገኙበታል ይላሉ፡፡ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ሙሉ በሙሉ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ሲሆን፣ በንግዱ ዘርፍም አሁንም ድረስ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል አርጐቦች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ሊሰራጩ የቻሉት ሀገር ለማስተዳደር እንደሆነ ሼህ መሀመድ አወል ይገልጻሉ፡፡

> አርጐቦች ለረጅም ጊዜ ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ ነበር፡፡ ሀገር ለማስተዳደር ደግሞ አመች የሚሆነው ማዕከላዊ ቦታ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አርጐቦች ይፋት ወይም ሰሜን ሸዋ ላይ ለመስፈር ችለዋል፡፡ አርጐቦች በዋናነት ሰሜን ሸዋ ይስፈሩ እንጂ፣ ከማዕከላዊ እስላማዊ መንግሥት እየተሾሙ የተለያዩ አካባቢዎችን ለማስተዳደር በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ይኖሩ ነበር፡፡ የእነሱ ቤተሰቦችም እስከ ዛሬ ድረስ በተለያዩ ቦታዎች ሰፍረው ይገኛሉ (አንኮበር፣ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

አርጐቦች በዋናነት ሰፍረው የሚገኙት ሰሜን ሸዋ አካባቢ እንደሆነ በሁለቱም ሰዎች የቃል ተረክ ውስጥ ይስተዋላል፡፡ ሰሜን ሸዋን ለመኖሪያነት የመረጡበትን ምክንያት በማስረዳት ረገድ ግን ሁለቱ ልዩነት አላቸው፡፡ አንደኛው የአገሪቱ ማዕከላዊ ቦታ በመሆኑ ለንግድ አመቺ እንደሆነ ሲገልጹ፣ ሌላው ደግሞ አገር ለማስተዳደር አመቺነቱን ያስረዳሉ፡፡ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍል ተሰራጭተው የሚገኙት ግን የእስልምና ኃይማኖትን ለማስፋፋት፣ ለንግድና አገር ለማስተዳደር እንደሆነ ከተረኮቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አርጐቦች እነዚህን ተረኮች መተረካቸው ምን ጥቅም ያስገኝላቸዋል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ የማኅበረሰቡ አባላት እኛ የኃይማኖት አስተማሪዎች፣ ታታሪ ነጋዴዎችና አገር መሪዎች ነን ለማለት እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ በዚህም ከሌሎች የተሻሉ መሆናቸውን በማስረጽ ማንነታቸውን ለመገንባት ተረኮቻቸው ከፍተኛ ሚና አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

## 4.2. ከጋብቻ፣ ከሽምግልና እና ከእደ ጥበብ ሙያ ጋር የተገናኙ ተረኮች

### 4.2.1. ከጋብቻ አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች

አርጎቦች ራሳቸውን ልዩ ዘር አድርገው በመቁጠር ከሌላው ዘር ጋር ላለመቀላቀል ሲሉ በጋብቻ አይተሳሰሩም፡፡ ጋብቻ የሚመሰርቱት ከጐሳቸው አባል ጋር፣ ምናልባትም ከአጐትና ከአክስት ልጆች ጋር ነው፡፡ ሌላውን ዝቅ አድርገው የማየት ዝንባሌ አላቸው፡፡ ከነብዩ መሀመድ የዘር ሐረጋቸውን ይመዝዛሉ (አክሊሉ፣ 1991፣ 21)፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሼህ መሀመድ ሲራጅ የሚከተለውን አጫውተውኛል፡፡

> የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ከሌላ ብሔር ጋር አንጋባም፡፡ እኛ የቁረይሽ[9] ጐሳ አባል ነን እንላለን፡፡ የእኛ ዘር ከሌላ ዘር ጋር አይገጥምም የሚለት አስተሳሰብ አለን፡፡ በአንድ ወቅት አንድ የሚያምር የአርጐባ ተወላጅ ለአንድ ንጉስ ግንብ ሲገነባ የንጉሱ ልጅ አይታው ወደደችው፡፡ ለአባቷም አግብታው ከእሱ ጋር መኖር እንደምትፈልግ ትገልጽላቸዋለች፡፡ ንጉሱም ልጁን እንዲያገባ ይጠይቁታል፡፡ የአርጐባ ተወላጁም "ከሰለመች አገባታለሁ" ይላል፡፡ እስልምናን ካልተቀበለች ግን እንደማያገባት ይገልጽላቸዋል፡፡ እሷም እስልምናን ተቀብላ አገባችውና ልጅ ወለዱ፡፡ የልጁን ስም ወርቅ ኸሰር ብሎ ጠራው፡፡ወርቅ ኸሰር ማለት ወርቅ ከሰረ እንደማለት ነው (ሸዋሮቢት፣ ግንቦት፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ ቃላዊ ዝርው ተረክ መረዳት እንደሚቻለው የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት የራሳቸውን ማንነት(identity) ሲገልጹ ከሌሎች ጋር በማወዳደር ነው፡፡ ውድድሩም ዝርያቸው ከሌሎች የተሻለ ነው በሚል ነው፡፡ ለራስ ከሚሰጥ ከፍ ካለ ግምት የሚመነጨው የማንነት ግንባታ እሳቤያቸው በአንድ በኩል የአስተዳደር መሪነት ድርሻቸውን በማጉላት የመደብ የበላይነት ስሜት ለማስረጽ ሲያገለግላቸው በሌላ በኩል ደግሞ የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ብቻ ሳይሆኑ የእምነት መሪዎችና ባለቤቶች መሆናቸውን የሚያረጋግጥላቸው የትውልድ ሐረግ ከነብዩ መሀመድ በመምዘዝ መንፈሳዊ ከፍታን ፈጥረዋል፡፡ ስለሆነም የማንነት ተረክ መሠረታቸው ሥጋዊና መንፈሳዊ ገጽታን አጣምሮ የያዘና የዝርያቸውን ልዕልና አግዝፎ ለማሳየት በእጅጉ የሚያግዝ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የእስልምና ኃይማኖት ጀማሪዎች መሆናቸውን ለማስረዳት መጤነታቸውንና የአረብ ምድር መነሻቸውን ማስረጃ ሲያደርጉ ለአስተዳደራዊ የበላይነታቸው የወላስማ እስላማዊ ስርዎ መንግሥትን በታሪክ

---

[9] እንደ ሼህ መሐመድ ሲራጅ ገለፃ ነብዩ መሐመድን ያሳድዷቸው የነበሩት የራሳቸው ጐሳ የ"ቁረይሽ" አባላት ናቸው፡፡

ግስረጃነት ያቀርባሉ፡፡ ከንጉስ ልጅ በጋብቻ መተሳሰር እንኳ የማይመጥናቸው መሆኑን ገመጠቆም ልዩ መሆናቸውን ለማንጸባረቅ ይሞክራሉ፡፡

ማኅበረሰቡ አባላት ከራሳቸው የትውልድ ሐረግ ውጭ እንዳያገቡ በተረካቸው ሚማካይነት በአርፈህ ተቀመጥ ማስጠንቀቂያ የሚቆጣጠሩበት ተረክ እንዳለቸው ሼህ ዩሱፍ የነገሩኝ ተረክ ዋቢ ሊሆን ይችላል፤

> የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር አይጋቡም፡፡ አርጐባ የሚኖረው ዘሩን ጠብቆ ነው፡፡ ዘሩ ከሌላ ዘር ጋር እንዲበረዝ አይፈልግም፡፡ ሰው የገዛ ዘመዱን ሲያገባ መተዛዘንና መከባበር ይኖራል፡፡ "አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ" መባባልን ይፈጥራል፡፡ ይህም ዝምድናን የበለጠ ያጠናክራል፡፡ አንድ የአርጐባ ተወላጅ ከማኅበረሰቡ ውጪ ቢያገባ ይገለላል፡፡ ለምሳሌ ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ የአርጐባ ተወላጅ ከማኅበረሰቡ ውጪ የሆነች ልጅ አገባ፡፡ ከማግባቱ በፊት ከወንድሙ ጋር በአንድ ግቢ ውስጥ ቤታቸውን ፊት ለፊት ሰርተው ይኖሩ ነበር፡፡ ጋብቻ ከመሠረተ በኋላ ግን ወንድሙ ቀደም ሲል ይገለገልበት የነበረውን የቤት በር በመዝጋት እና የግቢውን በር በመተው ሌላ በር ከፈተ፡፡ ይህም ለወንድሙ ያለውን ጥላቻ ለመግለጽ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ተግባራት መፈፀማችን ለረጅም ጊዜ ማንነታችንን ጠብቀን እንድንኖር አስችሎናል (መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም)።

ይህ "የአርፈህ ተቀመጥ" ግሳጼን የያዘ ተረክ የወጣቱን ደፋር ድርጊት የለወጠ ባይሆንም የሌሎች አፈንጋጮች መቀጣጫ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ የማኅበረሰቡን የጋብቻ ወግ ለመፃረር ፍላጎት ያለው ሁሉ የመገለል ቅጣትን (Social exclusion) ፈርቶ "አርፎ እንዲቀመጥ" ለአይደፈሬው የማኅበረሰቡ ስርዓት እንዲገዛና ማንነቱን ጠብቆ ገዥውን አስተሳሰብ እንዲያስቀጥል ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም አርጐቦች ማንነታቸውን ጠብቀው ለመኖር ተረኮቻቸው ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አበርክተውላቸዋል፡፡ እነሱ ትክክል ናቸው ከሚሏቸው እሴቶች ለማፈንገጥ ዳር ዳር የሚሉትን በ"አረፈህ-ተቀመጥ" ግሳጼ ወደ ብዙሀኑ አስተሳሰብ ይመልሷቸዋል፡፡ ማኅበረሰቡ ትክክል አይደሉም የሚላቸውን ስነምግባሮች እንዳይደረጉ፣ እንዳይስፋፉ በመጠበቅ የማኅበረሰቡን ማንነት በዘላቂነት ለመጠበቅ ይገለገሉባቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

### 4.2.2. ከሽምግልና ስርዓት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች

በአርጐባ ማኅበረሰብ በአረጋውያን የሚፈፀም የእርቅና ግልግል ልማድ ረከቦት ይባላል። ረከቦቱ የሚፈፀመው ልምድ ባላቸው ሰዎች ነው፡፡ ልምድና እውቀቱ የወላጅ ውርስ ሆኖ የሚያገኙት ሲሆን ልጅ ከአባቱ ተጠግቶ እየተማረ ለልጁ በማውረስ ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣ ያስረዳሉ። የሽምግልና እውቀቱና መነሻ የእስልምና አስተምህሮው መሪና

ርአያ የሆነው ኡላማ ነው። ለኡላማው ከአላህ የሚሰጠው ኢጃዛ (ፈቃድ) ነው ይላሉ። ኢጃዛ ባህርይ የነብዩ መሀመድ ባህርይ ነው ሲሉ፣ የነብዩ ባህርይ ደግሞ ቅዱስ ቁርዓንን ይመስላል ይላሉ። በዚህ ምክንያት ሰዎች ከረከቦቱ ፈቃድ አይወጡም። ከእሱ ፈቃድ የሚወጡትን ፈጣሪ እንደሚበቀላቸው ያምናሉ (ሼህ መሀመድ፣ አንኮበር፣ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም)። ለዚህም ይመስላል ከማኅበረሰቡ አባላት ውጭ የሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ጭምር ሲጋጩ በአመዛኙ የአርጎባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የአስታራቂነትን ሚና የሚይዙት፡፡ ይህን አስመልክቶ ሼህ አረቡ ሁሴን የሚከተለውን ተርከውልኛል፤

> ረከቦት ማለት ትልቅ ቤተሰብ ማለት ነው። ረከቦቶች የወልይዎች፣ የሼሆች (የትልልቅ ሰዎች) ልጆች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ልመናቸው የፈጣሪን ፈጣን ምላሽ የሚያስገኝላቸው፣ ሌላው ቀርቶ ግደል ካሉት የሚገድልላቸው፤ አድርግ ያሉትን በሙሉ የሚያደርግላቸው ናቸው።
>
> ልጆቹ ወይም ከቤተሰቤ አንዱ ከሰው ጋር ከተጋጨ ወይም ከተበደለ ወደ ረከቦቶች በመሄድ ሙስባህ (አንካሴ) በመቀበል ወስጄ እሰጣቸዋለሁ። በዚህን ጊዜ በዳዩ እነሱ ጋ ይቀርባል። እምቢ ብሎ የሚቀር የለም። ከቀረ አንዳች ችግር ያጋጥመዋል። በዳይ እንደቀረበ እነሱም ነገሩን አጣርተው ቀላል ከሆነ ያስታርቁናል። ከባድ ከሆነ ቀጠሮ በመስጠት እያንዳንዳችን ሁለት ሁለት ሽማግሌ ይዘን እንድንመጣ ያደርጋሉ። በቀጠሮው ቀን በዳይና ተበዳይን ፊት ለፊት እንድንከራከር ያደርጋሉ። እኔ ተበድዬ የደረሰብኝን በደል ስናገር በዳይ መልስ ይሰጣል። ከክርክሩ በኋላ ሁለታችንም ተከራካሪዎች እንድንወጣ ይደረጋል። ከዚያም ከሽማግሌዎች ጋር በመነጋገር ፍርድ ይሰጣሉ። የተጋጨነው ወገኖች እንጠራና "እንደዚህ አይነት በደል አይተናል። በበዳዩ ላይም እንዲህ ወስነናል። ስለዚህ በዳይ እንደዚህ ያለ ካሳ ትክሳለህ" ይላሉ። ላይም እንዲህ ወስነናል። ስለዚህ በዳይ እንደዚህ ያለ ካሳ ትክሳለህ" ይላሉ። የተወሰነበትም ከእናንተ አልወጣም እክሳለሁ ይላል። በዚህም እርቅ ይወርድና እንዝያየራለን። ነገሩ በዚህ መልኩ ይቋጫል (ሼህ አረቡ፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 8 ቀን 2004 ዓ.ም )።

በረከቦቶች የታረቀ ሰው ካሳ "አልከፍልም" ወይም ቂም ይዞ "ልበቀል" አይልም፡፡ በቀል የሚያስብ አንዳች የሆነ ችግር እንደሚገጥመው በተረኮቻቸው ይገልፃሉ፡፡ ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ ረከቦቶች የሚያስታርቁት የማኅበረሰቡን አባላት ብቻ አለመሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በአፋር፣ ኦሮሞ እና አማራ ማኅበረሰቦች መካከል ከጊዜያዊ ፀብ ያለፈ እስከ ግድያ የሚደርስ አለመግባባት ሲፈጠር በአርጎባ ረከቦቶች ወገን በኩል የእርቅ ጥረታቸው ተቀባይነት እንደሚያገኝ ይገልፃሉ፡፡ የተቀባይነታቸው ምንጭ ኃይማኖታዊ መሪነታቸው ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡

አርጎቦች በአካባቢያቸው ኀብረተሰብ ዘንድ የሚታወቁት በአስታራቂነታቸውና በኃይማኖት አስተማሪነታቸው እንደሆነ (ከበደ አለሙ፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 7 ቀን 2004

.ም) የሰጡኝ እማኝነትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ይህን እውነታም ሼህ ዩሱፍ
ብዱልሰመድ ተርከውልኛል፡፡

> አርጐቦች በሌላው ኅብረተሰብ ዘንድ ከሚታወቁባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የረከቦት ሥርዓታቸው ነው፡፡ አንድ ማኅበረሰብ ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር ሲጋጭ ለአስታራቂነት የሚመረጡት አርጐቦች ናቸው፡፡ አፋር፣ ኦሮሞና አማራ ሲጋደሉ ተው ባዮች የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ናቸው፡፡
>
> ሰው ተጋደለብን ወይም ተጋጨብን የሚል መልዕክት ሲደርሳቸው ሰይፍ ወይም ሙስብሀ (አንካሴ) ለሁለቱም ወገን ይላካል፡፡ መልዕክቱ እንደደረሳቸው ግጭቱ ይቆማል፡፡ ዳስ ይጣልና ከሁለቱም ወገን ሽማግሌዎች ይመረጣሉ፡፡ ደም አድራቂዎቹም ይዘዋቸው የሚሄዱን ሽማግሌዎችን ይመርጣሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ቀጠሮ ይያዛል፡፡ በቀጠሮው ቀን ሁለቱም ወገኖች ከነቤተሰቦቻቸው ይገኛሉ፡፡ በቀጠሮው ቀን የሚቀር አይኖርም፡፡ ምክንያቱም የሚቀሩት ሰዎች ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሽምግልናው ይደረጋል፡፡ ጠቡን ማን እንዳስነሳው፣ የጠቡ መነሻ ምን እንደሆነ፣ የጠፋው ንብረትና ህይወት ምን ያህል እንደሆነ ያጣራሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ሚዛናዊ ፍርድ ይሰጣሉ፡፡ በፍራቻ ወይም በጥቅም ተደልለው የተዛባ ፍርድ አይሰጡም፡፡ በዚህ ምክንያት ተቀባይነት ለማግኘት ችለዋል፡፡ ከእርቅ በኋላ እርቁን አፍርሶ ያልተገባ ነገር የሚፈጽም ሰው ችግር ይገጥመዋል፡፡ ለአላህ ቅርብ በመሆናቸው ተአምራቸው በጣም ፈጣን ነው፡፡ ፀሎት ሲያደርጉ አላህም ፀሎታቸውን ሰምቶ የእርቅ ስርዓቱን ባፈረሰው ሰው ላይ አንዳች መአት ያወርዳል፡፡
>
> ለምሳሌ አንዴ የጐሳ ግጭት ተነሳና ወደ 17 ሰዎች ሞቱ፡፡ የተጐጅ ወገኖች መልዕክት ላኩ፡፡ "ግጭቱን አቁሙ እናስታርቃችሁ፤ ለሞተው የደም ዋጋ እናስከፍላለን፡፡ የጠፋውን ንብረት እናስመልሳለን" ብለው ላኩባቸው፡፡ ግጭቱ ቆመና የጠፋው ህይወትም ታወቀ፡፡ የወደመው ንብረት ተቆጠረ፡፡ ከዚህ በኋላ ቀጠሮ ተያዘ፡፡ በቀጠሮው ቀን የሚች ወገኖች በገዳይ ወገን ላይ አደጋ ለመጣል ለሁለት ተከፍለው ያደፍጣሉ፡፡ የገዳይ ወገን ግን በሌላ መንገድ ሄደው ኖሮ ከሽምግልናው ቦታው በሰዓቱ ይደርሳሉ፡፡ የተበዳይ ወገኖች በመቅረታቸው ሽማግሌዎች ምክንያቱን ሲያጣሩ ደፈጣ ማድረጋቸውን ይደርሱበታል፡፡ "ለምን እንደዚህ አይነት ሥራ ትሰራላችሁ?" ብለው መልእክት ላኩባቸው፡፡ በዚህን ጊዜ በአንደኛው ቦታ ላይ ያደፈጡት "ባላንጣዎቻችን ከሽምግልናው ቦታ ከደረሱ እኛም ወደዚያው እንሂድ" ብለው መንገድ ይጀምራሉ፡፡ በጉዞ ላይ እያሉ የገዛ ዘመዶቻቸው የገዳይ ወገን የመጣ መስሏቸው ተኮሱባቸው፡፡ እነርሱም የጠላት ወገኖች መስለዋቸው መሬት በመያዝ ተታኮሱ፡፡ በተካሄደው ተኩስ ሦስት ሰዎች ሞተው ሦስት ደግሞ ቆሰሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ የአካባቢው ማኅበረሰብ ከብቦ በመያዝ ከሽማግሌዎች ፊት አቀረባቸው፡፡ ይህ ችግር የደረሰባቸው የደም አድራቂዎችን ቃል በማፍረሳቸው ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ችግር ስለሚያጋጥም ከሽማግሌዎች ቃል የሚወጣ የለም (ሼህ ዩሱፍ ፡ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

ይህ ተረክ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ከሌሎች በተለየ መልኩ ለእርቅና ግልግል ትልቅ ትርጉም እንደሚሰጡ ያሳያል፡፡ ረከቦቶቻቸው በፍራቻና በጥቅም የማይደለሉ መሆናቸውን በኅብረተሰቡ ውስጥ በማስረጽ የእነሱን ተቀባይነት ከፍ ለማድረግ ተረኮቹ

ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ የረከቦቶቹ የሽምግልና አቅም የሚመነጨው ከመንፈሳዊው ኃይል በመሆኑና የአላህ ፈጣን ምላሽ ድጋፍ እንደሚሆናቸው ስለሚታመን ከማኅበረሰቡ ውጪ ባለው የአካባቢው ኅብረተሰብ ጭምር ገናን የአስታራቂነት ክብር ሊያጎናጽፉቸው ችሏል፡፡ በዚህ ምክንያት የእነሱን ቃል ለማፍረስ የሚያስቡትን በሙሉ "አርፊህ ተቀመጥ አለበለዚያ ችግር ያጋጥምሀል" የማለት ኃይል አላቸው፡፡ የቃል ተረኩ በአስታራቂነት ያላቸውን ተቀባይነት ከማኅበረሰብ ድንበራቸው ማለፍን የሚጠቁም ብቻ ሳይሆን የማኅበረሰቡን ማንነት በመቅረጽ ሂደትም ሐይማኖታዊ ደጀን ያለው የበላይነት ስሜት እንዲፈጥሩ ረድቷቸዋል፡፡

### 4.2.3. ከእደጥበብ ሙያ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች

አርጐቦች ለእርሻ ሥራና ለቤት ውስጥ መገልገያ የሚያስፈልጓቸውን የብረታ ብረት እና የሸክላ ውጤቶች አይሰሩም፤ የብረትና የሸክላ ውጤቶችን የሚያገኙት ከገበያ ወይም በመንደራቸው ውስጥ "የከሰል መሬት[10]" የሚባል ቦታ ተሰጥቷቸው ከእነሱ ጋር እንዲኖሩ ከፈቀዱላቸው ሰዎች በግዥ ነው፡፡ አርጐቦች የብረታ ብረት እና የሸክላ ሥራ የማይሰሩበትን ምክንያት አስመልክቶ አሚኑ ኢድሪስ የሚከተለውን አጫውተውኛል፤ "አርጐቦች ብረታ ብረትና ሸክላ አይሰሩም፡፡ እነዚህን ተግባራት የሚያከናወኑ ሰዎች አይነ ወጊነት አለባቸው ይባላል፡፡ ይህም የሚመጣው ከዘር ነው፡፡ አዝመራ በሚደርስበት ወቅት 'እኔምሁን (አይናችሁን) ሰብስቡልን' ተብሎ ማኅበረሰቡን በሚያስተዳድረው ቃዲ ወይም ተወካይ አማካይነት ይነገራቸዋል፡፡ እነሱም አዝመራው ጥሩ ምርት እንዲሰጥ አይናቸውን ወደ እርሻው ከመጣል ይታቀባሉ (ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

የብረታ ብረትና የሸክላ ጥበብ ባለሙያዎችን አስመልክቶ ጥዩፍ አተያይ መያዝ በሌላው ማኅበረሰብ ዘንድም የሚታይ ቢሆንም በአርጐቦች ዘንድ ግን የማግለልና በአይነ ወጊነት የመፈረጅ ስሜት ብቻ አይደለም ወሰኑ፡፡ ይልቁንም ከተረኩ እንደምንረዳው አይነወጊዎች በሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን በሰብል ላይ ጉዳት ስለሚያደርሱ በማኅበረሰቡ ዘንድ ድርብ ጥላቻንና የበታችነትን አትርፌዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በዕደ ጥበብ ሙያዎቹ ላይ መሠማራት እንደ ቡዳ ልንቆጠር እንችላለን ከሚል ስጋትም ባሻገር ማንነትን የማጣትና የዘር ውርስ መንፈሳዊ እሴትን የመካድ ጠንካራ አቋምን የሚመለከት ጉዳይ

---

[10] የከሰል መሬት፡- የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ለመስራት የማይፈቅዱትን የዕደ ጥበብ ሥራ የሚሰሩ የተገለሉ ሰዎች (ፈላሻዎች) እንዲኖሩበት የተፈቀደ ገለልተኛና ለእርሻ ሥራ የማያገለግል ጠፍ መሬት ነው፡፡

ይመስላል፡፡ ሼህ መሀመድ ይህን ሀሳብ የሚጋሩት ቢሆንም "አይን" የሚባለውን ነገር ለማመንም ሆነ ላለማመን በጣም አስቸጋሪ መሆኑን አጫውተውኛል፡፡

> እርግጥ ነው የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የብረታብረትና የሸክላ ሥራ አይሰሩም። ብረት የሚሰሩ ፈላሻዎች ናቸው። "የከሰል መሬት" ተሰጥቷቸው ከአርጐቦች ጋር ይኖራሉ። ለአርጐቦችም በእጅ በእጅ ክፍያ ወይም በዱቤ ማረሻ፣ ማጭድ፣ ምሳርና የመሳሰሉትን ይሰሩላቸዋል። በዱቤ የሰሩላቸው ከሆነ ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት ገንዘቡን ይሰጧቸዋል። 'ከፈላሻ ጋር ያደረች ሴት ሰውነቷን ያሳክካታል፤ ጤነኛ አትሆንም' ይባላል። በዚህ ምክንያት የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ከእነሱ(ከፈላሻዎች) ጋር አንጋባም። አይን አለባቸው። በሚበላ ምግብ ላይ አይናቸው ካረፈ የሚመገበው ሰው ይታመማል። አይን የሚባለው ነገር የማይካድም የማይዋጥም ነው። ውሸት ነው እንዳንል 'እከሌ መጣብኝ' ወይም 'እከሊት መጣችብኝ' እያሉ ሲሞቱ ይታያል። እውነት ነው እንዳንል የሚወረወር የሚታይ ነገር የለም። በላ የተባለውን ሰው አግኝተን 'እንደዚህ አድርገሀል?' ስንለው ይደነግጣል። እሱ ራሱ ያደረገውን ነገር አያውቀውም። ይህ በጣም አስቸጋሪ የሆነ ነገር ነው (ሼህ መሀመድ፣ አንኮበር፣ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡



ሼህ መሀመድ አወል (አንኮበር)

ምንም እንኳን የብረታ ብረትና የሸክላ ሥራ ጥበበኞቹ ፈላሻዎች[11] ስለመሆናቸውም ሆነ እንዴት ወደ አርጐባ አካባቢ ሊመጡ እንደቻሉ ሼህ መሀመድ አወል ማብራራት ባይችሉም ገለልተኛ መኖሪያ (የከሰል መሬት) ተሰጥቷቸው የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት የማይሰሩትን "ጥዩፍ" ሥራ እየሰሩ መኖራቸውና በቡዳነት መፈረጃቸው በሰፊው እንደሚታመንበት መረዳት ይቻላል፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ በአሉታዊ ባህርያቸው የሚታወቁት እነዚሁ የተናቁ ወገኖች አይናቸው ለህመምና ለሞት የሚዳርግ፣ እንዲሁም አካላዊ ንክኪያቸው (መተቃቀፍ) ለእከክ የሚያጋልጥ በመሆኑ ለዝምድና በፍጹም እንደማይመረጡ ከተረኩ መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ከእነዚህ ወገኖች ጋር መዛመድ ቀርቶ

[11] ፈላሻ ማለት እንደ ሼህ መሐመድ አወል ገላፃ አገሩን ትቶ የመጣ ማለት ነው፡፡

በተጠቀሱት የዕደ ጥበብ ሥራዎች መሠማራት እንኳ የባህርይ መወራረስን እንዳያስከትል በጥብቅ እንደሚፈራ ሼህ መሀመድ አወል ያስረዳሉ፡፡

ይሁንና በእጅ ሙያተኛነት መሰማራት አይነ ወጊ ያደርጋል ብሎ ከማመን በመለስ በቡዳነት እንዳይፈረጁ የመስጋት አዝማሚያ ተጨማሪ መነሻ ሳይኖረው የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ራሳቸው አርጐቦች በዚሁ በጥብቅ በሚፈሩት አይነ ወጊነት የሚጠረጠሩበት ሁኔታም በተቃራኒው ኃይለኛ ተከላካይ እንዲሆኑ በማድረግ ራሳቸውን ከፍረጃው ነፃ የሚያወጡበት የሥነ-ልቡና ግፊት ፈጥሮባቸው ሊሆንም ይችላል፡፡ በዚህ ረገድ በሐረር አካባቢ የሚኖሩ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት "ቡዳ" ናቸው የሚባል ስም ስለተሰጣቸው ከአካባቢው ማኅበረሰብ የመገለል ሁኔታ እንደደረሰባቸው መነገሩ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ እንዳጫወቱኝ በሀረር አካባቢ የሚኖሩ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች አርጐቦችን ለጋብቻ ጠይቀዋቸው ፈቃደኛ ስላልሆኑ፣ "አርጐቦች ከእኛ ጋር የማይጋቡት ቡዳ በመሆናቸው ነው" የሚል አቋም መያዝ መጀመራቸው አልቀረም፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ አርጐቦች ቡዳ ናቸው የሚል ቅስቀሳ ተደርጐባቸዋል ይላሉ፡፡ የሐረር ግንብ ካሉት አምስት በሮች መካከል አንዱን "ቡዳ በር" በማለትም እስከመጥራት የተደረሰው በዚህ የተነሳ እንደሆነ ሼህ ዩሱፍ ይገልፃሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን "ቡዳ በር" የሚለው ስያሜ ተለውጦ "አርጐባ በር" ተብሎ በመጠራት ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በሐረር አካባቢ ለሚገኙ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የአካባቢው ኅብረተሰብ ጥሩ የሆነ አመለካከት የላቸውም፡፡ በዚህ የተነሳም በሌሎች ክልሎች የሚኖሩ አርጐቦች የሐረሮች እጣ እንዳይገጥማቸው በመስጋት ለሥራው ጥላቻ ያደረባቸው ይመስላል፡፡ እነሱ ከሚሰሩ ይልቅ በማኅበረሰቡ ዘንድ "ፈላሻ" በመባል ለሚታወቁት ሰዎች ሥራውን በመተው ራሳቸውን ከዚህ ፍረጃ ነፃ አድርገው መኖሩን መምረጣቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ስለእነዚህ ሰዎች ሼህ ዩሱፍ የሚከተለውን ነግረውኛል፤

> በአርጐባ ማኅበረሰብ ውስጥ የከሰል መሬት የሚባል ተሰጥቷቸው የእደ ጥበብ ውጤቶችን የሚሠሩ አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት አይደሉም፤ ይሁን እንጂ፣ ከአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ጋር ይኖራሉ፡፡ የእርሻ መሬታቸውን የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች አርሰው፣ አርመው፣ አጭደውና ወቅተው ምርታቸውን ጐተራ ያስገቡላቸዋል፡፡ አንድ ጥማድ በሬ ያለው ሰው 50 ኪሎ ግራም እህል ይሰጣቸዋል፡፡ አጥራቸውም ይታጠርላቸዋል፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ የተከበሩ ባይሆኑም ለሚሰጡት ጥበባዊ አገልግሎት ምላሽ የሚሆን እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡ እነርሱም ለአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ማረሻ፣ ማጭድ፣ ምሳር፣ ቢላዋ እና የሸክላ ውጤቶችን ይሠራሉ (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.)።

ይህ ቃል ተረክ አርጐቦች ስለራሳቸው ያላቸውን ግምት ከመግለጹም በላይ ከሌሎች ወገኖች ጋር ያላቸውን ግልጽ ልዩነት በሥራ ክፍፍል፣ በዘር ሐረግና በመኖሪያ ቦታ ጭምር አስምሮ የሚያሳይ ነው። የሥራ ክፍፍሉ የአጋጣሚ ሳይሆን ማንነትን በሚገልጽ መልኩ "የዘር ጥራትን" እና "ጉድለትን" እንዲያሳይ ሆኖ የተዘረጋ ነው። ዕደ ጥበብ የቡዳነት መገለጫ ሆኗል። ይህንን አባባል ሼህ መሀመድ ሲራጅ ያጠናክሩታል፣ "የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጅ ሆኖ ብረታ ብረት እና ሸክላ የሚሠራ ሰው የለም። ምክንያቱን በትክክል ባላውቀውም 'ብረት ቀጥቃጭ ነው፣ ሸክላ ሰሪ ነው' የሚባል ነገር አለ። እንደዚያ መባል ስለማይፈልጉ ነው ብረትና ሸክላ የማይሰሩት" (ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም)።

ሸክላን ወይም ብረት ሰሪነትን በሩቁ የመፍራቱ ጉዳይ ምንጩ በሼህ መሀመድ አለመታወቁ ምናልባት ከረዥም ጊዜ በፊት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ መምጣቱ ምክንያት መነሻው በዚህ ትውልድ በውል እንዳይለይ ስላደረገ ሊሆን ይችላል። ይህም የባለ እጅነት አይነ ወጊ መሆንን የሚያረጋግጥ አስተሳሰብ ሆኖ መወሰዱ ጥንታዊ መሰረት እንዳለው አመላካች ነው።

እዚህ ላይ አርጐቦች የእደ ጥበብ ባለሙያዎችን አይነወጊ እያሏቸው ለምን አብረዋቸው ይኖራሉ? የሚል ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይሆናል። የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ቡዳና አይነወጊ መሆናቸውን ምንም እንኳን አርጐቦች ቢያምኑም ከጉዳታቸው ይልቅ ጥቅማቸው ስለሚያመዝን አብረው መኖሩን ሳይፈልጉት አይቀርም፣ ወይም ከሰው ተፈጥሯዊ ኃይል በላይ ካላቸው ሰዎች ጋር መኖር ፈልገውም ይሆናል፣ አሊያም የሚያገኙትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ አስገብተው ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።

በከሚሴ ገበያ ያገኘኋቸው እና የእደ ጥበብ ሙያ እንዳላቸው የገለጹልኝ ሁሴን ከማል ራሳቸውን የአርጐባ ማኅበረሰብ አባል እንደሆኑ ያምናሉ። ከአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች መካከል እነሱ የተለዩ ሙያ ባለቤቶች እንደሆኑ በመግለጽ፣ በችሎታቸው በማህበረሰባቸውም ሆነ በሌሎች ኅብረተሰቦች ዘንድ የተከበሩ እንደሆኑ ይገልፃሉ (ግንቦት 14 ቀን 2004ዓ.ም.)። ይሁን እንጂ ይህ አባባል መረጃ ለመሰብሰብ በተንቀሳቀስኩባቸው የአርጐባ መንደር ነዋሪዎች ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው ለመገንዘብ ችያለሁ።

በአጠቃላይ አርጐቦች ማንነታቸውን ከሚገነቡባቸው መንገዶች መካከል አንዱ ራሳቸውን የእደ ጥበብ ሙያተኞች ጋር በማወዳደር ነው፡፡ ውድድሩም "እኛ" ከእነርሱ የተሻልን ነን በሚል ነው፡፡ "እኛ እንሻላለን" ሲሉ "እነርሱ" ከእኛ ያንሳሉ የሚል አስተሳሰብ ይፈጥራል፡፡ ለራሳቸው ካላቸው የላቀ ግምት የተነሳ ሌላውን አይነ ወጊ (ቡዳ) ወይም ፈላሻ በማለት አሳንሰው የማየት ሁኔታን ያንፀባርቃሉ፡፡ በዚህም ከሌሎች የተሻሉ መሆናቸውን በመግለጽ ማንነታቸውን ለመገንባት እየተጠቀሙበት ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 4.3. ከጀግንነት ጋር የሚገናኙ ተረኮች

### 4.3.1. ከሼህ ጦለሃ ጃእፈር ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች

በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ላይ የጭካኔ በትር ያሳረፈውን የአጼ ዮሃንስን አገዛዝ ለመጣል ከፍተኛ ተጋድሎ ካደረጉት መካከል ሼህ ጦለሃ ጃእፈር በግንባር ቀደምነት እንደሚጠቀሱ (ሐጂ መሀመድ፣ ሾንኬ፣ ግንቦት ቀን 2004 ዓ.ም.) ያስረዳሉ፡፡ ሼህ ጦለሃ ባሳዩት ጀግንነት በአርጐባ ማኅበረሰብ ዘንድ በታላቅ አርበኝነታቸው ይወሳሉ፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ በተንቀሳቀስኩባቸው የአርጐባ መንደሮች ስለአጼ ዮሃንስ ጭካኔ እና ስለሼህ ጦለሃ ጀግንነት የማይተርክ አላጋጠመኝም፡፡ ከሼህ ጦለሃ ጋር የቅርብ ዝምድና እንዳላቸው የገለጹልኝ ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ ስለሼህ ጦለሃ ጃእፈር የሚከተለውን ተርከውልኛል፤

> ሼህ ጦለሃ ጃእፈር ከአርጐባ የኃይማኖት መሪዎች መካከል ትልቁና ዋነኛው የሆኑት የዩሱፍ ወይም አባ ስያ የሚባሉት የልጅ ልጅ ናቸው፡፡ የተወለዱትም አሁን በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ተብሎ በሚታወቀው ዞን ስር በሚገኘው የአርጐባ ልዩ ወረዳ 02 ቀበሌ ጐጥ ስር ዋሻ በምትባል ቦታ ነው፡፡ ሼህ ጦለሃ ዕድሜያቸው ወደ 30 ዓመት አካባቢ ሲደርስ አፄ ዮሃንስ የተባሉ ንጉስ በኢትዮጵያ ነገሱ፡፡ በዚህ ወቅት 'ያላማተበ፣ ክርስቲያን ያልሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር አይችልም' ተባለ፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አንገቱ ላይ መስቀል ያለው ማተብ ማሰር አለበት አሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም በእስልምና እምነት ተከታዮች በተለይ ደግሞ በአርጐባ ማኅበረሰብ ላይ ከፍተኛ የሆነ እልቂትና መከራ ደረሰ፡፡ ቀደም ሲል "የእስላም ሀገሩ መካ፣ የወፍ ሀገሩ ዋርካ" የሚል ሀሳብ በፍትሃ ነገስት ላይ ተቀምጦ ነበር፡፡ ይህን አባባል ተፈፃሚ ለማድረግ "ሙስሊም ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር አይቻልም" የሚል አዋጅ ወጣ፡፡ ይህ ጉዳይ ሼህ ጦለሃ ጃእፈርን እንቅልፍ ሊያስተኛቸው አልቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት ጦር አደራጅተው በወቅቱ የደሴ አካባቢ የጦር መሪ ከነበሩት ከባላምባራስ በጀሮንድ ነውጤ ጋር ጦርነት ገጠሙ፡፡ የአፄ ዮሃንስ ጦር ከፍተኛና በሚገባ የተደራጀ ይሁን እንጂ፣ ሼህ ጦለሃ ጫካ ውስጥ ጉድጓድ ቆፍረው እሳር እያለበሱ የንጉሱ ሠራዊት አካል የሆነው የባላምባራስ በጀሮንድ ነውጤ ፈረሰኛ ጦር እየጋለበ ሲመጣ ጉድጓድ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ከፍተኛ ጥቃት አድርሰውበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰሜን ወሎ ውስጥ ራያና ወልዲያ

አካባቢ እንዲሁም ሰሜን ሸዋና ትግራይ ላይ ፊት ለፊት ጦርነት በመግጠም በአፄ ዮሃንስ ጦር ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት አድርሰዋል፡፡

ሼህ ጠለሃ ይንቀሳቀሱ የነበረው የእስልምና እምነት ተከታዮች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ስለሆነ ኅብረተሰቡ ከፍተኛ የሆነ ድጋፍና እርዳታ ያደርግላቸው ነበር፡፡ በተለያዩ ቦታዎች እየተንቀሳቀሱ በአፄ ዮሃንስ ጦር ላይ ጉዳት በማድረስ ለ14 ዓመት ያህል እንደተዋጉ በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ድርቅ ተከሰተ፡፡ በድርቁ ምክንያት ሠራዊታቸው ስለተበተነ መዋጋት በማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ፡፡ ከዚያም የተወሰኑ ተከታዮቻቸውን በመያዝ ወደ ሱዳን ሄዱ፡፡ በዚያን ወቅት በሱዳን ማህዲ የሚባል መሪ ነበር፡፡ ለማህዲ አፄ ዮሃንስ እስልምናን ለማጥፋት እየፈፀሙ ያለውን በደል በዝርዝር አስረዱት፡፡ እስልምናን ለማዳን ለ14 ዓመት ትግል ማካሄዳቸውንና ከውጪ አገራት ድጋፍ ማግኘት እንዳልቻሉም ገለጹለት፡፡

ማህዲም "እኛ እንረዳቸኋለን!" ብሎ ቃል ገባላቸው፡፡ ከዚያም ለ6 እና ለ7 ወራት ያህል ሱዳን እንደተቀመጡ ሼህ ጠለሃ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ጦራቸውን አደራጅተው ከ6 ወር በኋላ ወሎ አካባቢ ጦርነት እንዲጀምሩ ከማህዲ ጋር ተስማሙ፡፡ "እናንተ እዚያ ጦርነት ስትጀምሩ እኛ እንደርስላችኋለን" በማለት ነበር ማህዲ ያሰናበታቸው፡፡

ሼህ ጠለሃ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ድርቁ አልፎ ሰው ተረጋግቶ አገኙት፡፡ ጦራቸውን እያደራጁ ከቆዩ በኋላ በስድስተኛው ወር ላይ ደሴ አካባቢ ደረቅ ወይራ በሚባል ስፍራ ከባላምባራስ በጀሮንድ ነውጤ ጋር ጦርነት ጀመሩ፡፡ በጦርነቱም በርካታ ቤተ ክርስቲያኖችን አቃጠሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ባላምባራስ በጀሮንድ ነውጤ ሀይል እንዲጨመርላቸው ለአፄ ዮሃንስ ላኩባቸው፡፡ የአፄ ዮሃንስ ከፊል ጦር ባላምባራስ በጀሮንድ ነውጤን ለመርዳት ወደ ወሎ ሲጓዝ የማህዲ ጦር በመተማ አድርጐ ጐንደር በመግባት ከአፄ ዮሃንስ ዋና ሠራዊት ጋር ጦርነት አካሄደ፡፡ መንገድ ላይ የነበረው የአፄ ዮሃንስ አጋዥ ጦር ለበጀሮንድ ሳይደርስ ማህዲስቶች የአፄ ዮሃንስ ጦርን ድል ነስተው የንጉሱን አንገት በመቁረጥ ወደ ሱዳን ተመለሱ፡፡

ከአፄ ዮሃንስ ሞት በኋላ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ወደ ስልጣን መጡ፡፡ በዚህ ወቅት ሼህ ጠለሃ በአፋርና በኢሳ በኩል ከጅቡቲ አንድ ሺህ የሚጠጋ "ውጅግራ" የተሰኘ መሳሪያ በእርዳታ አገኙ፡፡ ባገኙት የጦር መሳሪያ በመበረታታት ጦራቸውን መልክሰዲ በሚባል ቦታ በአዲስ መልኩ አደራጅተው ለጦርነት መዘጋጀት ጀመሩ፡፡

በዚያን ጊዜ በመንግሥትም ሆነ በኅብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ተቀባይነት ያላቸው ሼህ ኑርዬ ኡመር የሚባሉ ሰው ነበሩ፡፡ እርሳቸውን አፄ ምኒልክ ፈለጓቸውና ወደ ቤተ መንግሥት ተጠርተው ሄዱ፡፡ አጼ ምኒልክ "እንደዚህ አይነት ችግር ገጥሞኛል፤ ይህን ደግሞ የምትፈቱት እናንተ ናችሁ" አሏቸው፡፡

ሼህ ኑርዬ ግን "ከዚህ በፊት መፍታት የሚገባን ሌላ ችግር አለ" ብለው መለሱ፡፡

አጼ ምኒልክ "ከጠለሃ ጋር ታረቅ አይበሉኝ እንጂ፣ ከዚህ ወጪ ከሆነ ምንም ችግር የለውም" አሏቸው፡፡

ሼህ ኑርዬ "እኔም የምፈልገው ይህንኑ ነው" የሚል መልስ ሰጡ፡፡

አጼ ምኒልክ "የጠለሃ የአባቱ እናት የእኛ ዘመድ ናት፡፡ እሱም ይህን ያህል ዓመት የተዋጋው የአባቱን እናት ስልጣን ለመውሰድ ነው ከእሱ ጋር እንዴት እታረቃለሁ? እኔ ስልጣን ለቅቄ? ወይስ ስልጣኔን አካፍየው ነው?" አሏቸው፡፡

ሼህ ኑርዬም "ጠለሃ እኮ የሚፈልገው ስልጣን አይደለም፡፡ ጭቃ ሹምነት እንኳን አይፈልግም፡፡ እሱ የሚፈልገው የኃይማኖት ነፃነት ነው፡፡ ፍትሃ ነገስት 'የእስላም ሀገሩ መካ ነው' ስለሚል በአፄ ዮሃንስ ዘመን ሙስሊሙ ኅብረተሰብ በሐይማኖቱ ሰበብ ከፍተኛ የሆነ ስቃይና መከራ አይቷል" በማለት አስረዱ፡፡

አጼ ምኒልክ "እውነት ነው ወይ?" ሲሏቸው፣

ሼህ ኑርዬም "አዎ" ብለው መለሱ፡፡

አጼ ምኒልክ "ይህ ነገር እውነት ከሆነ መክሬ መልሱን ነገ እነግረዎታለሁ" ብለው አሳደሯቸው፡፡ ከዚያም አጼ ምኒልክ ብልህ የሆነች ባለቤት ነበረቻቸውና ከባለቤታቸው ጋር ተማክረው አደሩ፡፡ ባለቤታቸውም ይህን ሀሳብ ስለደገፉት "የእስላም ሀገሩ መካ፣ የወፍ ሀገሩ ዋርካ" የሚለው አዋጅ ተሽሮ "ኃይማኖት የግል ነው አገር የጋራ ነው" የሚል አዋጅ ታወጀ፡፡ ይህ አዋጅ የእምነት ነፃነትን ከማስከበሩ በላይ በጊዜው የነበረውን ጦርነት፣ እልቂትና ስደት አስቀሟል፡፡ ይህ ትልቅ ብልህነት ነው፡፡ ሼህ ጠለሃ በዚህ ሁኔታ ከአጼ ምኒልክ ጋር ታርቀው እስከ አጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ የቆዩ ሲሆን በመጨረሻ ታመው ጣሊያን ከመምጣቱ በፊት አርፈዋል (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

አጼ ዮሃንስ 4ኛ የፀጋ፣ የሦስት ልደትና የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ተደምስሰው ሁሉም በተዋህዶ ክርስትና እንዲያምን ጽኑ የሆነ ፍላጐት እንደነበራቸው ይተረካል፡፡ በዚህ ምክንያት በተለይ በወሎ ሙስሊሞች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጭፍጨፋ ማካሄዳቸው በታሪክ ሰነዶች ተመዝግቧል፡፡ የኃይማኖት አንድነትን ለማስፈን በ1870 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሙስሊሞች ሁሉ እየተጠመቁ የተዋህዶ ክርስትናን እንዲቀበሉ አዘዙ (ተክለጻድቅ፣ 1982፣ 200)፡፡ ተዋህዶን ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆኑ ዜጐች መሬትና ንብረታቸውን በማስረከብ ከአገር እንዲወጡ አዝዘው ነበር፡፡ የትንባሆ ሱረት በአፍንጫው የሚጠጣ ወይም የትንባሆ ድፍድፍ በአፉ ቋጥሮ የሚመጥ አፍንጫውና ምላሱ እንዲቆረጥም አውጀዋል፡፡ በርካታ ሙስሊሞች በጭቃ ሹምና በመልከኛ እየተጐተቱ ወደ ቤተክርስቲያን ተወስደው በግድ እንዲቆርቡም ተደርገዋል፡፡ የፖለቲካ መሪ የነበሩትን መሀመድ አሊን እና አባ ዋጠውን ጨምሮ በርካታ ሙስሊሞች ከሚደርስባቸው ችግር ለማምለጥ ተጠምቀው ክርስትናን በመቀበል ቀን ለእግዚአብሔር ማታ ለአላህ ይፀልዩ ነበር፡፡ ሌሎች ስደትን መርጠው ወደ ጐረቤት ሀገሮች እና የንጉሡ ነገስቱ አስተዳደር ወደማይደርስባቸው አካባቢዎች ሲሸሹ፣ በርከት ያሉት ግን እንደ ሼህ

ጦለሃ በመሳሰሉ የኃይማኖት መሪዎች አደራጅነት እንዳመጹ (ባህሩ፣ 1989፣ 51-52፣ ተክለ ፃድቅ፣ 1982፣ 200) ያስረዳሉ፡፡

ሼህ ጦለሃ ለአርጐባ ማኅበረሰብ ህልውና የቆሙ ብቻ ሳይሆኑ ለመላው ህዝበ ሙስሊም በመቆም የትጥቅ ትግል ማድረጋቸውንና በመጨረሻም አሸናፊ ሊሆኑ መብቃታቸውን ከሼህ ዩሱፍ የቃል ተረክ መረዳት ይቻላል፡፡ የአርጐባ ማኅበረሰብ መሪና አርአያ የሆኑት ሼህ ጦለሃ የመላው ሙስሊም ኅብረተሰብና የኃይማኖት አዳኝና ጠባቂ የሚያደርጋቸውን ገድል ከመፈፀም ባሻገር በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የሙስሊም ህዝቦችንና አገሮችን በማስተባበር አካባቢያዊ ህብረት እስከ መፍጠር የደረሱ ሆነው ተስለዋል፡፡ የሼህ ጦለሃ የመሪነት ሚና በጦር ጀግንነት የተወሰነ ሳይሆን በዲፕሎማሲውም ከዳግማዊ ምኒልክና ከአፄ ኃይለስላሴ ጋር በነበራቸው ግንኙነት ተንፀባርቋል፡፡

አህመድ (1999፣ 110) በበኩላቸው አጼ ዮሃንስ 4ኛ የአፀኑትን የማጥመቅና ማተብ የማሳሰር ህግ መቀበል ለሼህ ጦለሃ ሐይማኖቱን የመክዳት ያህል ስለተሰማቸው፣ እስልምናን የህልውናቸው እና የማንነታቸው መገለጫ በማድረግ ከመቶ የማይበልጥ ጦራቸውን አስከትለው ወደ አፋር በርሀ በመውረድ በስርዓቱ ላይ የአመጽ ትግል የገለጹበት ታሪክ ሼህ ዩሱፍ ከተረኩት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሲሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ግን ተነካክቶ የታለፈ ይመስላል፡፡

ሼህ ጦለሃ ጃእፈር ለረጅም ጊዜ በረሀ በመቆየት በሺህ የሚቆጠር ሠራዊት አሰልፈው ወደ አሰብ፣ ከረንና ተሰነይ በመንቀሳቀስ ከዚያም በሱዳን ከሰላ ወደሚባል ስፍራ በመሄድ በሙስሊም ከሚመራ ጦር ጋር ተቀላቅለዋል፡፡ ከዚያም በፖሊሲው ላይ ካመጹ ሙስሊሞች ጋር በመሆን በተለያዩ አውደ ውጊያዎች ላይ በንቃት የተሳተፉ ሲሆን፣ የአጼ ዮሃንስ ጦር በመተማ ውጊያ እንዲሸነፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል (አህመድ፣ 1999፣ 111) ፡፡

የታሪክ ተመራማሪዎች ለአጼ ዮሃንስ መሸነፍ እንደ ምክንያት የሚጠቅሱት አሉላ አባ ነጋን ከጦር ጠቅላይ አዛዥነት ማንሳታቸው፣ ራሳቸው ደጀን በመሆን ከማዋጋት ይልቅ አምሳያ አሳሳች ሊቀመኳስ አዘጋጅተው በዋናው አውደ ውጊያ ማሰለፋቸው፣ እንዲሁም በእሳቸው ላይ ጉዳት ሲደርስ የሚተካቸው አልጋ ወራሽ አለማዘጋጀታቸውና የመሳሰሉትን ነው (ተክለጻደቅ፣ 1982፣ 543-544)፡፡ አርጐቦች ግን ለአጼ ዮሃንስ አገዛዝ መውደቅ ዋናው ምክንያት በእስልምና እምነት ተከታዮች በተለይ ደግሞ በወሎ

አርጐቦች ላይ ያደረሱት ግፍና መከራ ያስከተለው የተቃውሞ ትግል መጠናከር ነው ይላሉ፡፡

የሼህ ጦለሃ ሰራዊት ለአጼ ዮሃንስ መውደቅ ያደረገውን አስተዋጽኦ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ እንዲህ ይገልጹታል፤ "ከድርቡሽ ጦር ጐን ከወሎና ከወሎ አካባቢ፣ ከዋጅራት፣ ከራያና አዘቦ፣ እየሸሸ የሄደው በሼህ ጦለሃ ቤን ጃእፈር መሪነት የቀረውም ከወዲህ ከኢትዮጵያ ሰሜንና ሰሜን ምዕራብ፣ ከቦጐስና ከቤኒ አሚር በነአህመድ ኤልጅር፣ በነዳግላል መሀመድ እየተመራ ግማሹ ወደ ኢጣሊያ ሲጠጋ የቀረው ወደ ድርቡሾቹ ተደባልቆ ኃይላቸውን አጠናክሮላቸዋል"(1982፣ 538)፡፡ ከተክለጻድቅ ማብራሪያ መገንዘብ እንደሚቻለው ሼህ ጦለሃ ለአጼ ዮሃንስ አገዛዝ መውደቅ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱበትን የአውደ ወጊያ ተሳትፎ ጉልህነትና ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎችም ሰፊ የሰው ኃይል አሰባስበው የተጠናከረ ኃይል ፈጥረው የነበሩ መሆናቸውን ነው፡፡

አጼ ዮሃንስ የኃይማኖት ነፃነትን ባለማክበራቸው ህይወትን የሚያህል ዋጋ የከፈሉ መሆናቸውን መረዳት ሲቻል በእምነታቸው ምክንያት የተገፉ ዜጐች ከወራሪ ኃይል ጋር እስከ መተባበር የደረሰ በአገሪቱ ዜጐች ዘንድ እምብዛም ያልተለመደ አቋም ሊይዙ በቅተዋል፡፡ በተለይም በአርጐቦች ዘንድ የተፈጠረው የተቃውሞ እንቅስቃሴ የማኅበረሰቡን የመኖሪያ አካባቢ ለደህንነት ስጋት በማይፈጥር የተራራ ጫፍ እንዲወሰን ያስገደደ ይመስላል፡፡

ሼህ ጦለሃ ጃእፈር በአጼ ዮሃንስ ዘመነ መንግሥት ወቅት ለእስልምና ኃይማኖት እኩልነት ያደረጉት ተጋድሎ በአርጐቦች ዘንድ የማኅበረሰቡ ታሪክና ማንነት ዋነኛ አካል ሆኖ ይተረካል፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ጉልህ ስፍራ የተነፈጉትና በማኅበረሰቡ ዘንድ ከተወዳጅነትም በላይ ዘመን ተሻጋሪ ተጽዕኖ በመፍጠር የማንነቱ መለያ ተደርገው ስለሚጠቀሱት ሼህ ጦለሃ ጃእፈር መሀመድ ያሲንም የሚከተለውን ተርከውልኛል፤

> የክርስትናን ኃይማኖት ያልተቀበለ ኢትዮጵያን ለቆ ይሂድ የሚል አዋጅ ያወጡት አጼ ዮሃንስ በነገሱበት ዘመን ጌታው ጦለሃ ወሎ አርጐባ ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ የአርጐባ ተወላጆችን ሰበሰቡና "ቆርባችሁ ክርስቲያን ሁኑ እየተባለ ነው፤ ምን ይሻለናል?" ይሏቸዋል፡፡ በዚህን ጊዜ "በሐይማኖታችን ከመጣ ሴት ወንድ ሳንል እንዋጋለን" የሚል ምላሽ ያገኛሉ፡፡ ይህን ሲያደርጉ የአፄ ዮሃንስ ሁለት ሰላዮች ሰምተው ኖሮ ሄደው ለጌታቸው ይናገራሉ፡፡ አፄ ዮሃንስ ጦራቸውን ይዘው በመምጣት ወሎ አርጐባ አካባቢ ይሰፍራሉ፡፡
>
> በመቀጠልም የአርጐባ ተወላጅ የሆነ በሙሉ እንዲመጣ ትዕዛዝ ይሰጣሉ፡፡ ጌታው ጦለሃ ቃል የገቡትን የአርጐባ ተወላጆች ሰብስበው "ምን ይሻለናል?" ይሏቸዋል፡፡ ተወላጆችም

"እኛ መሳሪያ የለንም፡፡ ያለነው ባዶ እጃችንን ነው፡፡ ኃይላችንም የማይረባ ነው፤ ስለዚህ 'እሺ' ብለን ክርስትናን እንቀበልና ውስጥ ውስጡን የራሳችንን ኃይማኖት እናራምድ" የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡

ጌታው ጦለሃም "ያኔ ምን ነበር ያላችሁት? 'በአፈር በቅጠሉም ቢሆን እንዋጋለን' አላላችሁም ወይ?" በማለት ያፋጥጧቸዋል፡፡ በኋልም ወጣቶችን ለይተው በመሰብሰብ "እንዴት ነው ሲሏቸው?" ወጣቶችም፣ "አንቱ እንዳሉ" ይሏቸዋል፡፡ "እንግዲያውስ ባለን መሳሪያ እንግጠም" የሚል ስምምነት ላይ ይደርሳሉ፡፡

በጌታው ጦለሃ መሪነት ወጣቶች ሲዋጉ ጥቂት በመሆናቸው ዙሪያውን ይከበባሉ፡፡ ከዚያም ይማከሩና እጅ ከመስጠት ማምለጥ እንሚሻል ወሰኑ፡፡ "እኔን ተከተሉኝ" በማለት ሰልለው የአፄ ዮሃንስ ጦር በሳሳበት በኩል እየተዋጉ ሰብረው አመለጡ፡፡ ከዚያን ቀን በኋላ እያደፈጡ በአጼ ዮሃንስ ጦር ላይ አደጋ ማድረስ ጀመሩ፤ ብዙ ጊዜም ፊት ለፊት ተዋግተው ድል አድርገዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ረጅም ጊዜ ከቆዩ በኋላ አፄ ዮሃንስ በኃይማኖት ሰበብ አንገታቸው ተቆርጦ ተገደሉ፡፡

አፄ ምኒልክ ንጉሰ ነገስት ተብለው ሲነግሱ "ኃይማኖት የግል ነው፤ ሀገር የጋራ ነው" ብለው አወጁ፤ "ጦለሃም የፈለገውን እናደርግለታለን፤ ይግባ" አሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ጌታው ጦለሃ ከአጼ ዮሃንስ ሠራዊት ጋር ጦርነት በመግጠም ሲዘርፉ፣ "ዘረፋው የእስልምና ኃይማኖት በሚያዘው መንገድ ይሁን" ሲሉ ተከታዮቻቸው ሊቀበሏቸው ስላልቻሉ ይናደዱ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ አጼ ምኒልክ የእርቅ ጥያቄ ሲያቀርቡላቸው ለመደራደር ፈቃደኛ ሆኑ፡፡ ሰራዊታቸው ባያበሳጫቸው ግን ለመታረቅ አይፈልጉም ነበር ይባላል፡፡

ጦለሃም "እኔ ሹመት አልፈልግም፤ የምፈልገው ሐይማኖቴ እንዳይነካ ነው፡፡ ቀደም ሲል የክርስትና ኃይማኖትን ተከተሉ የሚል አዋጅ ታውጇል፡፡ አሁን ደግሞ 'ኃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው' የሚለው አዋጅ በየገበያው ይታወጅ፣ አለበለዚያ አልገባም" አሉ፡፡ አፄ ምኒልክም በየገበያው እንዲታወጅ አደረጉ፡፡ ከዚያ በኋላ ከአፄ ምኒልክ ጋር እርቅ አድርገው ገቡ፡፡ ሰፊ መሬትም ተሰጣቸው፡፡ ከዚያ በኋላ በሰላምና በደስታ እስከ አፄ ኃለስላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ ኖረው ሞቱ (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋ ሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡



ሼህ መሀመድ ያሲን (ሸዋሮቢት)

ሼህ ዩሱፍ አቀራረብ የተሻሉ ዝርዝር ጉዳዮችን በመያዙ በተወሰነ መልኩ
ሲሆን፣ በአጼ ዮሃንስ ጦር ተከበው የመደምሰስ አደጋ ሲጋረጥባቸው ሽሽትን
የማድረጋቸውን ገለጻ እናገኝበታለን፡፡ ምናልባትም ሌሎቹ የመረጃ አቀባዮቹ
ለሃን ሽንፈትና ሽሽት መጥቀሱ የማኅበረሰቡን የማንነት ሥነ-ልቡና የገነቡበትን
ት ታሪክ የሚያዳክም እንዳይሆንባቸው በመስጋት ሊሆን ይችላል የዘለሉት፡፡
ስለዚህ ጉዳይ በቂ መረጃ እንደሌላቸው ስለገለጹልኝ በከፊል የመረጃ እጥረት
የትነት ሊጠቀስ ሲችል፣ የእርሱም የመረጃ ምንጮች በተመሳሳይ ሁኔታ
ና ሽንፈት ጉዳይን ማንሳት አለመፈለጋቸውን የሚያመለክትም ይሆናል፡፡
ቸው መንስኤ በርግጥ በተረኩ በሚገባ የተገለጸ ሲሆን፣ መቶ የማይሞላ ጦር
ቸውን በቂ የጦር መሳሪያ አለመታጠቃቸውን ሽሽታቸውን እንኳን ተቀባይነት
የጀግንነት ተግባር አድርገን እንድንቀበል የሚጋብዝ አንድምታ አለው፡፡ የሼህ
የጀግንነት መንፈስ የበለጠ ጐልቶ የሚታየውም ብዙኃኑ የማኅበረሰቡ አባላት
ላ ክርስቲያን የመሆን ሀሳብ ሲያቀርቡላቸው ጥቂት ወጣቶችን ብቻ አስልፈው
ትግል መሰለፋቸውን ስንገነዘብ ነው፡፡ ሼህ ጦለሃ በቂ ድጋፍ ባልነበራቸው
እንኳ ለኃይማኖት ነፃነታቸው ምን ያህል ጠንካራ አቋም እንዳላቸው በመግለጽ
ረሰቡ መታወቂያ የሆነው የእስልምና ኃይማኖት የተከፈለበትን መስዋዕትነትና
ረሰቡም ከዚሁ ኃይማኖት ጋር ያለውን የጠበቀ ትስስር የሚያሰርጽ ተረክ ነው፡፡

ቸውን ጽናትም ለአጼ ዮሃንስ አሳልፈው ለሰጧቸው አሲረው ለነበሩት የገዛ
ቸው ሳይቀር አሳይተዋል፡፡ "ሁለት መቶ ሃምሳ ወታደሮች በመያዝ ወደ
ዎች መንደር ገሰገሱ፡፡ የአሳልፎ መስጠት ውሳኔ ያደረሱትን የአዋቂ አጥፊዎች
ደት የኃይል እርምጃ ወስደው ወደ በረሀው ተመለሱ (አህመድ፣ 1999፣ 110)፡፡
መልኩ ለእስልምና ኃይማኖት መጽናት ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱት ሼህ ጦለሃ
ሎቦች ዘንድ የተለየ ቦታ አላቸው፡፡ የማኅበረሰቡ አባላት እነዚህን ተረኮች
ርቡ ቢያንስ በሦስት መንገዶች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በአንድ በኩል ሌሎች
ረሰቦች ከሚያደርሱባቸው ሥነ-ልቡናዊ ጫና ለማምለጥ ይረዳቸዋል፡፡ በሌላ በኩል
የሼህ ጦለሃን ጀግንነት በማሳየት ወጣቱ ትውልድ ቆራጥና የዓላማ ጽናት
ኖረው የማስተማር ኃይል አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የእስልምና ኃይማኖትን
በረሰቡ ማንነት ጋር በማስተሳሰር ፀንቶ እንዲዘልቅ ያጠናክሩበታል፡፡ ከላይ
ለጸው ተረክ ላይ በአባታቸው በኩል የጦለሃ ሴት አያት የአጼ ምኒልክ ዘመድ
ናቸው ሰፍሯል፡፡ ይህም የአርጐባ ማኅበረሰብ የገዥ መደብ ታሪክ እንዳለውና

የነገስታት የትውልድ ሐረጉ ከጥንት ጀምሮ እየቀጠለ መምጣቱን የሚያስረዳ የቅርብ ዘመን ተጨማሪ የታሪክ ማጣቀሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህንን የቃል ተረክ በማጠናከር የሼህ ጦለሃ አያት የአፄ ምኒልክን የእህት ልጅ ሳይቀር ማግባታቸውን ሼህ ዩሱፍ ተርከውልኛል፡፡

አጼ ምኒልክ ይኖሩ የነበረው በአንኮበር ነው፡፡ አንኮበርና አልዩ አምባ ደግሞ ያላቸው ርቀት 15 ኪሎ ሜትር ነው፡፡ አባስያ ከዚህ (መዲና) ተነስተው ወደ አልዩ አምባ ይሄዳሉ፡፡ አባስያ ማለት የጦለሃ አያት ናቸው፡፡ አባስያ ወደ አልዩ አምባ በሄዱበት ወቅት የአፄ ምኒልክ የእህት ልጅ የአልጋ ቁራኛ ሆና ትኖር ነበር፡፡ ይህች ልጅ በጣም የምታምርና ቆንጆ ስትሆን፣ ከ12 ዓመቷ ጀምሮ አጋንንት ስለሰፈረባት መንቀሳቀስም ሆነ መናገር አትችልም ነበር፡፡ በእሷ ህመም ምክንያት ቤተሰቦቿና ዘመዶቿ በጣም ተሰቃይተዋል፡፡ ከያዛት አጋንንት ለማላቀቅ በርካታ ቀሳውስትና ደብተራዎችን ጥረት አድርገው የነበረ ቢሆንም ሊሳካላቸው ግን አልቻለም ነበር፡፡

በወቅቱ አባስያ በጣም የሚፈሩና የሚከበሩ ሰው ይሁኑ እንጂ፣ እምብዛም ወደ ቤተ መንግሥት የሚጠጉ አልነበሩም፡፡ የአባስያን አልዩ አምባ መምጣት የሰሙት ምኒልክ መላክተኛ ልከው አስጠሯቸው፡፡ አባስያ አንኮበር ሲመጡ ምኒልክ የእህታቸው ልጅ ስላለችበት ሁኔታ በመግለጽ ፀሎት እንዲያደርጉላት ፈልገው እንዳስጠሯቸው ገለጹላቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ልጅቱ 18 ዓመት ሞልቷት ነበር፡፡ አባስያም ልጅቱ ወዳለችበት ቤት በመሄድ ፀሎት ያደርጉላታል፡፡ ፀሎታቸውን ሲጨርሱ በዚህ ውሀ እጠቧት በማለት አረፍ አሉ፡፡ ልጅቱ በውሀው እንደታጠበች በሚገርም ሁኔታ መራመድና መናገር ጀመረች፡፡

በዚህ በረከታቸው የተደነቁት ምኒልክ "አባስያ! ምን እናድርግልህ?" በማለት ጠየቋቸው፡፡ አባስያም "ምንም ነገር አልፈልግም፣ ነገር ግን ልጅቱን ለእኔ ስጡኝ" በማለት መለሱላቸው፡፡ ምኒልክም እንቢ እንዳይሉ ፈሩ "ምን ይደረጋል?" በማለት ሰጧቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ሁለቱ ተጋብተው ስምንት ልጆችን ወለዱ፡፡ ከልጆቻቸው መካከል ዞቢር፣ ጃቤር፣ ሽሪፍ፣ ሶፊያ፣ ሩቅያ… የሚባሉ ይገኙባቸዋል፡፡ ሩቅያ የምትባለው የአባ ስያ ልጅ ከሼህ ጦለሃ ጃእፈር ጋር ለጦርነት ጐንደር ሄዳ አግብታ ለረጅም ጊዜ እዚያ ኑራለች፡፡ የእሷ ልጆችና የልጅ ልጆች ጐንደር ከተማ እስከ ቆላድባ ድረስ ባሉት ከተሞች ይገኛሉ፡፡ የኋላ ኋላ ወደ እዚህ (መዲና አርጐባ) ተመልሳ ለተወሰነ ጊዜ ከቆየች በኋላ ሞታለች፡፡ መቃብሯም እዚህ ይገኛል (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

ተረኩ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላትን ንጉሳዊ የትውልድ ሐረግ ትስስር ብቻ በመግለጽ አይወሰንም፡፡ ይልቁንም በዚሁ የጋብቻ ዝምድና ውስጥ የኃይማኖት ጽናታቸውንና የበላይነታቸውን ጭምር በኩራት የሚያሳዩበት ሆኖም እናገኘዋለን፡፡ ለበርካታ ቀሳውስትና ደባትር ያልተበገረው አጋንንት በአባስያ አጭር ፀሎት ምክንያት መንበርከኩ ከእምነቱ ያገኙት ፀጋና ኃይል መሆኑን በመግለጽ የሐይማኖቱን ትክክለኛነት ወይም ከሌላው እምነት የተሻለ መሆን ማመልከቻ አድርገው

ተጠቅመውበታል፡፡ ሌላው ቀርቶ ምድራዊው ኃያል ንጉሰ ነገስቱ እንኳ የጋብቻ ጥያቄውን በእንቢታ ለመግፋት ፍርሀት እስከማሳደር ያደረሰው ተጽዕኖ ፈጣሪነታቸው መነሻው መለኮታዊ ኃይል መሆኑን እንረዳለን፡፡ በሌላ በኩል የአርጐቦችን የነገስታት ዝርያ የሚያጠናክር የቃል ተረክ የሚያቀርቡት ሼህ መሀመድ ያሲን የአርጐባ ሴቶች ቁንጅና የነገስታትን የጋብቻ ጥያቄ በተደጋጋሚ እንደሚጋብዝ ያብራራሉ፡፡ እንደእርሳቸው ገለፃ የአርጐባ ሴቶች በጣም ቆንጆዎች ናቸው፡፡ በቁንጅናቸው ምክንያት አጼዎች ለእቁባትነት እያስገደዱ ይወስዷቸው ነበር፡፡ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ አባት፣ የራስ መኰንን እናት በእቁባትነት የሄዱ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጅ ናቸው ይባላል፡፡ የኢትዮጵያ ነገስታት በሙሉ የአርጐባ ተወላጆች እንደሆኑም አያቶቻችን ይናገራሉ፡፡ (ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

# ክፍል አምስት

## 5. ማጠቃለያ

የአርጐባ ማኅበረሰብ ዝርው ትረካዎች የማኅበረሰቡን ማንነት፣ ሥነ-ልቡናና የአኗኗር ዘይቤ በመገንባት ረገድ ከፍ ያለ ሚና እንዳላቸው ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰቡት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዋነኛነት የማኅበረሰቡ አባላት በተራራ አካባቢ የመኖራቸውን ምስጢር፣ የመተዳደሪያ ሥራቸውን ምንነት፣ ከታላላቅ የእስልምና መሪዎችና የተቃውሞ ትግል ፋናወጊዎች ጋር ያላቸውን ትስስር፣ እንዲሁም ከመካከለኛው ምስራቅ ፈልሰው በመምጣት ዝርያቸውን በማበራከትና ኃይማኖታቸውን በማስፋፋት ያደረጉትን ጥረት በመተረክ የማኅበረሰቡን ማንነት የማጽናትና የማስረጽ ሙከራ ያደርጋሉ፡፡

ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡትን መረጃ መሰረት በማድረግ በተሰጠው ትንታኔ መሰረት አርጐባ የሚለው ስያሜ አመጣጥ ተደርጐ በማኅበረሰቡ አባላት ዘንድ በብዛት የሚተረከው “አረብ- ገባ” ከሚለው የመጣ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አርጐባ የሚለው ቃል ከአገር ስም፣ ከቋንቋው እና ከእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች መጠሪያ ጋር የተያያዘ እንደሆነ መረጃ ሰጭዎቹ ያስገነዝባሉ፡፡ የማኅበረሰቡን አባላት ጥንተ አመጣጥ በተመለከተም ነብዩ መሀመድ የነብይነት ማዕረግ አግኝተው በመካ ለሚገኘው ህዝብ የእስልምናን ኃይማኖት እንዲቀበሉ ጥሪ ካደረጉበት ዘመን ጋር ያያይዙታል፡፡ ጥሪውን መስማት ያልፈለጉት የመካ ቁረይሾች ሲያሳድዷቸው ነብዩ መሀመድ ተከታዮቻቸውን ለመታደግ ሲሉ ወደ ሀበሻ ምድር እንዲሄዱ በመከሯቸው መሰረት ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው በብዙዎቹ ዘንድ ይታመናል፡፡ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ አርጐቦች ከውጭ አገር የመጡ ባዕዳን እንደሆኑ የሚነገረውን እውነታ ሳይስቱ ነገር ግን የመጤነትን አሉታዊ ገጽታ በሚያዘናጋ ሁኔታ የዘራቸውን ምርጥነት በመግለጽ የማኅበረሰቡን ሥነ- ልቡና ለመገንባት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በአጭሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት መጠሪያቸውን እንዴት እንዳገኙ፣ ከየት፣ መቼና ለምን እንደመጡ ያላቸውን አመለካከት የማሳየት ፋይዳ አላቸው፡፡

አርጐቦች በተራራ(ጉባ) ላይ ለመኖራቸው በምክንያትነት የሚጠቀሰው ራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል አመች በመሆኑ ሲሆን፣ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች ለመሰራጨታቸው የሚያቀርቡት ምክንያት ደግሞ የኃይማኖት ትምህርት ለማስተማር፣

በንግድ፣ እና አገር ለማስተዳደር እንደሆነ ብዙዎቹ እምነት አላቸው:: በዋናነት ሰፍረው የሚገኙበትን የሰሜን ሸዋ አካባቢ ለመኖሪያነት የመረጡትም የአገሪቱ ማዕከላዊ ቦታ በመሆኑ ለአስተዳደር እና ለንግድ ሥራ ባለው አመችነት መሆኑን ከቃላዊ ዝርው ተረኮቹ መገንዘብ ተችሏል::

የማኅበረሰቡ አባላት ከራሳቸው ዘር ውጭ የማያገቡትም እነርሱ የቁረይሽ ጐሳ አባል በመሆናቸው ምርጥ ዘር አለን ብለው ስለሚያስቡ ከሌላ ዘር ጋር በመቀላቀል "ጥራቱን" እንዳያጡ በመስጋት ነው:: ይኸው የዘራቸውን ታላቅነት የሚገልጹ የተለያዩ አመለካከቶችም በቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው ውስጥ በብዛት ይታያሉ:: በዚህም አርጎቦች ዘራቸውን ጠብቀው ለመኖር ተረኮቻቸው ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ እያበረከቱ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል::

አርጎቦች ግጭቶች ሲያጋጥሟቸው እልባት እንዲያገኙ የሚያደርጉት በረከቦቶቻቸው አማካይነት ነው:: ረከቦቶች ከራሳቸው ማኅበረሰብ በተጨማሪ አፋሮችን፣ ኦሮሞዎችን እና አማራዎችን ያስታርቃሉ:: የማኅበረሰቡ ተረኮች ረከቦቶቻቸው በፍራቻና በጥቅም እንደማይደለሉ በመግለጽ በአርጎቦችና በሌሎች ማኅበረሰቦች ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት ከፍ እንዲል አድርገዋል:: በዚህም ምክንያት በረከቦቶች የታረቀ ሰው ካሳ አልከፍልም ወይም ቂም ይዞ ልበቀል አይልም:: ከእነሱ ቃል ለመውጣት የሚያስቡትን አርፊህ ካልተቀመጥክ ችግር ይገጥምሀል የማለት ኃይል እንዳላቸው መረዳት ተችሏል::

በአርጎባ ማኅበረሰብ ዘንድ ብረታ ብረት እና የሸክላ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች እንደ አይነወጊ ይቆጠራሉ:: አይነወጊዎች በሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን በሰብል ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብሎ ስለሚታመን በማኅበረሰቡ ዘንድ በክፉ ይታያሉ:: በዚህ ምክንያት አርጎቦች የብረታ ብረት ሆነ የሸክላ ሥራ ብንሰራ እንደ ቡዳ ልንቆጠር እንችላለን ከሚል ስጋት በመነጩ እነዚህ የእደ ጥበባት ሥራዎችን አይሰሩም:: ይህ አስተሳሰባቸው በወጣቱ ትውልድ ላይ እንዲሰርጽ በማድረግ እና በወጣቱ ትውልድ ላይ ጫና በማሳደር ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ላቅ ያለ ሚና አላቸው::

አጼ ዮሃንስ በእስልምና እምነት ተከታዮች በተለይ ደግሞ በወሎ አርጎቦች ላይ ያደረሱት ግፍና መከራ ለማስቆም ለበርካታ ዓመታት በዱርና በገደል የታገሉት ሼህ ጦለሃ ጃእፈር ለአርጎቦች የማንነታቸው ማሳያ መስታወት ሆነው ቀርበዋል:: ከእሳቸው የቃል ተረክ ወጣቱ ትውልድ ጀግንነትንና የዓላማ ጽናትን እንዲማር የመስበክ ተግባር ይዘዋል::

የአርጐባ ሴቶች ቆንጆ በመሆናቸው አጼዎች በእቁባትነት አስገድደው ይወስዷቸው ነበር፡፡ በዚህ መሰረት የቀዳማዊ ኃይለስላሴ አባት፣ የራስ መኰንን እናት በእቁባት የሄደች የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጅ እንደሆነችና በአመዛኙ የኢትዮጵያ ነገስታት የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች እንደሆኑ ከቃላዊ ዝርው ተረኮቹ መረዳት ይቻላል፡፡ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ከአጼ ምኒልክ ጋር ያላቸው የዘር ግንኙነት በተረኮቹ መገለጹም የማኅበረሰቡን የትውልድ ሐረግ ከገዥው መደብ ጋር የሚያስተሳስር ምሳሌ በመሆን ማኅበራዊ የበላይነቱን የማስረጽ ሚና እንዳላቸው አመላካች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የአርጐባ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከማኅበረሰቡ አኗኗር፣ እምነትና የትውልድ ሐረግ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ እነዚህ ተረኮች የማኅበረሰቡን አመጣጥ፣ ዘር፣ አሰፋፈር እና ጀግንነትን ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚገልጹ እና ከእደ ጥበብ ሙያ ጋር የተያያዙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ተረኮቹ ስለ ማኅበረሰቡ ማንነት በመግለጽ ረገድ ከፍተኛ የሆነ ፋይዳ አላቸው፡፡ በመሆኑም ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የማኅበረሰቡ የማንነት መሰረት ስለሆኑ በጥንቃቄ ይጠብቋቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት እስካሁን ድረስ ሊተረኩ መቻላቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

## ሀ. የአማርኛ ምንጮች


ለማ ንጋቱ፡፡ "በየም ማኅበረሰብ ዖታ ተኮር ተረኮች የወንድና የሴት ምስል ትንተና፡፡" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999 ዓ.ም.፡፡

ሙሀመድ ሳኒ ሐቢብ፡፡ የታላቁ ነብይ የመሀምድ ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1982 ዓ.ም.፡፡

ማን ያለው አባተ፡፡ "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማኅበራዊ ፋይዳቸው፡፡" በኢትዮጵያ ቋንቋ እና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1999 ዓ.ም.፡፡

ምንዳ ገብሬ፡፡ "የጌዲኦ ልማዳዊ ስርአትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ባህሩ ዘውዴ፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966፡፡ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1989፡፡

ቡሽራ ሸኽ ያሕያ፡፡ የሰይድ ኣህመድ ነጋሽ ታሪክ፡፡ ትግራይ፣ (የታተመበት ማተሚያ ቤት አልተገለጸም)፣ 2000 ዓ.ም.፡፡

ብርሃኑ ድንቄ፡፡ የኢትዮጵያ አጭር ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1941 ዓ.ም.፡፡

ተስፋዬ ኃይሉ፡፡ "የሶሺዮ- ካልቸራል ጥናት በአርጐባ ማኅበረሰብ፡፡" በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1991 ዓ.ም.

ተሾመ ብርሃኑ፡፡ ኢማም አህመድ ኢብራሂም፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ. ማህበር፣ 2000፡፡

ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ፡፡ ዐፄ ዮሃንስና የኢትዮጵያ አንድነት፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1982፡፡

________:: የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ኑብያ-አክሱም ዛጉዬ እስከ ዓጼ ይኹኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት:: አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1946::

________:: የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ስላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1965 ዓ.ም.::

________:: የግራኝ አህመድ ወረራ:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ስላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1966 ዓ.ም.::

ቴዎድሮስ ገብሬ:: በይነ-ዲሲፕለናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ:: አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2001 ዓ.ም.::

ነጋሽ መሀመድ:: "አርጐብኛና የአርጐቦች ህይወት በሁለት (አልዩ አምባና አዋሽ) ከተሞች ውስጥ::" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1981 ዓ.ም::

አለቃ ታየ ገ/ማርያም። የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ። አዲስ አበባ፣ ሴንተራል ማተሚያ ቤት፣ 1964 ዓ.ም.::

አቢዩ አስማማው:: "የአርጐባ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፣ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ፣ አርጐባ ልዩ ወረዳ::" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2000 ዓ.ም::

አህመድ መሀመድ:: የአርጐባ ሕዝብ የመነሻና የማንነት ግንዛቤ:: አዲስ አበባ፣ 1999 ዓ.ም.:: (የታተመበት ማተሚያ ቤት አልተገለጸም)

አህመዲን ጀበል:: ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ከ615-1700 የጭቆናና የትግል ታሪክ:: አዲስ አበባ፣ መረዋ ማተሚያ ቤት፣ 2003 ዓ.ም.::

አማረ ሞላ:: "የሽክቾ ብሄረሰብ ሀገረ ሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና::" በኢትዮጵያ ቋንቋ እና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1999 ዓ.ም::

አብርሃም ዓለሙ:: "የስነቃል ጥናት በኢትዮጵያ::" በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነጽሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1995 ዓ.ም::

አክሊሉ አስፋው፡፡ "የአርጐባ አጭር ታሪክ፡፡" በአርኪዎሎጂና አንትሮፖሎጂ መምሪያ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1991 ዓ.ም.፡፡

ከሁሉም በላይ "የነገደ ወይጦ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች፡፡" በኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2003 ዓ.ም፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡ የአማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ፡፡ ስድስተኛ እትም፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1996 ዓ.ም.፡፡

ወልደ ስላሴ አቡቴ፡፡ "የስነቃል ግንዛቤ፣ ባህርይና ጠቀሜታ፡፡" የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ መጽሄት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1979፣ ቅጽ7፣ ቁጥር 2፣ ገጽ 3-15፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን፡፡ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992 ዓ.ም.፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ጥናት ምርምር ማዕከል፡፡ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1993 ዓ.ም.፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ የሥነቃል መምሪያ፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጻሕፍት ማዕከል፣ 1991 ዓ.ም፡፡

________፡፡ "የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ስነቃል ጥናት ቅኝት፣ እና ግምገማ፡፡" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የስነጽሁፍ መጽሔት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1996፣ ቁጥር 6፣ ገጽ 3፡፡

## ለ. የእንግሊዝኛ ምንጮች

Aberaham, Alemu. "Jimma Oromo Oral Prose Narrative: A Preliminary Descriptive Analysis." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, Unpublished, 2000.

Abdul Kadir, Haji Jama "Some Cultural elements reflected in Somali Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, Unpublished, 1982.

Aklilu Asfaw. "A short history of the argobaba." http://www.persee.fr/web/revues/home/prescript/article/ethio_0066-2127_2000_num_16_1_973

Anna, De Finna. Identity in Narrative: a Study of Immigrant Discourse. Amsterdam /Philadelphia, John Benjamin's publishing, 2003.

Bascom, William R "The forms of folklore: prose Narrative." Journal of American folklore, vol. 78, No 307 published by American folklore society. (Jan-Mar 1965)

Bayileyegn Tasew. "Anyuaa Oral Prose Narratives: Ethnic Genres and Social Functions." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature: Addis Ababa University, Unpublished, 1999.

Bender, M.L. and others. Language in Ethiopia. London, Oxford University Press, 1976.

Dégh, Linda. "Oral Folklore Oral Narratives." In Dorson, Richard M. (Ed.) Folklore and Folk life: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Dorson, Richard M. (Ed.). Folklore and Folk Life: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Dundes, Alen. Folklore Matters. USA, The University of Tennessee press, 1986.

________. The Study of Folklore. USA, University of California Press, 1996.

Federal democratic republic of Ethiopia population census commission central statistical agency: The 2007 population and housing census of Ethiopia result for SNNPR. Part1 statistical report on population size and characteristics: Branna Printing Enterprise, August 2010 Addis Ababa.

Finnegan, Ruth. Oral Literature in Africa. Oxford: Clarendon Press, 1970.

Gray, Martin. A Dictionary of Literary terms. (2nd revised edition), Longman, 1992.

Jason, Heda. Concerning the Historical and the Local Legends and Their Relatives. (Electronic version) Towards New Perspectives in Folklore, Vol. 84, No 331, 1971.

Leach, Maria. Standards Dictionary of Folklore Mythology and Legend. USA: New York, Vo:2, 1950.

Lewis P. Henchman and Sandra K., Henchman. (eds) Memory, Identity and Community. State University of New York press, 2001.

Melakneh Mengistu. "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales." Unpublished, M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1990.

Okpewho, Isidore. Africa Oral Literature in Africa: Backgrounds, Characters and Continuity. Bloomington: Indiana University, 1992.

Oring, Elliot. Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction. Long: Utah University Press, 1986.

__________. "Three Function of Foklore: Tradtional Functionalizm as Explanation In Folkloristic". The Jornal of Amercan Foklore, Vol.89,No.351 (Jan.Mar.,1976)pp.6780,Http://www.Jstor.org/stable/539547.

Peek, Philip M. and Kewesi Yankah. Africa Folklore, An Encyclopedia. New York: Rouldge, 2004.

Sahilu Kidane. "Borana Oromo Prose Narratives: A Contextual Study." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature: Addis Ababa University, Unpublished, 1996.

Sergaw Hablesellassi. Ancient and Medieval Ethiopia History to 1270. Addis Ababa, /Unknown Publisher/ 1972.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions. Long, Utah State University Press, 2005.

Stitz, Volker. The Western Argoba of Yifat, Central Ethiopia, in the proceedings of the first United States Conference on Ethiopia Studies. Michigan State University. 1973.

Taddesse Tamrat. Church and State in Ethiopia (1270-1527). London: Oxford University press, 1972.

__________. "The States in Ethiopia and the Horn". The General History of Africa. UNESCO press, 1984, volume IV, page 9.

Tesfaye Gebre Mariyam. "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature: Addis Ababa University, Unpublished, 1990.

Tesfaye Hailu. "History and Culture of the Argobaba" http://www.persee.fr/web/ Revues/home/prescript/article/ethio_0066-2127_2000_num_16_1_975

Thompson, Stitch. The Folktale. New York, University of California Press, 1946.

Vansina, Jan. Oral Tradition As History. USA: The University of Wisconsin Press, 1985.

Weeks, V. Richards. Muslim Peoples: A world Ethnographic survey. /Second edition/, Revised and expanded, 1984.

Yihenew Jembere. "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature: Addis Ababa University, Unpublished, 1996.

# አባሪ አንድ

## የፎቶግራፎች ዝርዝር (በከፊል)



አቶ አሚኑ ኢድሪስ (ሸዋሮቢት)



ሼህ አረቡ ሁሴን (ከሚሴ)



ከግራ ወደ ቀኝ ሐጅ መሀመድ እስማኤል፣ አጥኚው፣ ሼህ አህመድ አባቡሽ እና አቶ በሺር ከማል(ሾንኬ)



ሼህ ዩሱፍ አብዱሰመድ (መዲና)



የሾንኬ መንደር



አቶ አብዱሰላም ከማል (ከሚሴ)



አቶ አህመድ ኑር (መዲና)



ከሸዋሮቢት ከተማ 15 ኪ.ሜ ርቀት ላይ

የሚገኘው ጥንታዊው የጉዜ መስጊድ



ወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድ (አባ ወላስማ)

(አልዩ አምባ)



ከግራ ወደ ቀኝ ወላስማ ሐጅ ኑርሴን

መሀመድ እና አጥኚው (አልዩ አምባ)



አቶ መሀመድ ሰይድይድ

(ሸዋ ሮቢት)



የአርጐባ መንደር ህጻናት (ሾንኬ)

# አባሪ ሁለት

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

### ሀ. ቁልፍ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | አድራሻ | ሥራ | መረጃ የተሰጠበት ቀን | የሰጡት መረጃ አይነት | መረጃ የሰጡበት ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሼህ አረቡ ሁሴን | ወ | 61 | ከሚሴ | የማኅረሰቡ ታሪክ አዋቂና የአገር ሽማግሌ | 08/09/ 2004 ዓ.ም. | ስለ አርጎባ ባህልና ቃላዊ ዝርው ተረኮች | በቴፕሪከርደር ፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 2 | ሼህ ዩሱፍ አብዱሰመድ | ወ | 60 | መዲና | የማኅረሰቡ ታሪክ አዋቂና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል | 09-10/ 09/ 2004 ዓ.ም. | ስለአርጎባ ባህል፣ ታሪክ እና ቃላዊ ዝርው ተረኮችን | በቴፕሪከርደር ፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 3 | ሐጅ መሀመድ እስማኤል (አባ ባሀር) | ወ | 66 | ሾንኬ | የኃይማኖት መሪ፣ አስተማሪ እና የሀገር ሽማግሌ | 15-16/ 09/ 2004 ዓ.ም. | ስለአርጎባ ባህል፣ ታሪክ እና ቃላዊ ዝርው ተረኮችን | በቴፕሪከርደር ፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 4 | ሼህ አህመድ አባቡሽ | ወ | 89 | ሾንኬ | የሀገር ሽማግሌ | 15-16/ 09/ 2004 ዓ.ም. | ስለአርጎባ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን | በቴፕሪከርደር ፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 5 | አቶ በሽር ከማል | ወ | 45 | ሾንኬ | የሾንኬ መንደር አስተዳዳሪ | 15-16/ 09/ 2004 ዓ.ም. | ስለአርጎባ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን | በቴፕሪከርደር ፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 6 | አቶ አሚኑ ኢድሪስ | ወ | 61 | ሸዋሮቢ ት | የአርጎባ ታሪክ አዋቂ እና የፌ ዴሬሽን ምክር ቤት አባል | 20/09/200 4 ዓ.ም. | ስለአርጎባ ባህል፣ ታሪክ እና ቃላዊ ዝርው ተረኮችን | በቴፕሪከርደር ፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 7 | ሼህ መሀመድ ያሲን | ወ | 86 | ሸዋሮቢ ት | የአርጎባ ታሪክ አዋቂና የሀገር ሽማግሌ | 21/09/200 4 ዓ.ም. | ስለአርጎባ ባህል፣ ታሪክ እና ቃላዊ ዝርው ተረኮችን | በቴፕሪከርደር ፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 8 | ሼህ መሀመድ አወል | ወ | 43 | አንኮበር | የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኛ | 22/09/200 4 ዓ.ም. | ስለአርጎባ ባህል፣ ታሪክ እና ቃላዊ ዝርው ተረኮችን | በቴፕሪከርደር ፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 9 | ወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድ | ወ | 62 | አልዩ አምባ | ንግድ | 15/06/200 5 ዓ.ም. | ስለአርጎባ ባህል፣ ታሪክ እና ቃላዊ ዝርው ተረኮችን | በቴፕ ሪከርደና በማስታወሻ ደብተር |
| 10 | ወላስማ ሐጅ ኑርሴን መሀመድ | ወ | 58 | አልዩ አምባ | ንግድ | 16/06/200 5 ዓ.ም. | ስለአርጎባ ባህል፣ ታሪክ እና ቃላዊ ዝርው ተረኮችን | በቴፕ ሪከርደና በማስታወሻ ደብተር |

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | አድራሻ | ሥራ | መረጃ የተሰጠበት ቀን | የሰጡት መረጃ አይነት | መረጃ የሰጡበት ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | አቶ መሀመድ ሰይድ | ወ | 73 | አልዩ አምባ | ንግድና ግብርና | 16/06/2005 ዓ.ም. | ስለአርጐባ ባህል፣ ታሪክ እና ቃላዊ ዝርው ተረኮችን | በቴፕ ሪከርደና በማስታወሻ ደብተር |

## ለ. ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | አድራሻ | ሥራ | መረጃ የተሰጠበት ቀን | የሰጡት መረጃ አይነት | መረጃ የሰጡበት ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አብዱሰላም ከማል | ወ | 27 | ከሚሴ | የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ | 06/09/ 2004 ዓ.ም. | ስለአርጐባ ባህል እና ታሪክ | በቴፕሪከርደር፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 2 | አቶ ሚሊዮን እሸቱ | ወ | 32 | ከሚሴ | የታሪክ መምህር | 07/09/ 2004 ዓ.ም. | ስለአርጐባ ባህል እና ታሪክ | በቴፕሪከርደር፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 3 | አቶ ከበደ አለሙ | ወ | 46 | ከሚሴ | የቋንቋ መምህር | 07/09/ 2004 ዓ.ም. | ስለአርጐባ ባህል እና ታሪክ | በቴፕሪከርደር፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 4 | አቶ አህመድ ኑሩ መሐመድ | ወ | 27 | መዲና | የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ | 09-10/ 09/ 2004 ዓ.ም. | ስለአርጐባ ባህል እና ታሪክ | በቴፕሪከርደር፣ በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 5 | አቶ ሁሴን ከማል | ወ | 45 | ከሚሴ | የእደጥበብ ባለሙያ | 14/09/2004 ዓ.ም | ስለእደ ጥበብ ሙያተኞች ማንነታች | በማስታወሻ ደብተር |
| 6 | አቶ ሙሉጌታ ልዑልሰገድ | ወ | 35 | አንኮበር | የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ | 14/06/2005 ዓ.ም. | ስለአርጐባ ባህል፣ | በጽሁፍና በማስታወሻ ደብተር |
| 7 | አቶ አሰፋ ዘነበ | ወ | 30 | አንኮበር | የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሙያ | 14/06/2005 ዓ.ም. | ስለአርጐባ ባህል፣ | በማስታወሻ ደብተር |

# አባሪ ሦስት

## ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ስምዎትን፣ የትውልድ ስፍራዎትን፣ ዕድሜዎትንና ማኅበረሰብዎትን ቢገልጹልኝ?
2. በዚህ አካባቢ ለምን ያህል ጊዜ ኖሩ?
3. አርጐባ ማለት ምን ማለት ነው? የቃሉ ትርጉም ምንድን ነው? ለምን አርጐባ የሚል ስያሜ ተሰጠው? ከአርጐባ ማኅበረሰብ ስያሜ ጋር የተያያዙ ተረኮች ካሉ ቢነግሩኝ?
4. የአርጐባ ማኅበረሰቦች ከየትና መቼ መጡ? በምን ምክንያትስ መጡ ? ስለ አርጐባ ታሪክ የሚያውቁትን ቢገልጹልኝ? ለምን መጡ ተብሎ ይነገራል? ከአመጣጣቸው ጋር የተያያዘ ምን የሚባል ነገር አለ?
5. አርጐቦች ከይፋት ጋር ተያይዘው የሚነሱበት ሁኔታ አለ፡፡ ስለዚህ የሚያውቁት ታሪክ ካለ ቢያብራሩልኝ? እናንተ ከይፋት በምን በምን ነጥቦች ትለያላችሁ?
6. አርጐቦች ከሌሎች ማኅበረሰቦች የሚለዩበት ባህል አላቸው? ካላቸው ቢነግሩኝ?
7. አርጐቦች በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተሰራጭተው እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ የሁሉም ምንጭ አንድ ነው? ወይስ የተለያየ ነው? ከአርጐቦች ስርጭት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ታሪኮችን ቢያጫውቱኝ? ለምን ተበተኑ?
8. ከአርጐቦች ዝርያ ጋር በተያያዘ ዱባና ሻጉራ ሲባል ይሰማል ምን ማለት ነው? ለምን ተባለ?
9. በደቡብ ክፍል በተለይም በአዋሽና በሐረር አካባቢ የሚኖሩ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ከእናንተ የተለዩ ናቸው? የሚለዩ ከሆነ የሚለዩበትን ምክንያት ምንድን ነው?
10. አርጐቦች በአካባቢያቸው ከሚኖሩት ኦሮሞዎች፣ አማራዎችና አፋሮች የሚለያችሁ ነገር ካለ ቢገልጹልኝ? ሌሎች ማኅበረሰቦችስ ስለእናንተ ምን ይላሉ?
11. ጥንታዊ የአርጐባ ማኅበረሰብ መኖሪያዎች ተራራ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ተራራ ላይ ከመስፈራችሁ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች ካሉ ቢነግሩኝ? ለምን ተራራን መረጣችሁ? ገጠመኝ ካለዎት በገጠመኝ ቢያስረዱኝ?
12. አርጐቦች የተለዩ የቤት አሠራር እንዳላቸው ይነገራል፡፡ ከቤት አሠራራችሁ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች አሉ? ይህ አይነት የቤት አሠራር እንዴትና መቼ እንደተጀመረ የሚያውቁትን ታሪክ ቢነግሩኝ? ቤቱን በዚህ ቅርጽ ያልሠሩ የማኅበረሰቡ አባላት ምን ይገጥማቸዋል? ገጠመኝ ካለ በገጠመኝ ቢያስረዱኝ?

13. አርጕቦች የሚተዳደሩት በምን ሥራ ነው? ከጕበዝና ከሰነፍ ገበሬ ጋር በተያያዘ ምን ተረክ አላችሁ?

14. የሥራ ባህላችሁ ምን ይመስላል፣ ከሥራችሁ አንፃር ወይም ከአካባቢያችሁ ካለ ነገር ጋር በተያያዘ የተሰጠ ስያሜ ካለ ቢገልጹልኝ?

15. በአርጕባ ማኅበረሰብ ለወንዶችና ለሴቶች ተብለው የተለዩ ሥራዎች አሉ፡፡ ካሉ የተለዩበትን ምክንያት ቢያብራሩልኝ? ይህንን የማያከብሩ ወንዶች/ሴቶች ቢኖሩ ምን ይደረጋል? ካሁን በፊት ምን ያጋጠመ ነገር አለ?

16. የሸክላ እና የብረታብረት ሥራ አርጕቦች እንደማይሰሩ ይነገራል ይህ እውነት ከሆነ የማትሰሩበትን ምክንያት ቢገልጹልኝ? ከዚህ በፊት እነዚህን ሥራዎች የሰሩ ሰዎች ምን የገጠማቸው ነገር አለ? እነዚህን ሥራዎች አሁን ቢሰሩ ምን ይደርስባቸዋል ተብሎ ይታመናል?

17. በአርጕባ ባህል መሠረት የጋብቻ ምርጫ በማን ነው የሚከናወነው?

18. የአርጕቦች የሠርግ ስርዓት ምን ይመስላል ከመተጫጨት ጀምሮ ሙሽራዎች ጐጆ እስከሚወጡ ድረስ ያለውን ሂደት ቢገልጹልኝ?

19. አርጕቦች ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር እንደማይጋቡ ይነገራል? የማይጋቡበት ምክንያት ምን እንደሆነ ይታወቃል? ሌሎች የአካባቢ ሰዎች የአርጕባን ማኅበረሰብ ተወላጆችን ማግባት ይፈልጋሉ? ይህ አይነት ሁኔታ ቢፈጠር ምን ታደርጋላችሁ? ያጋጠመ ነገር ካለ ቢገልጹልኝ?

20. አርጕቦች በዋናነት የምታከብሯቸው ሐይማኖታዊና ባሕላዊ በዓላት አሏችሁ? ካሏችሁ የበዓላት አከባበራችሁ ምን ይመስላል? ከየት? መቼ? እንዴት? ለምን? በማን? እንደተጀመሩ ይታወቃል? በዓላቱን የማያከብሩ የማኅበረሰቡ አባላት ምን ይገጥማቸዋል? ከዚህ በፊት ያጋጠመ ነገር ካለ ቢገልጹልኝ?

21. ቀደም ሲል ታከብሯቸው የነበረና አሁን የተዋቻኋቸው በዓላት አሉ? ካሉ የትኞቹ በዓላት ናቸው? ለምንስ ማክበረ አቆማችሁ? ምን ገጥሟችሁ ልታቆሙ ቻላችሁ?

22. አርጕቦች በሐይማኖታዊና ባሕላዊ በዓላት ወቅት የምትጫወቷቸው ጨዋታዎችን ቢነግሩኝ? ጨዋታችሁስ ከሌሎች ማኅበረሰቦች ጨዋታ በምን ይለያሉ? ለምን ይህንን ጨዋታ ትጫወታላችሁ?

23. በአርጕባ ማኅበረሰብ ዘንድ የግርዘት ስርዓት አለ? ካለ የግርዘት ስርዓታችሁ ምን ይመስላል? የግርዘት ስርዓት ለምን ያስፈልጋል? የዚህ ባህላዊ/ ሐይማኖታዊ

ስርዓት ምንጩ ምንድን ነው? አንድ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጂ ባይገረዝ ምን ይደርስበታል? ከዚህ በፊት ያጋጠመ ነገር ካለ ቢገልጹልኝ?

24. በአርጐቦች ዘንድ ሐዘን ሲደርስባችሁ ሐዘናችሁን የምትገልጹበት ስርዓት ምን ይመስላል? ለምን እንዲህ አይነት ስርዓት ልትከተሉ ቻላችሁ?
25. በአርጐቦች ዘንድ ግጭት ሲፈጠር ግጭቱን የምትፈቱበት መንገድ አለ? ከግጭት አፈታት ጋር በተያያዘ "በሌ" ወይም "ረከቦት" የሚባል ባህላዊ መንገድ እንዳለ ይነገራል? "በሌ" ወይም "ረከቦት" ምንድን ነው? ከዚህ ስርዓት የወጣ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጂ ምን ይደርስበታል ተብሎ ይታመናል? ከዚህ በፊት ምን ደርሶ ያውቃል?
26. ባህላዊ የግጭት አፈታት መቼ እና እንዴት እንደተጀመረ የሚታወቅ ነገር ካለ ቢገልጹልኝ?
27. የአርጐቦች የወሊድ ስርዓት ምን ይመስላል? የመውለጃ ጊዜዋ ከደረሰች ነፍሰጡር ጋር በተያያዘ "ፋጢማዬ" የተሰኘ ስርዓት እንዳለ ይነገራል፡፡ "ፋጢማዬ" ማለት ምን ማለት ነው? ለምን ፋጤማዬ ተባለ?
28. የአርጐባ ህፃናት አፋቸውን የሚፈቱት በምን ቋንቋ ነው? የአርጐብኛ ቋንቋ በሌሎች ቋንቋዎች (በአማርኛና በኦሮምኛ) እየተዋጠ እንደሆነ ይነገራል? ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቁት ነገር አለ? የአርጐባ ቋንቋ ከሌሎች ቋንቋ በምን ይለያል? ከዚህ ጋር የተያያዘ የሚያውቁት ታሪክ አለ? ካለ ቢገልጹልኝ?
29. አርጐቦች ባህላዊ የአስተዳደርና የዳኝነት ስርዓት አላቸው? ካላቸው ምን ይመስላል? በተለይም ወላስማ፣ ቃዲና ደሚና የሚባሉ የአስተዳደር ስርዓቶች እንዳሏችሁ ይነገራል ስለዚህ የሚያውቁት ነገር አለ? እነዚህ ስርዓቶች ለምን ወላስማ? ቃዲና ዳሚና ተባሉ? ከዚህ የዳኝነት ስርዓት የወጣ አርጐባ ምን ይደርስበታል ተብሎ ይታመናል? ከዚህ በፊት የደረሰ አጋጣሚ ካለ ቢነግሩኝ?
30. የአርጐቦች የአለባበስ ስርዓት ምን ይመስላል? በአዘቦትና በበዓለት ወቅት ስለሚለበሱ አልባሳት ቢያብራሩልን? አርጐቦች ይህንን ያለባበስ ስርዓት ለምን መረጡት? ሌሎች ስለእናንተ ምን ይላሉ?
31. አርጐቦች የተለየ የአጋጌጥ ስርዓት አላቸው? ካላቸው ቢያብራሩልኝ? አርጐቦች ይህንን የአጋጌጥ ስርዓት ለምን መረጣችሁ?
32. አርጐቦች የተለየ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ አላቸው? ካላቸው ምን ይመስላል? ይህ የምግብ አዘገጃጀታችሁና አመጋገባችሁ ምን የተለየ ጥቅም አለው?

33. አርጎቦች “ወቃሊሞ” የሚባል የተለየ ምግብ እንዳላቸው ይነገራል፡፡ ስለዚህ ባህላዊ ምግብ አዘገጃጀት ቢገልጹልኝ? ስለ አመጣጡ (አጀማመሩ) የሚያውቁት ነገር አለ? ካለ ቢያብራሩልኝ? ለምን ወቃሊሞ ተባለ?

34. በአርጎቦች ዘንድ የተለያዩ ተረቶች እንደሚነገሩ ይነገራል? ተዘውትርው የሚተረኩ ተረቶችን ቢነግሩኝ/ቢተርኩልኝ? ተረቶች በምን ሁኔታና በምን ሰዓት ነው የሚተረኩት?

35. እስቲ ስለ ፈሪ፣ ስለጀግና፣ ስለእውቀት፣ ስለብልህነት፣ ስለአስተዋይነት፣ ስለጀግንነት፣ ስለደፋር፣ ስለሰነፍ፣ ስለጐበዝ፣ ስለጠረኛ፣ ተረቶች ካሏችሁ ቢነግሩኝ?

# አባሪ አራት

## ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን

ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት ለጥናቱ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጌአለሁ። በቅድሚያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት እና ከምሠራበት መስሪያ ቤት የትብብር ደብዳቤ እንዲጻፍልኝ አደረግኩ። በመቀጠል አዲስ አበባ የሚገኘው የአርጐባ ልማት ማህበር አባላት ትብብር ሊያደርጉልኝ የሚችሉ ሰዎች ስልክ ቁጥር ተቀበልኩ። በመስክ ቆይታ ወቅት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉና ሌሎች የመገልገያ ቁሳቁሶችን በማዘጋጀት ሁሉም ነገር እንዲሟላ አስፈላጊውን ጥረት አደረኩ፡፡

ቅድመ መስክ ዝግጅቴን ካጠናቀቅኩ በኋላ እሁድ ግንቦት 5 ቀን 2004 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ወደ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኦሮሞ ልዩ ዞን በመጓዝ ከሚሴ ደረስኩ። ከሚሴ ከአዲስ አበባ 325 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ሞቃታማ የአየር ንብረት ያላት ከተማ ናት። ከሚሴ እንደደረስኩ አልጋ በመያዝ እረፍት አደረግኩ። በማግስቱ ሰኞ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም. የተፃፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ ወደ ከሚሴ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ሄድኩኝ። የአስተዳደሩ ጽ/ቤት ተወካይ ለሆኑት ለአቶ መሰረት ተፈራ የመጣሁበትን ጉዳይ በመግለጽ በአርጐባ ማኅበረሰብ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች ወይም ጽሁፎች እንደምፈልግ አስረዳኋቸው። እርሳቸውም መረጃዎች ላገኝ ወደምችልባቸው መስሪያ ቤቶች ማለትም የኦሮሞ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት እና ወደ ደዌ ጨፋ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በመደወል አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉልኝ በመንገር አሰናበቱኝ። ላደረጉልኝ ትብብር በማመስገን ወደ ዞኑ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሄድኩ። በጽ/ቤቱ ውስጥ ያገኘኋቸው ባለሙያዎች ስለእኔ ከከሚሴ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ተደውሎ እንደተነገራቸው በማስታወስ፣ ነገር ግን የአርጐባን ማኅበረሰብ የሚመለከት ምንም አይነት መረጃ እንደሌላቸው ገልጸው አሰናበቱኝ። ከዚያም ወደ ደዌ ጨፋ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት አመራሁ። የጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ አብዱሰላም ከማል በጥሩ ሁኔታ ተቀብለው ምን አይነት መረጃ እንደምፈልግ ጠየቁኝ። በአርጐባ ማኅበረሰብ ዙሪያ የተፃፉ ማናቸውንም አይነት መረጃ ባገኝ ደስ እንደሚለኝ ነገርኳቸው። እርሳቸውም በእነርሱ ወረዳ ውስጥ የሸንኬ መንደር እንደሚገኝ በማስረዳት፣ ስለማኅበረሰቡ የሚያውቁትን በሙሉ በቴፕና በጽሁፍ እንደሚሰጡን ገልጸውልኝ፣ ያዘጋጀኋቸውን ጥያቄ በመቀበል ከሰዓት በኋላ ለመገናኘት ተስማምተን

ተለያየን። ከሰዓት በኋላ ከመጠይቆች መካከል የሚያውቋቸውን መርጠው በቴፕ ሪከርደር የምፈልገውን መረጃ ሰጡኝ። በጽሁፍ ያዘጋጁትን ደግሞ ከኮምፒዩተራቸው ላይ ፕሪንት በማድርግ አቀበሉኝ። የተሻለ መረጃ ለማግኘት ወደ ሾንኬ መንደር እንድሄድ በመምከር የትብብር ደብዳቤ ጻፉልኝ። ስላደረጉልኝ ሁሉ አመስግኜ አልጋ ወደ ያዝኩበት ሆቴል ተመለስኩ።

ማክሰኞ ግንቦት 7 ቀን 2004 ዓ.ም. ወደ ከሚሴ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በመሄድ ከንቲባውን አቶ ሰይድ መሀመድን አግኝቼ የመጣሁበትን አስረዳኋቸው። እርሳቸውም የአርጎባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ሆነው፣ በማኅበረሰብ ባህልና ታሪክ ላይ ጥሩ ዕውቀት ያላቸውን ሽማግሌዎች በሚቀጥለው ቀን እንደሚያዘጋጁልኝ ተነጋግረን ተለያየን። ከሰዓት በኋላ ወደ ከሚሴ ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ት/ቤት በመሄድ በከተማዋ ውስጥ ለረጅም ዓመታት የኖሩ የታሪክና የቋንቋ መምህራንን አግኝቼ በአርጎባ ማኅበረሰብ አመጣጥና ባህል ባላቸው አመለካከት ዙሪያ መረጃ በማሰባሰብ ዋልኩ።

ረቡዕ ግንቦት 8 ቀን 2004 ዓ.ም. ወደ ከሚሴ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በመሄድ ከንቲባው ካስጠሩልኝ ሽማግሌዎች ጋር ተዋወቅሁ። ቀኑ የገበያ ቀን በመሆኑ ሽማግሌዎች ሥራ እንዳላቸው ስለነገሩኝ፣ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ላይ ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘን ተለያዩን። በቀጠሯችን ሰዓት ከሽማግሌዎች ጋር በመገናኘት ጥያቄዎችን አቅርቤ የምፈልጋቸው አይነት መረጃዎችን ሰበሰብኩ።

ሃሙስ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም. ጠዋት ከከሚሴ 50 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ወደ ምትገኘው የአርጎባ ልዩ ወረዳ ከተማ ወደ ሆነችው መዲና አመራሁ። መዲና እንደደረስኩ ከአርጎባ ልማት ማህበር መረጃዎችን በማሰባሰብ ዙሪያ እንደሚያግዙኝ ወደተነገሩኝ ሰዎች ስልክ ደወልኩ። ከሰዓት በኋላ ከሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ ጋር ተገናኘሁ። እርሳቸው የሚያውቁትን መረጃ በመግለጽና ስለማኅበረሰቡ ታሪክና ባህል የሚያውቁ ሰዎችን በማሰባሰብ ከፍተኛ እገዛ አደረጉልኝ። ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ እና የአርጎባ ልዩ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አህመድ ኑር መሀመድ ባደረጉልኝ ድጋፍ በሁለት ቀናት ውስጥ መረጃዎችን አሰባስቤ ወደ ከሚሴ ተመለስኩ።

ከከሚሴ ወደ ሾንኬ ለመሄድ የእግር መንገድ ስላለው አብሮኝ የሚሄድ ሰው ማፈላለግ ነበረብኝ። ወደ ሾንኬ የሚሄድ ሰው የሚገኘው በገበያ ቀን በመሆኑ እስከ ግንቦት 14 ቀን 2004 ዓ.ም. ከሚሴ መቆየት የግድ ሆነ። በከሚሴ ቆይታዬ በቴፕ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በመገልበጥ (Transcribe በማድረግ) ቆየሁ።

ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ ከሚሴ መጥተው ስለነበር ወደ ሾንኬ የሚሄድ ሰው አፈላልገው አገኙልኝ። ረቡዕ ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡30 ላይ ወደ ሾንኬ ከሚወስደኝ ልጅ ጋር በመሆን እስከ ቦርከና ወንዝ ድረስ በመኪና ሄደን። ከዚያም በእግራችን ተጉዘን ከአራት ሰዓት ጉዞ በኋላ ሾንኬ ደረስን። ሾንኬ ስንደርስ የደዌ ጨፋ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሠራተኞችን ለሥራ ሾንኬ ገብተው አገኘኋቸው። በከሚሴ ቆታዬ ከእነሱ ጋር ተግባብቼ ስለነበር ከመንደሯ አስተዳዳሪ አቶ በሽር ከማል ጋር በማስተዋወቅ የምፈልገውን መረጃ እንዳገኝ ትብብር እንዲያደርጉልኝ ነገሯቸው፡፡ እኔም ከደዌ ጨፋ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የተፃፈልኝን ደብዳቤ ሰጠኋቸው፡፡ አስተዳዳሪውም በመንደሯ ታዋቂ ወደ ሆኑት ሐጅ መሀመድ እስማኤል ቤት በመውሰድ የምፈልገውን መረጃ እንዲሰጡኝ አደራ በማለት ተመለሱ። ከሐጅ መሀመድ እስማኤል ቤት እየተመገብኩና እያደርኩ በሁለት ቀን ውስጥ የምፈልገውን ያህል መረጃዎችን ማሰባሰብ ቻልኩ።

አርብ ግንቦት 17 ቀን 2004 ዓ.ም. ወደ ከሚሴ ተመልሼ፣ ቅዳሜ ግንቦት 18 ቀን 2004 ዓ.ም. ጠዋት ወደ ሸዋሮቢት ሄድኩኝ። ሸዋሮቢት እንደደረስኩ አልጋ በመያዝ መረጃ ሊሰጡኝ እንደሚችሉ ለተነገሩኝ ሰዎች እየደወልኩ ቀጠሮ ያዝኩ። በቀጠሮው መሰረት እሁድ ግንቦት 19 ቀን 2004 ዓ.ም. ጠዋት ተነስቶ መረጃ ከሚሰጡኝ ሰዎች ጋር ተገናኘሁ። እነሱም የአርጐባን ታሪክና ባህል ከሚያውቁ ሌሎች ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ቢሰጡኝ የተሻለ እንደሆነ በማስረዳት ከሰዓት በኋላ አሰባስበው እንደሚጠብቁኝ ተስማምተን ተለያዩን። ከሰዓት በኋላ በቀጠሮው ቦታ ስደርስ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጅ ሽማግሌዎች እየጠበቁኝ አገኘኋቸው። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተጻፈልኝን ደብዳቤ እና መታወቂያየን በማሳዬት የመጣሁበትን ምክንያት አስረዳኋቸው። በምፈልገው መረጃ ዙሪያ ተነጋግረን የምፈልገውን መረጃ ለመሰብሰብ ቴፕሬከደር ሳወጣ ከመካከላቸው አንዱ የከተማው አስተዳደር ሳያውቅ ሰዎችን በማሰባሰብ መረጃ ለማግኘት መሞከሬ አግባብ አለመሆኑን ነገሩኝ። የከተማው አስተዳደር ካልፈቀደ ምንም አይነት መረጃ እንዳልሰበስብም ከለከሉኝ። ሽማግሌዎች ከመበተናቸው በፊት የቀወት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኋላፊን ስልክ በማግኘቴ ደውዬ ሁኔታውን አስረዳኋቸው። እርሳቸውም ነገ ጠዋት የእነርሱ ሰዎች ባሉበት መረጃውን እንዳገኝ እንደሚረዱኝ አስረድተውኝ በሚቀጥለው ቀን ማለትም ሰኞ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም ከዩኒቨርስቲው የተጻፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ለመገናኘት ተስማማን፡፡ በዚህ ምክንያትም ሽማግሌዎችን በማመስገን አሰናበትኳቸው፡፡

ሰኞ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም. ወደ ቀወት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በመሄድ የጽ/ቤቱን ኋላፊ አግኝቼ አነጋገርኳቸው። እርሳቸው በቅርቡ በመመደባቸው በአርጐባ ባህል ዙሪያ መረጃ እንደሌላቸው በመግለጽ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ሽማግሌዎችን በማፈላለግ እንደሚተባበሩ አስረዱኝ። ስልክ በመደወል ሰዎችን ለማሰባሰብ ጥረት ቢያደርጉም ዕለቱ የሥራ ቀን በመሆኑ ከአቶ አማኑ ኢድሪስ በቀር ሌሎች ሰዎችን ሊያገኙልኝ አልቻሉም። አቶ አማኑ ኢድሪስ በአርጐባ ማኅበረሰብ ዙሪያ ጥናት ካካሄዱ የተለያዩ አጥኝዎች ጋር ረዳት መረጃ ሰባሳቢ ሆነው በመሥራታቸው በቂ የሆነ እውቀት ያላቸው በመሆናቸው የሚያውቁትን መረጃ በቴፕ ሰጡኝ። በተጨማሪም የአንኮበር ከተማ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኛ ከሆኑት ከሼህ መሀመድ አወል ጋር በስልክ አስተዋወቁኝ።

ማክሰኞ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም. ከሌሎች የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ጋር ተገናኝቼ መረጃዎችን በማሰባሰብ ከቀዬሁ በኋላ ማምሻ ላይ ወደ ደብረብርሃን ሄድኩኝ።

ረቡዕ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም. ወደ አንኮበር በመሄድ ከሼህ መሀመድ አወል ጋር ተገናኘሁ። ሼህ መሀመድ አወል ቤታቸው በመውሰድ ጋበዙኝ። ቡና አስፈልተውና ጫት ገዝተው አስተናገዱኝ። ሌሎች የአርጐባ ተወላጆችን በመጥራት እየቃምንና ቡና እየጠጣን መረጃዎችን አሰባስቤ ደብረብርሃን ተመልሼ አደርኩ።

ሃሙስ ግንቦት 23 ቀን 2004 ዓ.ም. በጠዋቱ ተነስቼ ወደ ሰሜን ሸዋ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ አመራሁ። የመጣሁበትን ሁኔታ በማስረዳት በአርጐባ ማኅበረሰብ ዙሪያ የተሰራ ጥናት ወይም ጽሁፍ እንዳለ ጠየቅኳቸው። እነርሱም ምንም አይነት መረጃ እንደሌላቸው ስለገለጹልኝ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩኝ። በዚህ አይነት ሁኔታ የመጀመሪያውን ዙር መረጃ የመሰብሰብ ሥራዬን በ19 ቀናት ውስጥ አጠናቅቄ ተመለስኩ።

በቀጣይነት በአልዩ አምባ ከተማና አካባቢ የሚኖሩ የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት የሚተርኳቸው ተረኮችን በጥናቱ ውስጥ ለማካተት ከአማካሪዬ ጋር በመመካከር ረቡዕ የካቲት 13 ቀን 2005 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ወደ ደብረ ብረሃን በመሄድ አደርኩ፡፡ በማግስቱ ሃሙስ የካቲት 14 ቀን 2005 ዓ.ም. ጠዋት ከደብረ ብርሃን 58 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ወደምትገኘው አልዩ አምባ አመራሁ። አልዩ አምባ ሞቃታማ የአየር ንብረት ያላት ትንሽ ከተማ ስትሆን የአማራና የአርጐባ ማኅበረሰብ በጋራ ይኖሩባታል፡፡ ከተማዋ ቀደም ሲል የንግድና የጉሙሩክ ማዕከል እንደነበረች ነዋሪዎቿ ይገልፃሉ፡፡ አልዩ አምባ

እንደደረስኩ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተፃፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ ወደ ከተማዋ አስተዳደር ጽ/ቤት አመራሁ። የከተማዋ አስተዳዳሪ ለሆኑት አቶ ሀሰን ኑሬ የመጣሁበትን ጉዳይ በማስረዳት በአርጐባ ማኅበረሰብ ዙሪያ የተሻለ እውቀት ያላቸው ሰዎችን ለማነጋገር እንደምፈልግ ገለጽኩላቸው። እርሳቸውም መረጃዎችን ማሰባሰብ የምችለው ከአንኮበር ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ይዤ ካመጣሁ ብቻ መሆኑን በመንገር አሰናበቱኝ። ከሰዓት በኋላ ወደ ጐረቤላ(አንኮበር) በመሄድ አደርኩ፡፡

አርብ የካቲት 15 ቀን 2004 ዓ.ም. ወደ አንኮበር ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በማምራት የጽ/ቤቱን ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ልዑልሰገድን አግኝቼ የመጣሁበትን ጉዳይ አስረዳኋቸው፡፡ እርሳቸውም በአርጐባ ማኅበረሰብ ዙሪያ ያሰባሰቡትን መረጃ ፎቶ ኮፒ በማድረግ አቀበሉኝ፡፡ የሚያውቁትንም በቃል ነገሩኝ፡፡ ከዚያም አልዩ አምባ ከሚኖሩ የአርጐባ ተወላጆች መካከል ስለማኅበረሰቡ ባህልና ታሪክ ጥሩ ዕውቀት ያላቸውን ሽማግሌዎች በመጠቆም የትብብር ደብዳቤ ጽፈው አሰናበቱኝ። ስላደረጉልኝ ሁሉ አመስግኜ ወደ አልዩ አምባ አመራሁ።

አልዩ አምባ እንደደረስኩ ወደ ከተማዋ አስተዳደር ጽ/ቤት በመሄድ የተፃፈልኝን የትብበር ደብዳቤ ለአስተዳዳሪው ሰጠኋቸው፡፡ እርሳቸውም ደብዳቤውን ካነበቡ በኋላ በከተማዋ ውስጥ በመንቀሳቀስ መረጃ እንዳሰባስብ ፈቀዱልኝ፡፡ እኔም ከአንኮበር ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት መረጃዎችን በማሰባሰብ ዙሪያ እንደሚያግዙኝ ከተነገሩኝ ሰዎች መካከል ለወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድ ስልክ በመደወል ቀጠሮ ያዝኩ፡፡ በቀጠሮው መሰረት ከሰዓት በኋላ ተገናኝተን ስለማኅበረሰቡ ታሪክና ባህል የሚያውቁትን መረጃ በቴፕ ሰጡኝ፡፡ በተጨማሪም ወንድማቸውንና ሌሎች ሰዎችን በማስተዋወቅ ባደረጉልኝ ድጋፍ በሁለት ቀናት ውስጥ መረጃዎችን አሰባስቤ እሁድ የካቲት 17 ቀን 2005 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ። በዚህ መልኩ የሁለተኛ ዙር መረጃ የመሰብሰብ ሥራዬን በ5 ቀናት ውስጥ አጠናቅቂያለሁ። በመጨረሻም የተጓደሉ መረጃዎችን ስልክ በመደወል ለማሟላት ጥረት አድርጌአለሁ።

## አባሪ አምስት

## የተረኮች ስብስብ

## ከአርጐባ ስያሚ ጋር የተያያዙ

### ተረክ አንድ

የነብዩ መሀመድ የእርጅና ዘመን ባለቤታቸው፣ ልጃቸው ሩቅያና ባለቤቷ፣ የአጐቷ ልጅ እና የነብዩ መሀመድ ተከታዮች ላይ ጥቃት ያደርስባቸው ከነበረው ቁረይሽ ጐሳ ሸሽተው በስደት ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ "አረብ ገብ" ተባሉ፡፡ አረብ ገብ የሚለው ቃል በጊዜ ሂደት አርጐባ ወደሚለው ስያሜ ተለወጠ (ሼህ ዩሱፍ አብዱሰመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም.፤ አብዱሰላም ከማል፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም፤ ወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድ እና ወላስማ ሐጅ ኑርሴን መሀመድ፣ የካቲት 15 እና 16 ቀን 2005 ዓ.ም)፡፡

### ተረክ ሁለት

አርጐባ የሚለው ስያሜ "ሀሬ ገባ" ከሚለው የተወሰደ ሲሆን፣ "ሀሬ ገባ" ማለት በወቅቱ በኢትዮጵያና በአረቦች መካከል በነበረው የባርያ ንግድ ሽያጭን መሠረት አድርጐ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ ትርጉሙም የማይሸጥ የማይለወጥ አረብ መጣ ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም "ሀሬ ገባ" ማለት ማኀበረሰቡ በጣም ቀያይ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ ተራራ ላይ ያለ ሀር ማለት ነው (ሼህ ዩሱፍ አብዱሰመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም፤ አብዱሰላም ከማል፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

### ተረክ ሦስት

በይፋት ውስጥ የሚገኙ የክርስትና ኃይማኖት ተከታዮች አማራ ተብለው ይጠራሉ፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች ደግሞ አርጐባ እንባላለን ስለዚህ ስያሜችንን ያገኘነው ከሐይማኖታችን ነው (ሼህ አረቡ ሁሴን፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 8 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

### ተረክ አራት

ስያሜው አርጐባ ሳይሆን ኸርጐባ ነው፡፡ ኸር ማለት ሀር ወይም ደማቅ ቀለም ያለው ጠንካራ ጨርቅ ሲሆን፣ ጐባ ማለት ደግሞ መቀመጥ (ተቀማጭ) ማለት ነው፡፡ ኸርጐባ ማለት በሀር ላይ የሚቀመጡ ሰዎች ማለት ነው፡፡ ስያሜው ከባህላዊ አለባበሳችንና

ከአኗኗራችን ተወስዶ የተሰጠን ነው (ሼህ ዩሱፍ አብዱሰመድ፣ መዲና፤ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም፤ አብዱሰላም ከማል፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም) ፡፡

## ተረክ አምስት

የአርጐባ ማኅበረሰብ የመጣነው ከአረብ አገር ስለሆነ አረብ ገባ የሚሉትን ቃላት በማጠጋጋት አረብ ገብ የሚል ስያሜ ተሰጠን (ሐጅ ኑርሴን ወላስማ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 16 ቀን 2005 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ስድስት

የአርጐባ ማኅበረሰብ የመጣነው ከየመን ነው፡፡ የመን ውስጥ የእርስ በርስ ግጭት ሲነሳ የተሸነፈው ወገን ወደ ኢትዮጵያ ሸሽተው ይመጡ ነበር፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገሮች በተሻለ ለየመን ቅርብ ስለሆነች ይመስለኛል፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት በወቅቱ የክርስትናን ኃይማኖት ተቀብሎ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ስደተኞችን ተቀብሎ በአገሩ እንዲኖሩ ፈቀላቸዋል፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ ክርስቲያኖች አማራ ተብለው ሲጠሩ ከየመን በስደት የመጣነው የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ደግሞ አርጐባ ተባልን፡፡ (መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም)

## ተረክ ሰባት

አርጐባ ማለት "ሁር-ገባ" ማለት ነው፡፡ ሁር ማለት በአረበኛ ነፃ ማለት ሲሆን፣ በወቅቱ የባርያ ንግድ ስለነበረ አረብ ገቦች ሐይማኖታዊ ሆነ የሥራ እንቅስቃሴ በነፃ እንዲያደርጉ ተፈቅዶላቸው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት "ነፃ ሰው ገባ" ወይም "ሁር-ገባ" የሚል ስያሜ ተሰጣቸው (ሼህ ዩሱፍ አብዱሰመድ፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ስምንት

አርጐባ ማለት "አረብ ገባ" ማለት ሲሆን በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከአረብ አገር በስደት ወደ ኢትዮጵያ ለመጡ ስደተኞች የተሰጣቸው ስያሜ ነው (አሚኑ ኢድሪስ፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም) ፡፡

## ተረክ ዘጠኝ

## ከአርጐቦች አመጣጥን ጋር የተያያዘ

ነብዩ መሀመድ የእስልምናን ኃይማኖት ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ ሲመሰርቱ ቁረይሾች ነብያችንንና ተከታዮቻቸውን ያሳድዷቸው ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ ነብዩ መሀመድ በኢትዮጵያ ውስጥ እውነተኛ መሪ እንዳለ ያውቁ ነበርና ቤተሰቦቻቸውንና ተከታዮቻቸውን "ወደ ሀበሻ ሀገር ሂዱ" አሏቸው፡፡ ይህንን የሰሙ ቁረይሾች እስልምና ወደ ሌሎች አገሮች ከተዛመተ ሠፊ የሆነ ድጋፍና ተቀባይነት ያገኛል ብለው ሠጉ፡፡ በዚህ ምክንያት ገፀ በረከት በመያዝ በፈረስና በግመል ፈጥነው ወደ ሀበሻ መንግሥት መጡ፡፡ ከንጉሱ ነጃሺ /ነጋሲ/ ፊት ቀርበው እጅ በመንሳትም ያመጡትን ወርቅና የከበሩ ድንጋዮች በማቅረብ "እንዲህ አይነት ስደተኞች ወደ እናንተ አገር መጥተዋል፡፡ ሐይማኖታችሁን የሚያረክሱ ቤተ-ክርስቲያኖቻችሁንና ጽላቶቻችሁን የሚያዋርዱ ናቸው፤ እንዳትቀበሏቸው" በማለት ለነጃሺ ገለጹላቸው፡፡ ነጃሺም በወንጌል ያምኑ ነበር፡፡ ወንጌል ላይ ደግሞ መሀመድ የሚባል ነብይ በመጨረሻ እንደሚመጣ ስለሚገልጽ ጊዜውን ሲጠብቁ ቆይተዋል፡፡ በዚህን ጊዜ "ስደተኞችን እስኪ ጥሯቸው፤ እናነጋግራቸው" አሉ፡፡ ቀድመው የገቡት ቁረይሾች ግን "ኧረ እባክዎን እርስዎ ፊት የሚቀርቡ አይደሉም፡፡ በጣም የተጠሉ፣ ወራዳና ድሆች ናቸው፡፡ በእኛ አካባቢ እንደ ሰው የሚቆጠሩ ስላልሆኑ አይቅረቡ፤ ከፊትዎ ቢቀርቡ እንኳን እጅ አይነሱም፡፡ ለባለስልጣን ሆነ ለታቦቶች አይሰግዱም፤ አያመልኩም፤ ግትሮች ናቸው" አሏቸው፡፡

እርሳቸው ግን "ይግቡና ምን እንደሆኑ እንያቸው" በማለት ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ስደተኞችም ከንጉሱ ፊት በመቅረብ ነብዩ መሀመድ የፃፉላቸውን ደብዳቤ ሰጧቸው፡፡ ነጃሺም ደብዳቤውን አነበቡና "ለመሆኑ ነብይ ለምትሉት እንደ ወንጌል ከፈጣሪ የወረደለት መጽሐፍ አለው ወይ?" በማለት ጠየቋቸው፡፡ የቡድኑ መሪ የነበረው ጃዕፈር ከፈጣሪ ለነብዩ መሀመድ የወረደላቸው መጽሐፍ እንዳላቸው ገልጾ ቁርዓን ቀራላቸው (አነበበላቸው)፡፡ በዚህን ጊዜ ንጉሱ ከአይናቸው ደም እስኪፈስ ድረስ ስቅስቅ ብለው አለቀሱ፡፡ "ይህ ኢንጅልና ወንጌል ከአንድ ማንቆርቆሪያ (በራድ) የተቀዱ ናቸው፤ ምንም አይነት ለውጥ የላቸውም" አሉ፡፡ ከዚያም "ቁረይሾችን ያመጣችሁትን ገፀ-በረከት በመያዝ ወደ መጣችሁበት ተመለሱ" አሏቸው፡፡ "እናንተ ስደተኞች ግን ተቀብያችኋለሁና በአገሬ ላይ በፈለጋችሁበት ቦታ መኖር ትችላላችሁ" አሏቸው፡፡ በዚህ መልኩ የመጡት አረብ ገቦች የእስልምናን ኃይማኖት እያስተማሩ አሁን ያለንበት ደረጃ ደረሱ፡፡ የአርጐቦች አመጣጥ ይህን ይመስላል፡፡ (ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ፣ መዲና፣

ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም፤ ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም፤ ወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)።

## ከአርጐብኛ ቋንቋ አመጣጥን ጋር የተያያዙ

## ተረክ አስር

አርጐቦች በስደት ወደ ሀበሻ ሲመጡ ቋንቋቸው አረብኛ ነበር። ከአረብ ሀገር እንደመጡ የሰፈሩት ሐውዜን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። ይህ ቦታ በአረብኛ "ሐወዘ" ይባላል። ሐወዘ ላይ ለተወሰነ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ከትግርኛና ከአረብኛ የተዳቀለ የራሳቸውን የሆነ ቋንቋ ይዘው ተነሱ። ለዚህም ነው የአርጐብኛ ቋንቋ ለትግርኛ ቋንቋ በጣም የቀረበ የሆነው። የሚጠቀሙት ግን በአረበኛ ፊደል ነበር። በዚያን ወቅት የጉሙሩክ ቀረጥ ይቀርጡ የነበረውና ማህተማቸውን ያዘጋጁት በአረብኛ ቋንቋ ነው። በወቅቱ ይገለገሉበት የነበረው ማህተም እስከ ዛሬ ድረስ በአልዩ አምባ ይገኛል (ሼህ አረቡ ሁሴን፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 8 ቀን 2004 ዓ.ም.፤ ወላስማ ሐጅ ኑርሴን መሀመድ ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 16 ቀን 2005 ዓ.ም.)።

## ተረክ አስራ አንድ

አርጐቦች ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ናቸው። በንግድና በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ደቡብ አረብያና የመን ይሄዱ ነበር። ነብዩ መሀመድ የእስልምናን ኃይማኖት በሚመሠርቱበት ወቅት ከ80 በላይ የአርጐባ ተወላጆች ሳውዲ አረቢያ ውስጥ ይኖሩ ነበር። የቁረይሽ ጐሳ አባላት ነብዩ መሀመድን እና ተከታዮቻቸውን ሲያሳድዷቸው ወደ ሀበሻ አገር ሂዱ ሰውን የማይበድል ትክክለኛ ንጉስ እዚያ አለ። ለሐይማኖታችሁም ሆነ ለእናንተ ጥሩ ነው አሏቸው። ምክንቱም አንድ ወገን የሚሰደደው ወደ ወገኑ ነው። በደል ሲደርስበት የሚሄደው ወደሚያምነውና ወደሚያስጠጋው ነው። በዚህ ምክንያት ሰይድ ኡስማን ጃፈር ቡድኑን እየመራ ወደ ኢትዮጵያ መጡ። በዚያን ጊዜ በስደት ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት ውስጥ የአርጐባ ተወላጆች ይገኙበታል።

እነዚህ ስደተኞች በኢትዮጵያ ውስጥ 15 ዓመት ከኖሩ በኋላ የነብዩ መሀመድ ልጅ ሩቅያና ባለቤቷ፣ የአጐቷ ልጅ፣ የነብዩ የእርጅና ዘመን ባለቤታቸው፣ ሰይድ ኡስማን ጃፈርን ጨምሮ የተወሰኑት ወደ ሳውዲ ተመልሰዋል። የተወሰኑት ግን የእስልምናን ኃይማኖት ለኢትዮጵያዊያን ለማስተማር እዚሁ ቀርተዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ የቀሩት

አረብ ገቦች ዝርያ የዛሬዎቹ አርጐቦች ናቸው (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድ እና ወላስማ ሐጅ ኑርሴንመሀመድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 እና 16 ቀን 2005 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ አስራ ሁለት

## የአርጐቦች አሠፋፈር ጋር የተያያዙ

አርጐቦች ከአረብ አገር እንደመጡ የሰፈሩት ሰሜን ሸዋ አካባቢ ነው፡፡ ሰሜን ሸዋን የመረጡትም የአገሪቱ ማዕከላዊ ቦታ ስለሆነ ነው፡፡ በወቅት አርጐቦች ታዋቂ ነጋዴዎች ነበሩ፡፡ ከሱማሌ፣ ከጅቡቲ፣ ከየመንና ከህንድ ሀገራት ጋር ጥሩ የሆነ የንግድ ግንኙነት ነበራቸው፡፡ አልዩ አምባ ደግሞ በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ ከተማዎችና ከውጭ አገራት ጋር ለመገናኘት አማካይ ቦታ ነው፡፡ ይህ ቦታ ሸቀጦችን ከውጭ በማስገባት ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለማሠራጨትና ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ደግሞ የዝሆን ጥረስ፣ ባሪያዎችን አሰባስቦ ወደ ውጪ ለመላክ ምቹ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አርጐቦች ለመኖሪያነት ሰሜን ሸዋን መርጠዋል (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ አስራ ሦስት

አርጐቦች ከአርብ ሀገር ሲመጡ ይዘውት የመጡት የእስልምናን ኃይማኖትን ነው፡፡ ይህንን ሐይማኖታቸውን ለማስፋፋት ደግሞ ወደ ተለያዩ ቦታዎች መንቀሳቀስን የግድ ይላቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት አርጐቦች እስልምናን ለማስተማር በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡ በወቅቱ በትግራይ፣ በአማራ፣ በአፋር፣ በኦሮሞ፣ በደቡብና በተለያዩ አካባቢዎች ተንቀሳቅሰው እስልምናን አስተምረዋል፡፡ በመምህርነት የተንቀሳቀሱት የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች በየሔዱበት አካባቢ በመስፈር ባህላቸውንና ሐይማኖታቸውን ጠብቀው እስከዛሬ ድረስ ይገኛሉ (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.)

## ተረክ አስራ አራት

አርጐቦች ከአረብ አገር እንደመጡ በዋናነት የሰፈሩት ሰሜን ሸዋ አካባቢ ነበር፡፡ ሰሜን ሸዋ እየኖሩ እያለ አጼ ዮሃንስ የሚባሉ ንጉስ በኢትዮጵያ ወስጥ ነገሱ፡፡ እሳቸውም ቁረቡ የሚል ህግ አፀደቁ፡፡ ያልቆረበ ሀገሩን ለቆ ይውጣ አሉ፡፡ በዚህን ጊዜ

ለህይወታቸው የሰጉ አርጐቦች ሲቀርቡ ብዙዎቹ ግን ሐይማኖታችንን ከምንለውጥ ሀገር ለቀን ብንወጣ ይሻለናል ብለው ተሰደዱ፡፡ ዛሬ በተለያዩ ቦታ ተበታትነው የሚገኙ አርጐቦች በቁረቡ ዘመን አካባቢያቸውን ጥለው የሄዱ ናቸው (ወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድ፤ ወላስማ ሐጅ ኑርሴን መሀመድ እና አቶ መሀመድ ሰይድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 እና 16 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ተረክ አስራ አምስት

አርጐቦች በስደት ወደ ሀበሻ የመጡት ሠላምን ፈልገው ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ ግን ቁረቡ በመባላቸው ሠላም ሊያገኙ አልቻሉም። በዚህ ምክንያት በየወቅቱ ከነበሩት አፄዎች ጋር ጦርነት ይገጥሙ ነበር። አፄዎቹ እናቁርባችሁ ሲሏቸው፣ እነሱ ደግሞ ማተባችሁን እናስበጥሳለን በማለት ለረጅም ጊዜ ጦርነት አካሂደዋል። ለጦርነት እንዲያመቻቸው ተራራማና ሠንሠለታማ ቦታዎች ላይ ሰፍረዋል። ሜዳውን የሚጠቀሙበት ለእርሻ ነበር (አሚኑ ኢድሪስ፣ ሸዋ ሮቢት፣ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ አስራ ስድስት

አርጐቦች ለረጅም ጊዜ ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ ነበር፡፡ ሀገር ለማስተዳደር ደግሞ አመች የሚሆነው ማዕከላዊ ቦታ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አርጐቦች ይፋት ወይም ሰሜን ሸዋ ላይ ለመስፈር ችለዋል፡፡ አርጐቦች በዋናነት ሰሜን ሸዋ ይኑሩ እንጂ፣ ከማዕከላዊ እስላማዊ መንግሥት (ይፋት ስርዎ መንግስት) እየተሾሙ የተለያዩ አካባቢዎችን ለማስተዳደር በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ይኖሩ ነበር፡፡ የእነሱ ቤተሰቦችም እስከ ዛሬ ድረስ በተለያዩ ቦታዎች ሰፍረው ይገኛሉ (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም፡፡

## ተረክ አስራ ሰባት

## አርጐቦች የባሪያ ንግድ ከማካሄዳቸው ጋር የተያያዘ

አርጐቦች በባሪያ ንግድ የታወቁ ነበሩ። አማራ ሀገር ሲገዛ ባሪያዎችን በማምጣት ለአርጐቦች ይሸጡላቸዋል። አሊያም እራሳቸው አርጐቦች ወደ መሀል ሀገር በመሄድ ባሪያዎችን አግበስብሰው ያመጣሉ። ከዚያም ወደ አረብ ሀገር በመውሰድ ይሸጡ ነበር (ወላስማ ሐጅ ኡመር መሀመድ እና ወላስማ ሐጅ ኑርሴን መሀመድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 እና 16 ቀን 2005 ዓ.ም.)።

## ተረክ አስራ ስምንት

## አርጐቦች እስልምናን ስለመመስረታቸውና ስለማስፋፋታቸው

የአርጐባ ተወላጆች ቀደም ሲል በንግድና በተለያዩ ምክንያቶች ከኢትዮጵያ ወደ ሳውዲ አረቢያ ይሄዱ ነበር፡፡ ነብዩ መሀመድ ሲወለዱ በሞግዚትነት ያሳደገቻቸው ከኢትዮጵያ የሄደች የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጅ ነበረች፡፡ የእስልምና ኃይማኖት መካ ላይ ሲጀመር የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ነብዮን ሲያገለግሏቸው የነበሩና በኋላም እስልምናን ለማስፋፋት በመጀመሪያ ከተላኩት መካከል የአርጐባ ተወላጆች ይገኙበታል፡፡ መካ ላይ የእስልምናን ኃይማኖት ለማስፋፋት አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ ነብዩ መሀመድ ተከታዮቻቸውን ወደ ሀበሻ ሂዱ ሲሏቸው ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት መካከል የአርጐባ ተወላጆች ይገኙበታል፡፡ የእስልምናን ኃይማኖት ለኢትዮጵያዊያን ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰበኩት መካከል አርጐቦች ግንባር ቀደሞች ናቸው፡፡ አርጐቦች እስልምናን ከሰበኩላቸው ሰዎች መካከል አልነጃሺ ይገኙበታል፡፡ አልነጃሺ እስልምናን የተቀበሉ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ መሪ ናቸው (ሼህ አህመድ አባቡሽ፣ ሾንኬ፣ ግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም.)።

## ተረክ አስራ ዘጠኝ

## አርጐቦች ዘመናዊ ትምህርት ካለመማራቸው ጋር የተያያዘ

በርካታ የአርጐባ ተወላጆች ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ አይደሉም፡፡ ቀደም ሲል ይሰጡ የነበሩ ትምህርቶች የእስልምና እምነት ተከታዮችን ከግምት ውስጥ ያስገባ አልነበረም፡፡ ከሚሰጡ የትምህርት አይነቶች መካከል "ግብረገብ" የተሰኘ ይገኝበታል፡፡ ይህ የትምህርት አይነት ስለክርስትና ኃይማኖት የሚሰብክ ነው፡፡ ወላጆችም የልጆቻቸው ኃይማኖት እንዳይበረዝ በመስጋት ወደ ትምህርት ቤት አይልኳቸውም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በኃይማኖት ትምህርት ብቻ ተወስንን እንድንቀር ሁነናል (ሐጅ ኡመር መሀመድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሃያ

## አርጐቦች ከተበደሩት እህል ላይ ቀንሰው ስለመስጠታቸው

በአርጐባ ማኅበረሰብ ችግር ከተከሰተ በርካታ እህል ያለው ብቻውን አይበላም፡፡ እህል ለመበደር የሚፈልጉ ሰዎች ተሰባስበው አንድ ተወካይ ይመርጣሉ፡፡ የመረጡትን ተወካይ ብዙ የእህል ክምችት እንዳለው ከሚታመን ሰው ጋር ያስተዋውቁታል፡፡

አበዳሪውም ከእሱ ፍጆታ በላይ ነው ብሎ የሚያምነውን እህል ለተወካያቸው ያስረክባል፡፡ ተወካዩም ከአበዳሪው እህሉን ሰፍሮ በመረከብ ለመበደር ለሚፈልጉ ሰዎች በሙሉ እየሰፈረ እኩል ያካፍላቸዋል፡፡

ተበዳሪዎች የምርት ወቅት ሲደርስ ከተበደሩት የእህል መጠን ላይ ትንሽ ትንሽ በመቀነስ ይመልሳሉ፡፡ ከተበደሩት መጠን ላይ የተወሰነ እህል የሚቀንሱት የተበደሩት እህል በጐተራ ወይም በጉድጓድ የቆየ ከሆነ ነው፡፡ እህሉ በጐተራ ወይም በጉድጓድ ረጅም ጊዜ ሲቆይ የተበላሸ እህል ሊኖረው ይችላል፡፡ የተበላሸ ካላ ደግሞ አበዳሪው የሌሎችን ገንዘብ በትርፍ መውሰድ የለበትም ብለው ያምናሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ትንሽ ትንሽ እህል በመቀነስ ይመልሳሉ (አብዱሰላም ከማል፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሃያ አንድ

## ከዚያራ በዓል አከባበርን ጋር የተያያዘ

የአርጐባ ማኅበረሰብ ከሚያከብሩት ባህላዊ በዓላት መካከል ዋነኛው የዚያራ በዓል ነው፡፡ የዚያራን በዓል የሚያከብሩት በዓመት ሁለት ጊዜ ነው፡፡ የመጀመሪያው የዚያራ በዓል የሚከበረው በጥቅምት ወር ነው፡፡ ይህ ወር ገበሬዎች እሸትና አገዳ የሚያገኙበት ወቅት ነው፡፡ እሸትና አገዳው ወደ ቤተ ከመግባቱ በፊቱ የአርጐባ ተወላጆች በየመንደራቸው በመሰባሰብ ያቅማቸውን ያህል እህል ያዋጣሉ፡፡ የተዋጣው እህል በመስጊድ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ በተዘጋጀው ምግብ ሽማግሌዎች ዱአ (ፀሎት) ያደርጋሉ፡፡ ዱአ ከተደረገ በኋላ ሴት፣ ወንድ፣ ህፃን፣ ሽማግሌ ሳይባል ሁሉም በመሰብሰብ ይበላሉ፡፡ በዚያራው ላይ በልዩ ልዩ ምክንያት ላልተገኙ ሰዎች በየቤታቸው እንዲላክላቸው ይደረጋል፡፡ ይህን በዓል የሚያከብሩት በመንደሩ የሚኖሩ አቅመ ደካሞችና የእርሻ መሬት የሌላቸው ድሀ የአርጐባ ተወላጆች የዓመቱን ሰብል፣ እሸትና አገዳ መቅመስ እንዲችሉ ነው፡፡

ሁለተኛው የዚያራ በዓል የሚከበረው በታህሳስ ወይም በጥር ወር ነው፡፡ ይህ ወቅት የተመረጠበት ምክንያት የእርሻ መጀመሪያ በመሆኑ ነው፡፡ ማንኛውም ገበሬ እርሻ ከመጀመሩ በፊት የአቅማቸውን ያህል ብር እንዲያዋጡ ይደረጋል፡፡ በተሰበሰበው ገንዘብ ለእርድ የሚሆን በግ፣ ፍየል ወይም በሬ ይገዛል፡፡ የተገዛው የእርድ ከብት በመስኪድ ውስጥ ይታረድና ሽማግሌዎቸው ዱኣ ያደርጋሉ፡፡ የሰፈሩ ነዋሪዎች ይበላሉ ይጠጣሉ (አብዱሰላም ከማል፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሃያ ሁለት

## አርጐቦች ኢትዮጵያን ከ700 ዓመት በላይ ስለማስተዳደራቸው

አርጐቦች ኢትዮጵያን ከ7ኛው እስከ 13ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ አስተዳድረዋል፡፡ አርጐቦች ሀበሻን በእስልምና ኃይማኖት መሠረት ሲያስተዳድሩ ዋነኛ መቀመጫቸው መሀል ኢትዮጵያ ሸዋ ነበር፡፡ በዚህን ወቅት የመጀመሪያ መሪያቸው ኡመር ወላስማ ይባላል፡፡ ኡመር ወላስማ የበኒ ሀሽም ጐሳ ተወላጅ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ያስተዳደሩት የአርጐባ ነገዶች በኒ ሀሽም፣ በኒ መጦሊብ፣ በኒ አቂል ይባላሉ፡፡ እነዚህ ነገዶች ኢትዮጵያን ተራ በተራ የመሩ ሲሆን፣ በዚህ ዘመን የሀበሻ ግዛት በመባል የሚታወቀው በሰሜን እስከ ቀይ ባህር፣ በምስራቅ እስከ ጅቡቲና ሶማሊያ፣ በደቡብ፣ እስከ ዳውሮ፣ ሐድያና ከምባታ ድረስ ነበር፡፡ ያኔ ሀበሻ ሲባል ሶማሊያን፣ ጅቡቲን፣ ሱዳንንና ኤርትራን ጨምሮ እስከ ኬንያ ድረስ ያለውን ያጠቃልላል፡፡ ኡመር ወላስማ እስላማዊ ስርዎ መንግስት መስርተው እነዚህን ሀገሮች በሙሉ አንድ አድርገው መርተዋል፡፡ እኒህ መሪ ኢትዮጵያን ሲያስተዳድሩ በ2ሺህ 750 የጦር አበጋዞችና ኡላማዎች አመራር ስር 240 ሺህ የተደራጀ ፈረሰኛና እግረኛ ጦር ነበራቸው፡፡ በዚያን ጊዜ እንደ አሁኑ ክልል ወይም ክፍለ አገር የሚባል አልነበረም፡፡ ሁሉም ማኅበረሰቦች ባህላቸውን፣ ቋንቋቸውንና መልካም ምድራዊ አቀማመጣቸውን መሰረት በማድረግ ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ አድርገዋል፡፡ ኡመር ወላስማ ማዕከላዊ መንግስቱን በበላይነት ይዘው ሌሎች ክልሎችን እያስገበሩ ይኖሩ ነበር፡፡ በአጠቃላይ 25 የአርጐባ ተወላጆች እየተፈራረቁ በመንገስ ኢትዮጵያን ለ750 ዓመት ያህል የመሯት ሲሆን የመጨረሻውና 25ኛው የአርጐባ ንጉስ ሳሉዲን ይባላል፡፡

ይህ ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክ ተጽፎ አይገኝም፡፡ እንዲያውም "የጨለማው ዘመን" ብለውታል፡፡ የጨለማው ዘመን ያሉት ቀደም ባሉት ጊዜያት የቤተ መንግሥት ታሪክ ፀሐፊዎች የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ የክርስትና እምነት ተከታዮች ስልጣን ከያዙ በኋላ የእስልምና ታሪክ መፃፍ የለበትም ብለው ያምኑ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ በአርጐቦች (በእስላማዊ መንግሥት) ስትደዳደር የነበረበትን ወቅት ታሪክ በማጥፋት "የጨለማው ዘመን" በማለት አልፈውታል፡፡ የክርስትና እምነት ተከታይ ነገስታት ይህን ታሪክ ቢያጠፉትም በአረብኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በጣሊያንኛና በፈረንሰኛ ቋንቋ የተፃፉትን ግን ማጥፋት ስላልቻሉ ይህ ታሪክ ተደብቆ አልቀረም (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሃያ ሦስት

## አርጐቦች በተለያዩ ስያሜ ከመጠራታቸው ጋር የተያያዙ

የአርጐባ ማኅበረሰብ ለብዙ ዘመናት የሀገርና የኃይማኖት መሪ ሆነው ቆይተዋል፡፡ በመሪነት ዘመናቸው በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ተሰራጭተው አስተዳድረዋል፡፡ የመሪነት ስልጣናቸው በሌሎች ገዥ መደቦች ሲነጠቁ ከፍተኛ የሆነ ጫናና መፈናቀል ሊደርስባቸው ችሏል፡፡ የአፄዎች ብትር ሲያርፍባቸው እና ጫናው እየበረታባቸው ሲመጣባቸው ማንነታቸውን ለመካድ ተገደዋል፡፡ እኔ አርጐባ ነኝ ከማለት ይልቅ እኔ አሲፉ ፣ነኝ፣ እኔ ዶባ ነኝ፣ እኔ ሙዝገዬ ነኝ፣ እኔ አምባ አይፈራ ነኝ፣ እኔ ኩላያ ነኝ፣ እኔ ሸጉራ ነኝ፣ እኔ ቀሪቦ ነኝ በማለት በአካባቢያቸው ስያሜ ሲጠሩ ቆይተዋል፡፡ በተለይም ከአጼ ምኒልክ በፊት በነበሩ ስርዓቶች የብሔራቸውን ስም ደብቀው ኑረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ቋንቋቸውንና ባህላቸው በሌሎች ማኅበረሰቦች ሊዋጥ ችሏል፡፡ ሐይማኖታቸውን ግን ሳይለውጡ እንደያዙ ለመዝለቅ ችለዋል (ሼህ መሀመድ አወል፣ አንኮበር፣ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሃያ አራት

የአርጐባ ጐሳዎች በጣም ብዙ ነው። ደቡብ ወሎ ውስጥ አሲፉ፣ ሸንኮር ፋራ፣ አባስያ እና አባሙራስ የሚባሉ ጐሳዎች ይገኛሉ። ከሾንኬ ጀምሮ ወደ መርሳና ትግራይ አካባቢ አባሙራስና ሸንኮር ፋራ የሚባለውን የዘር ግንድ እናገኛለን። ቃሉ ላይ አሲፉ፣ አባስያንና አባሙራስ ይገኛሉ። ከሰሜን ሸዋ ጀምሮ እስከ ሐረር ድረስ የሚገኙት የወላስማ ጐሳ አባላት ብቻ ናቸው (አሚኑ ኢድሪስ፣ ሸዋ ሮቢት፣ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም.)።

## ተረክ ሃያ አምስት

የአርጐባ ማኅበረሰብ በሦስት ጐሳዎች የተከፈለ ነው፡፡ እነዚህ ጐሳዎችም በኒ ሐሽም፣ በኒ አቂል እና በኒ ሙጠሊብ ይባላሉ፡፡ ሦስቱም ጐሳዎች የነብዩ መሀመድ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ የስደት ታሪካቸው ወደ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም የአረቡ ዓለም ተሠራጭተው የሚገኙ የተበታተኑ ጐሳዎች አድርጓቸዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የእነዚህ ጐሳ አባላት በተለያየ አካባቢ በተለያየ ስም ይጠራሉ፡፡ ስያሜያው የተሰጣቸው እንደሚኖሩበት አካባቢ እና እንደ ስልጣን ደረጃቸው ነው፡፡

የመጀመሪያው አሲፋ በመባል ይታወቃል፡፡ በአርጐብኛ ቋንቋ አ ማለት "ይህ" ማለት ሲሆን ሲፋ ደግሞ "መድሀኒት" ማለት ነው፡፡ ኢሲፋ ማለት ወደ አማርኛ ሲመለስ "ይህ መድሀኒት" እንደማለት ይሁን እንጂ፣ በዚህ ስያሜ የሚታወቁት ባለስልጣኖችና ቤተሰቦቻቸው ናቸው፡፡ የአሲፋ ጐሳ ከተባለ የባለስልጣን ጐሳ ማለት ነው፡፡ ስልጣኑ በዘር የሚወረስ ሳይሆን በምርጫ የሚገኝ ነው፡፡ የአርጐባ ማኅበረሰቦች ተሰብስበው በአመራር ብቃቱ እና በአስተዳደር ችሎታው ይመጥናል ያሉትን ሰው ይመርጣሉ፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ በዘሩ ምክንያት በመሪነት ቦታ ላይ የሚቀመጥ ሰው የለም፡፡ ምክንያቱም ህግ አለን፡፡ ህጋችን ቁርዓን ነው፡፡ በቁርዓን ህግ መሰረት በአግባቡ የማይመራ መሪን ህዝቡ ከስልጣን ያነሳዋል፡፡ ከስልጣን በተነሳው መሪ ምትክ ሌላ ይመርጣሉ፡፡ በዚህ መልኩ በመሪነት ያገለገሉ ሰዎች ዝርያዎች አሲፋ በመባል ይጠራሉ፡፡

ሁለተኛው ዶባ ይባላል፡፡ ዶባ ማለት የበሰለ ብርቱካን ቀለም ያለው ማለት ነው፡፡ በዚህ ስም የሚጠሩትም በጣም ቀይ የሆኑትን ወይም የበሰለ ብርቱካን የሚመስሉትን የማኅበረሰቡን ተወላጆች ነው፡፡

ሶስተኛው ሙዝገዬ ይባላል፡፡ "ገዬ" ማለት በአርጐብኛ ቋንቋ ሀገር ማለት ሲሆን፣ ሙዝገዬ " የሙዝ ሀገር" እንደ ማለት ነው፡፡ በዚህ ስያሜ የሚታወቁት በብዛት አትክልትና ፍራፍሬ በሚገኝበት አካባቢ የሚኖሩ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ናቸው፡፡ በጣም ቀያዮች አይደሉም፡፡

አራተኛው አምባ አይፈራ በመባል ይታወቃል፡፡ አምባ አይፈራ ማለት የጦር ምሽግ የሆነ ተራራ የማይፈራ ወይም ጦር የማይፈራ ማለት ነው፡፡ በዚህ ስያሜ የምንጠራቸው ጀግኖችንና በጣም ተዋጊ የሆኑ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆችን ነው፡፡

አምስተኛው ኩላያ ይባላል፡፡ ኩላያዎች ማለት መልካቸው ጠይም የሆኑ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ናቸው፡፡ ጠያይም የሆኑ የማኅበረሰቡ ተወላጆች የኩላያ ቤተሰቦች በመባል ይጠራሉ፡፡

ስድስተኛው ሸጐሬ ይባላል፡፡ ሸጐሬ ማለት በአረብኛ የቀሀ እንደማለት ነው፡፡ በዚህ ስያሜ የሚታወቁት በወይናደጋ አካባቢ የሚኖሩ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ሲሆኑ ቋንቋቸውም ከሌሎች የአርጐባ ተወላጆች ትንሽ ለየት ይላሉ፡፡

ሰባተኛውና የመጨረሻዎች ቀሪቦ ይባላሉ፡፡ ቀሪቦ በመባል የሚታወቁት ኃይማኖታቸውን በጣም የሚያጠብቁት ናቸው፡፡ እነዚህ የማኅበረሰቡ አባላት ለፈጣሪ በጣም የተጠጉ ናቸው ተብሎ በአርጐቦች ዘንድ ይታመናል (ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሃያ ስድስት

## አህመድ ግራኝ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጅ ስለመሆናቸው

ግራኝ አህመድ እውነተኛ ስማቸው አህመድ ኢብኑ ኢብራሂም ጋራድ ነው፡፡ ኢብራሂም ጋራድ አባታቸው የሶማሌ ሐውዬ ጐሳ ተወላጅ ሲሆኑ፣ በእናታቸው ግን የአርጐባ ተወላጅ ናቸው፡፡ ስማቸውም አሚና ይባላል፡፡

የኢብራሂም ጋራድ እናት የኡመር ወላስማ 25ኛ የልጅ ልጅ የሆነው ንጉስ ሳዕዱዲን እህት ናቸው፡፡ ሳዕዱዲን በጣም ብልህና አዋቂ ንጉስ ነበሩ፡፡ የክርስቲያኖች ጦር በጣም ስለአስቸገራቸውና ጦርነቱ ስለተራዘመባቸው ትንፋሽ ለማግኘት ሲሉ ከሐረሪዎች ጋር በመሆን ጀጐልን ገንብተው ሐረር ተቀመጡ፡፡ እዚያ ተቀምጠው እያለ አፄ ልብነ ድንግል ከትግራይ ጫፍ ጀምሮ እስከ አዋሽ ድረስ 11 ሺ.ህ 500 መስጊዶችን እየወረሩ በዘመቻ አቃጠሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ንጉስ ሳዕዱዲን ከ7 ሱልጣኖች የተውጣጣ 240 ሺ.ህ ጦር ነበራቸው፡፡ የዚህ ጦር መሪ ኢብራሂም ጋራድ ነበሩ፡፡ ወቅቱ የአውሮፓ ሀገሮች የእስልምና ተከታይ ሀገሮችን ተቆጣጥረው ስለነበር ከአረብ ሀገሮች እርዳታ ለማግኘት አስቸጋሪ ነበረ፡፡ በዚህ ምክንያት ንጉስ ሳዕዱዲን "ጦርነት ከምንገጥም የተቃጠሉ መስጊዶችን እንዲገነቡ በማድረግ ሙስሊሙን ኅብረተሰብ እናረጋጋ፡፡ ቀስ ብለን ሰራዊታችንን አጠናክረን ጦርነት ብንጀምር ይሻላል" የሚል ፍላጐት ነበራቸው፡፡ የንጉሱ ሀሳብ ግን የጦር መሪ ለነበሩት ኢብራሂም ጋራድ አልተዋጠላቸውም፡፡ በዚህ ተበሳጭተው ንጉስ ሳዕዱዲንን በማሰር ጦርነት አወጁ፡፡ ኢብራሂም ጋራድ በጦርነት አሸናፊ በመሆን ወደ ፊት ገሰገሱ፡፡ ጐጃም አካባቢ ሲደርሱ አጼ ልብነ ድንግል ሸሽተው ጐንደር ውስጥ ቆላድባ በተባለ አካባቢ ወደሚገኝ በረሀ ገቡ፡፡ በበረሀ ውስጥ ተቀምጠው ለቫቲካን ሮማ የድረሱልኝ ጥሪ ላኩ፡፡ ሆኖም የቫቲካን ጦር ሳይመጣ በተሸሸጉበት በርሀ ውስጥ እንዳሉ አጼ ልብነ ድንግል ሞቱ፡፡

ከዚህ በኋላ ኢብራሂም ጋራድ ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ተቆጥረው ሙሰስሊሙን ኅብረተሰብ በማረጋጋት የፈረሱ መስጊዶችን ያስገነቡ ሲሆን፣ ለ16 ዓመት ያህል ኢትዮጵያን በመልካም ሁኔታ በሸሪዓ ህግ አስተዳድረዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሀገሪቱን

እየመሩ እያለ የአጼ ልብነ ድንግልን ልጅ የሚረዱ በርካታ የቫቲካን ሮማ ወታደሮች 9 ጥይት የሚጐርስ ውጅግራ የሚባል ጠብመንጃ ይዘው መጡ፡፡ እነዚህ ወታደሮች ኢብራሂም ጋራድን ሲንቀሳቀሱ አድፍጠው በመሳሪያ በመምታት ገደሏቸው፡፡ ንጉስ ሳዕዱዲም ኢብራሂም ጋራድ ከሞተ ከ2 ዓመት በኋላ ሞቱ፡፡ ከዚህን ጊዜ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው እስላማዊ ሱልጣኔት ጠፋ፡፡

ኢብራሂም ጋራድ ከሞቱ በኋላ የክርስቲያን ታሪክ ፀሐፊዎች "ወራሪ ነው" ይሏቸዋል፡፡ ወራሪ ማለት እንደፋሽስት ኢጣሊያ ከውጭ አገር የመጣ እንጂ፣ እንደ አህመድ ግራኝ ላለ የአገር መሪ እና ማለፊያ አስተዳዳሪ የሚሰጥ ስም አይደለም (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሃያ ሰባት

በተለያየ ጊዜ የነበሩ አጼዎች በርካታ አርጐቦችን እና የእስልምና እምነት ተከታዮችን ደመሰሱ፡፡ ከምጽዋ እስከ በርበራ ድረስ ያሉትን መስጊዶች በሙሉ አቃጠሉ፡፡ ከዚያ በኋላ (በመካከለኛው ዘመን) አጼ ልብነ ድንግል ደግሞ ቀደም ሲል የነበሩ ነገስታት የፈፀሙትን ተግባር ደገሙት፡፡ ይህ ሁኔታ ያስቆጣው አህመድ ግራኝ ለበቀል ተነሳ፡፡ አህመድ ግራኝ በእናቱም ሆነ በአባቱ ሙሉ በሙሉ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጅ ነው፡፡ ይህን የምልበት ምክንያት በጣሊያን ጊዜ ሽማግሌዎች ዘራችንን ሲቆጥሩ አዳምጥ ስለነበር እሱን መሰረት አድርጌ ነው፡፡ በርካታ ሽማግሌዎች ዘር ሲቆጥሩ አህመድ ግራኝን የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጅ መሆኑን ይናገሩ ነበር፡፡ አህመድ ግራኝ መንግስቱን ተቆጣጥሮ እስከ ምጽዋ ድረስ የሚገኙ ቤተ-ክርስቲያኖችን በሙሉ አቃጠለ፡፡ እሱ በስልጣን ላይ እያለ ቱርኮች ወደ ኢትዮጵያን ሲመጡ አህመድ ግራኝ እንዳይገቡ ተከላከለ፡፡ በኋላ ላይ "ክርስቲያኖች ሲሶ መንግሥት እንሰጣችኋለን" በማለት ፖርቱጋሎችን አስገቧቸው፡፡ በዚህ ምክንያት አህመድ ግራኝ በመሞቱ ክርስቲያኖች የበላይነት አገኙ፡፡ ከዚህ በኋላ አጼዎች ስልጣን በያዙ ቁጥር በአርጐቦች ላይ ችግር እየፈጠሩ ለረጅም ጊዜ ኑረዋል፡፡ (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም)።

## ተረክ ሃያ ስምንት

## ከሼህ ጦለሃ ጃእፈር ጋር የተያያዙ

ሼህ ጦለሃ ጃእፈር ከአርጐባ የኃይማኖት መሪዎች መካከል ትልቁና ዋነኛው የሆኑት የዩሱፍ ወይም አባ ስያ የሚባሉት የልጅ ልጅ ናቸው፡፡ የተወለዱትም አሁን በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ተብሎ በሚታወቀው ዞን ስር በሚገኘው የአርጐባ ልዩ ወረዳ 02 ቀበሌ ጐጥ ስር ዋሻ በምትባል ቦታ ነው፡፡ ሼህ ጦለሃ ዕድሜያቸው ወደ 30 ዓመት አካባቢ ሲደርስ አፄ ዮሃንስ የተባሉ ንጉስ በኢትዮጵያ ነገሱ፡፡ በዚህ ወቅት 'ያላማተበ፣ ክርስቲያን ያልሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር አይችልም' ተባለ፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አንገቱ ላይ መስቀል ያለው ማተብ ማሰር አለበት አሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም በእስልምና እምነት ተከታዮች በተለይ ደግሞ በአርጐባ ማኅበረሰብ ላይ ከፍተኛ የሆነ እልቂትና መከራ ደረሰ፡፡ ቀደም ሲል "የእስላም ሀገሩ መካ፣ የወፍ ሀገሩ ዋርካ" የሚል ሀሳብ በፍትሃ ነገስት ላይ ተቀምጦ ነበር፡፡ ይህን አባባል ተፈፃሚ ለማድረግ "ሙስሊም ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር አይቻልም" የሚል አዋጅ ወጣ፡፡ ይህ ጉዳይ ሼህ ጦለሃ ጃእፈርን እንቅልፍ ሊያስተኛቸው አልቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት ጦር አደራጅተው በወቅቱ የደሴ አካባቢ የጦር መሪ ከነበሩት ከባላምባራስ በጀሮንድ ነውጤ ጋር ጦርነት ገጠሙ፡፡ የአፄ ዮሃንስ ጦር ከፍተኛና በሚገባ የተደራጀ ይሁን እንጂ፣ ሼህ ጦለሃ ጫካ ውስጥ ጉድጓድ ቆፍረው እሳር እያለበሱ የንጉሱ ሠራዊት አካል የሆነው የባላምባራስ በጀሮንድ ነውጤ ፈረሰኛ ጦር እየጋለበ ሲመጣ ጉድጓድ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ከፍተኛ ጥቃት አድርሰውበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰሜን ወሎ ውስጥ ራያና ወልዲያ አካባቢ እንዲሁም ሰሜን ሸዋና ትግራይ ላይ ፊት ለፊት ጦርነት በመግጠም በአፄ ዮሃንስ ጦር ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት አድርሰዋል፡፡

ሼህ ጦለሃ ይንቀሳቀሱ የነበረው የእስልምና እምነት ተከታዮች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ስለሆነ ኅብረተሰቡ ከፍተኛ የሆነ ድጋፍና እርዳታ ያደርግላቸው ነበር፡፡ በተለያዩ ቦታዎች እየተንቀሳቀሱ በአፄ ዮሃንስ ጦር ላይ ጉዳት በማድረስ ለ14 ዓመት ያህል እንደተዋጉ በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ድርቅ ተከሰተ፡፡ በድርቁ ምክንያት ሠራዊታቸው ስለተበተነ መዋጋት በማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ፡፡ ከዚያም የተወሰኑ ተከታዮቻቸውን በመያዝ ወደ ሱዳን ሄዱ፡፡ በዚያን ወቅት በሱዳን ማህዲ የሚባል መሪ ነበር፡፡ ለማህዲ አፄ ዮሃንስ እስልምናን ለማጥፋት እየፈፀሙ ያለውን በደል በዝርዝር አስረዱት፡፡ እስልምናን ለማዳን ለ14 ዓመት ትግል ማካሄዳቸውንና ከውጪ አገራት ድጋፍ ማግኘት እንዳልቻሉም ገለጹለት፡፡

ማህዲም "እኛ እንረዳቸኋለን!" ብሎ ቃል ገባላቸው፡፡ ከዚያም ለ6 እና ለ7 ወራት ያህል ሱዳን እንደተቀመጡ ሼህ ጦለሃ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ጦራቸውን አደራጅተው ከ6 ወር በኋላ ወሎ አካባቢ ጦርነት እንዲጀምሩ ከማህዲ ጋር ተስማሙ፡፡ "እናንተ እዚያ ጦርነት ስትጀምሩ እኛ እንደርስላችኋለን" በማለት ነበር ማህዲ ያሰናበታቸው፡፡

ሼህ ጦለሃ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ድርቁ አልፎ ሰው ተረጋግቶ አገኙት፡፡ ጦራቸውን እያደራጁ ከቆዩ በኋል በስድስተኛው ወር ላይ ደሴ አካባቢ ደረቅ ወይራ በሚባል ስፍራ ከባላምባራስ በጀሮንድ ነውጤ ጋር ጦርነት ጀመሩ፡፡ በጦርነቱም በርካታ ቤተ ክርስቲያኖችን አቃጠሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ባላምባራስ በጀሮንድ ነውጤ ሀይል እንዲጨመርላቸው ለአፄ ዮሃንስ ላኩባቸው፡፡ የአፄ ዮሃንስ ከፊል ጦር ባላምባራስ በጀሮንድ ነውጤን ለመርዳት ወደ ወሎ ሲጓዝ የማህዲ ጦር በመተማ አድርጎ ጉንደር በመግባት ከአፄ ዮሃንስ ዋና ሠራዊት ጋር ጦርነት አካሄደ፡፡ መንገድ ላይ የነበረው የአፄ ዮሃንስ አጋዥ ጦር ለበጀሮንድ ሳይደርስ ማህዲስቶች የአፄ ዮሃንስ ጦርን ድል ነስተው የንጉሱን አንገት በመቁረጥ ወደ ሱዳን ተመለሱ፡፡

ከአፄ ዮሃንስ ሞት በኋላ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ወደ ስልጣን መጡ፡፡ በዚህ ወቅት ሼህ ጦለሃ በአፋርና በኢሳ በኩል ከጅቡቲ አንድ ሺ ህ የሚጠጋ "ውጅግራ" የተሰኘ መሳሪያ በእርዳታ አገኙ፡፡ ባገኙት የጦር መሳሪያ በመበረታታት ጦራቸውን መልከሰዲ በሚባል ቦታ በአዲስ መልኩ አደራጅተው ለጦርነት መዘጋጀት ጀመሩ፡፡

በዚያን ጊዜ በመንግሥትም ሆነ በኀብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ተቀባይነት ያላቸው ሼህ ኑርዬ ኡመር የሚባሉ ሰው ነበሩ፡፡ እርሳቸውን አፄ ምኒልክ ፈለጓቸውና ወደ ቤተ መንግሥት ተጠርተው ሄዱ፡፡ አጼ ምኒልክ "እንደዚህ አይነት ችግር ገጥሞኛል፤ ይህን ደግሞ የምትፈቱት እናንተ ናችሁ" አሏቸው፡፡

ሼህ ኑርዬ ግን "ከዚህ በፊት መፍታት የሚገባን ሌላ ችግር አለ" ብለው መለሱ፡፡

አጼ ምኒልክ "ከጦለሃ ጋር ታረቅ አይበሉኝ እንጂ፣ ከዚህ ወጪ ከሆነ ምንም ችግር የለውም" አሏቸው፡፡

ሼህ ኑርዬ "እኔም የምፈልገው ይህንኑ ነው" የሚል መልስ ሰጡ፡፡

አጼ ምኒልክ "የጦለሃ የአባቱ እናት የእኛ ዘመድ ናት፡፡ እሱም ይህን ያህል ዓመት የተዋጋው የአባቱን እናት ስልጣን ለመውሰድ ነው ከእሱ ጋር እንዴት እታረቃለሁ? እኔ ስልጣን ለቅቄ? ወይስ ስልጣኔን አካፍየው ነው?" አሏቸው፡፡

ሼህ ኑርዬም "ጦለሃ እኮ የሚፈልገው ስልጣን አይደለም፡፡ ጭቃ ሹምነት እንኳን አይፈልግም፡፡ እሱ የሚፈልገው የኃይማኖት ነፃነት ነው፡፡ ፍትሃ ነገስት 'የእስላም ሀገሩ መካ ነው' ስለሚል በአፄ ዮሃንስ ዘመን ሙስሊሙ ኅብረተሰብ በሐይማኖቱ ሰበብ ከፍተኛ የሆነ ስቃይና መከራ አይቷል" በማለት አስረዱ፡፡

አጼ ምኒልክ "እውነት ነው ወይ?" ሲሏቸው፣

ሼህ ኑርዬም "አዎ" ብለው መለሱ፡፡

አጼ ምኒልክ "ይህ ነገር እውነት ከሆነ መክሬ መልሱን ነገ እነግረዎታለሁ" ብለው አሳደሯቸው፡፡ ከዚያም አጼ ምኒልክ ብልህ የሆነች ባለቤት ነበረቻቸውና ከባለቤታቸው ጋር ተማክረው አደሩ፡፡ ባለቤታቸውም ይህን ሀሳብ ስለደገፉት "የእስላም ሀገሩ መካ፣ የወፍ ሀገሩ ዋርካ" የሚለው አዋጅ ተሽሮ "ኃይማኖት የግል ነው አገር የጋራ ነው" የሚል አዋጅ ታወጀ፡፡ ይህ አዋጅ የእምነት ነፃነትን ከማስከበሩ በላይ በጊዜው የነበረውን ጦርነት፣ እልቂትና ስደት አስቆሟል፡፡ ይህ ትልቅ ብልህነት ነው፡፡ ሼህ ጦለሃ በዚህ ሁኔታ ከአጼ ምኒልክ ጋር ታርቀው እስከ አጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ የቆዩ ሲሆን በመጨረሻ ታመው ጣሊያን ከመምጣቱ በፊት አርፈዋል (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሃያ ዘጠኝ

የክርስትናን ኃይማኖት ያልተቀበለ ኢትዮጵያን ለቆ ይሂድ የሚል አዋጅ ያወጡት አጼ ዮሃንስ በነገሱበት ዘመን ጌታው ጦለሃ ወሎ አርጐባ ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ የአርጐባ ተወላጆችን ሰበሰቡና "ቁርባችሁ ክርስቲያን ሁኑ እየተባለ ነው፣ ምን ይሻለናል?" ይሏቸዋል፡፡ በዚህን ጊዜ "በሐይማኖታችን ከመጣ ሴት ወንድ ሳንል እንዋጋለን" የሚል ምላሽ ያገኛሉ፡፡ ይህን ሲያደርጉ የአፄ ዮሃንስ ሁለት ሰላዮች ሰምተው ኖሮ ሄደው ለጌታቸው ይናገራሉ፡፡ አፄ ዮሃንስ ጦራቸውን ይዘው በመምጣት ወሎ አርጐባ አካባቢ ይሰፍራሉ፡፡

በመቀጠልም የአርጐባ ተወላጅ የሆነ በሙሉ እንዲመጣ ትዕዛዝ ይሰጣሉ፡፡ ጌታው ጦለሃ ቃል የገቡትን የአርጐባ ተወላጆች ሰብስበው “ምን ይሻለናል?” ይሏቸዋል፡፡ ተወላጆችም “እኛ መሳሪያ የለንም፡፡ ያለነው ባዶ እጃችንን ነው፡፡ ኃይላችንም የማይረባ ነው፤ ስለዚህ ‘እሺ’ ብለን ክርስትናን እንቀበልና ውስጥ ውስጡን የራሳችንን ኃይማኖት እናራምድ” የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡

ጌታው ጦለሃም “ያኔ ምን ነበር ያላችሁት? ‘በአፈር በቅጠሉም ቢሆን እንዋጋለን’ አላላችሁም ወይ?” በማለት ያፋጥጧቸዋል፡፡ በኋላም ወጣቶችን ለይተው በመሰብሰብ “እንዴት ነው ሲሏቸው?” ወጣቶችም፣ “አንተ እንዳሉ” ይሏቸዋል፡፡ “እንግዲያውስ ባለን መሳሪያ እንግጠም” የሚል ስምምነት ላይ ይደርሳሉ፡፡

በጌታው ጦለሃ መሪነት ወጣቶች ሲዋጉ ጥቂት በመሆናቸው ዙሪያውን ይከበባሉ፡፡ ከዚያም ይማከሩና እጅ ከመስጠት ማምለጥ እንሚሻል ወሰኑ “እኔን ተከተሉኝ” በማለት ሰልለው የአፄ ዮሃንስ ጦር በሳሳበት በኩል እየተዋጉ ሰብረው አመለጡ፡፡ ከዚያን ቀን በኋላ እያደፈጡ በአጼ ዮሃንስ ጦር ላይ አደጋ ማድረስ ጀመሩ፤ ብዙ ጊዜም ፊት ለፊት ተዋግተው ድል አድርገዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ረጅም ጊዜ ከቆዩ በኋላ አፄ ዮሃንስ በኃይማኖት ሰበብ አንገታቸው ተቆርጦ ተገደሉ፡፡

አፄ ምኒልክ ንጉሰ ነገስት ተብለው ሲነግሱ “ኃይማኖት የግል ነው፤ ሀገር የጋራ ነው” ብለው አወጁ፤ “ጦለሃም የፈለገውን እናደርግለታለን፤ ይግባ” አሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ጌታው ጦለሃ ከአጼ ዮሃንስ ሠራዊት ጋር ጦርነት በመግጠም ሲዘርፉ፣ “ዘረፋው የእስልምና ኃይማኖት በሚያዘው መንገድ ይሁን” ሲሉ ተከታዮቻቸው ሊቀበሏቸው ስላልቻሉ ይናደዱ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ አጼ ምኒልክ የእርቅ ጥያቄ ሲያቀርቡላቸው ለመደራደር ፈቃደኛ ሆኑ፡፡ ሰራዊታቸው ባያበሳጫቸው ግን ለመታረቅ አይፈልጉም ነበር ይባላል፡፡

ጦለሃም “እኔ ሹመት አልፈልግም፤ የምፈልገው ሐይማኖቴ እንዳይነካ ነው፡፡ ቀደም ሲል የክርስትና ኃይማኖትን ተከተሉ የሚል አዋጅ ታውጇል፡፡ አሁን ደግሞ ‘ኃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው’ የሚለው አዋጅ በየገበያው ይታወጅ፣ አለበለዚያ አልገባም” አሉ፡፡ አፄ ምኒልክም በየገበያው እንዲታወጅ አደረጉ፡፡ ከዚያ በኋላ ከአፄ ምኒልክ ጋር እርቅ አድርገው ገቡ፡፡ ሰፊ መሬትም ተሰጣቸው፡፡ ከዚያ በኋላ በሰላምና በደስታ እስከ አፄ ኃለስላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ ኖረው ሞቱ (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋ ሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሠላሳ

## የጦለሃ አያት የአፄ ምኒልክን የእህት ልጅን ስለማግባታቸው

አጼ ምኒልክ ይኖሩ የነበረው በአንኮበር ነው፡፡ አንኮበርና አልዩ አምባ ደግሞ ያላቸው ርቀት 15 ኪሎ ሜትር ነው፡፡ አባስያ ከዚህ (መዲና) ተነስተው ወደ አልዩ አምባ ይሄዳሉ፡፡ አባስያ ማለት የጦለሃ አያት ናቸው፡፡ አባስያ ወደ አልዩ አምባ በሄዱበት ወቅት የአፄ ምኒልክ የእህት ልጅ የአልጋ ቁራኛ ሆና ትኖር ነበር፡፡ ይህች ልጅ በጣም የምታምርና ቆንጆ ስትሆን፣ ከ12 ዓመቷ ጀምሮ አጋንንት ስለሰፈረባት መንቀሳቀስም ሆነ መናገር አትችልም ነበር፡፡ በእሷ ህመም ምክንያት ቤተሰቦቿና ዘመዶቿ በጣም ተሰቃይተዋል፡፡ ከያዛት አጋንንት ለማላቀቅ በርካታ ቀሳውስትና ደብተራዎችን ጥረት አድርገው የነበረ ቢሆንም ሊሳካላቸው ግን አልቻለም ነበር፡፡

በወቅቱ አባስያ በጣም የሚፈሩና የሚከበሩ ሰው ይሁኑ እንጂ፣ እምብዛም ወደ ቤተ መንግሥት የሚጠጉ አልነበሩም፡፡ የአባስያን አልዩ አምባ መምጣት የሰሙት ምኒልክ መላክተኛ ልከው አስጠሯቸው፡፡ አባስያ አንኮበር ሲመጡ ምኒልክ የእህታቸው ልጅ ስላለችበት ሁኔታ በመግለጽ ፀሎት እንዲያደርጉላት ፈልገው እንዳስጠሯቸው ገለጹላቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ልጅቱ 18 ዓመት ሞልቷት ነበር፡፡ አባስያም ልጅቱ ወዳለችበት ቤት በመሄድ ፀሎት ያደርጉላታል፡፡ ፀሎታቸውን ሲጨርሱ በዚህ ውሀ እጠቧት በማለት አረፍ አሉ፡፡ ልጅቱ በውሀው እንደታጠበች በሚገርም ሁኔታ መራመድና መናገር ጀመረች፡፡

በዚህ በረከታቸው የተደነቁት አጼ ምኒልክ "አባስያ! ምን እናድርግልህ?" በማለት ጠየቋቸው፡፡ አባስያም "ምንም ነገር አልፈልግም፣ ነገር ግን ልጅቱን ለእኔ ስጡኝ" በማለት መለሱላቸው፡፡ ምኒልክም እንቢ እንዳይሉ ፈሩ "ምን ይደረጋል?" በማለት ሰጧቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ሁለቱ ተጋብተው ስምንት ልጆችን ወለዱ፡፡ ከልጆቻቸው መካከል ዞቢር፣ ጃቢር፣ ሸሪፍ፣ ሶፊያ፣ ሩቅያ... የሚባሉ ይገኙባቸዋል፡፡ ሩቅያ የምትባለው የአባ ስያ ልጅ ከሼህ ጦለሃ ጃእፈር ጋር ለጦርነት ጐንደር ሄዳ አግብታ እዚያ ቆታለች፡፡ የእሷ ልጆችና የልጅ ልጆች ጐንደር ከተማ እስከ ቆላድባ ድረስ ባሉት ከተሞች ይገኛሉ፡፡ የኋላ ኋላ ወደ እዚህ (መዲና አርጐባ) ተመልሳ ለተወሰነ ጊዜ ከኖረች በኋላ ሞታለች፡፡ መቃብሯም እዚህ ይገኛል (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሠላሳ አንድ

## የራስ መኰንን እናት የአርጐባ ተወላጅ ስለመሆናቸው

የአርጐባ ሴቶች በጣም ቆንጆዎች ናቸው፡፡ በቁንጅናቸው ምክንያት አጼዎች ለእቁባትነት እያስገደዱ ይወስዷቸው ነበር፡፡ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ አባት፣ የራስ መኰንን እናት በእቁባት የሄዱ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጅ ናቸው ይባላል፡፡ በኢትዮጵያ ነገስታት በሙሉ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ናቸው (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሠላሳ ሁለት

## ወላስማ አበጋዝ አጼ ምኒልክን ከእስር እንዲያመልጡ ስለማድረጋቸው

ወላስማዎች በጣም ብዙ ናቸው፡፡ የመጨረሻው ወላስማ አበጋዝ ይባላል፡፡ አጼ ምኒልክ ገና የ12 ዓመት ልጅ እያሉ አጼ ቴዎድሮስ ምንጃር ላይ አስረው በመውሰድ መቅደላ ላይ ያስቀምጧቸዋል፡፡ በዚህን ጊዜ ወላስማ አበጋዝ ሰዎችን አስተባብሮ ብዙ ገፀ በርክት በመያዝ ወደ አጼ ቴዎድሮስ ይሄዳሉ፡፡ ከአጼ ቴዎድሮስ ፊት ቀርበው የጌታዬን ልጅ አይኑን እንዳየው ይፍቀዱልኝ በማለት ጠየቋቸው፡፡ እሳቸውም የእስላም ንጉስ ለኔም ጊዜ ይኸው ነው በማለት እንዲያዩ ፈቅደው ወደ መቅደላ ላኳቸው፡፡ ወላስማ አበጋዝም የአጼ ሳህለስላሴ ባሪያ የነበሩትን አዛዥ ወ/ፃዲቅ የሚባሉትን አስቀድሞ በመላክ ፈረስ አዘጋጅተውና ጠባቂዎችን በገንዘብ ደልለው እንዲጠብቋቸው አደረጉ፡፡ ወላስማ አበጋዝ መቅደላ ደርሰው አፄ ምኒልክን በሌሊት በማስመለጥ ለአዛዥ ወ/ፃዲቅ ሰጧቸው፡፡ አዛዥ ወ/ፃዲቅ ተቀብለው ለፈረሰኛ አደረሷቸው፡፡ ፈረሰኞች ይዘዋቸው ወደ ሰሜን ሸዋ በመጓዝ ላይ እያሉ ወሎ ሲደርሱ የታወቀች ሸፍታ ይዛ አሰረቻቸው፡፡ ምክንያቷም ልጇን አጼ ቴዎድሮስ አስረውባት ስለነበር በልዋጭ አስለቅቅባቸዋለሁ በማለት አስባ ነበር፡፡ አፄ ቴዎድሮስ የአፄ ምኒልክን ማምለጥ እንደ ሰሙ የመሳፍንት ልጆችን በሙሉ ሰብስበው ወደ ገደል በመጨመር ፈጅተዋቸው ነበር፡፡ ስምምነቱን እንዲፈጽም መልዕክተኛ ስትልክ መልዕክተኛው መንገድ ላይ የሸፍታዋም ልጅ ከሌሎች የመሳፍንት ልጆች ጋር ወደ ገደል እንደተጨመረ ይሰማና ወደ ወሎ በመመለስ ይነግራታል፡፡ በዚህ ጊዜ አፄ ምኒልክን ለቃቸው አገራቸው ሸዋ ገቡ ይባላል (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሠላሳ ሦስት

## አጼ ምኒልክ ወላስማ አበጋዝን ስለማስገደላቸው

አፄ ምኒልክ የአባታቸውን ቦታ ይዘው የሸዋ ንጉስ ተብለው ያስተዳድሩ በነበረበት ወቅት ወላስማ አበጋዝን አንኮበር አስጠሯቸው፡፡ በዚያን ጊዜ አንኮበር ከአፋፍ በላይ ሹመቱ የአዛዥ ወ/ፃዲቅ ሲሆን፣ ከአፋፍ በታች ደግሞ የወላስማ አበጋዝ ነበር፡፡ ወላስማ አበጋዝ በተጠሩት መሠረት ወደ አፄ ምኒልክ ይሄዳሉ፡፡ የአፄ ምኒልክ ቤተሰቦች ወላስማ አበጋዝ በተኛበት በብረት መዳመጫ ዳምጠው ገደሉት፡፡ በበቅሎ የሄደውን ወላስማ አበጋዝን በቃሬዛ መለሱት፡፡ ይህንን ድርጊት ያስፈፀሙት አፄ ምኒልክ ይሁኑ እንጂ፣ ትዕዛዙ የመጣው በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከነበሩት ከአፄ ዮሃንስ ነው ይባላል፡፡ ምክንያታቸውም የክርስትናን ኃይማኖት ለማጥፋት እንቅስቃሴ እንዳያደርግ በመስጋታቸው ነው ይባላል፡፡ ከወላስማ አበጋዝ ሞት በኋላ የክርስትናን ኃይማኖት ያልተቀበለ ኢትዮጵያን ለቆ ይውጣ በመባሉ፣ ጨኖና አልዩ አምባ ሲቀር ሌሎች ግን ሐይማኖታቸውን ቀይረዋል፡፡ የቀወትና የመንዝ ህዝቦች በሙሉ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ነበሩ፡፡ አፄ ዮሃንስ ናቸው ክርስቲያን አድርገው ብሔርና ቋንቋቸውን ያስቀየሯቸው፡፡ (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሠላሳ አራት

አጼ ምኒልክ የሸዋ ንጉስ ሆነው ያስተዳድሩ በነበሩበት ወቅት ነጋሪት አፈላልገው ያጣሉ፡፡ በኋላ ላይ ወላስማ አባጋዝ እንዳለው ወሬ ይሰሙና መልዕክተኛ ይልኩባቸዋል፡፡ ወላስማ አበጋዝም ነጋሪት በቤታቸው ስለነበረ ለአጼ ምኒልክ መልዕክተኞች ይሠጧቸዋል፡፡ በዚህን ጊዜ አጼ ምኒልክ ይኸ ሰው ነጋሪት ከቤቱ ደብቆ ያስቀመጠ እኔን ከስልጣን አስወጋዱ የሸዋ ንጉስ ለመሆን በመፈለጉ ነው በማለት ይሰጋሉ፡፡ ከዚያም ወላስማ አበጋዝን በመልዕክተኛ ያስጠሯቸዋል፣ እሳቸውም በታዘዙት መሠረት አንኮበር ይሄዳሉ፡፡ አጼ ምኒልክ በሚገባ አስተናግደው ምኝታ ሰጥተው ያስተኟቸዋል፡፡ ሌሊት ላይ በጠባቂዎቻቸው አስደብድበው በፈረስ የሄዱትን ወላስማ አበጋዝን በቃሬዛ እንዲመለሱ ማድረጋቸውን አባቴ ሲያወሩ ሰምቻለሁ (ሐጅ ወላስማ ኡመር መሀመድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሠላሳ አምስት

## አርጐቦች ተራራ ላይ ከመስፈራቸው ጋር የተያያዙ

አርጐቦች ሀገር በመግዛትና የእስልምናን ኃይማኖት ለማስፋፋት ለረጅም ዘመናት ጦርነት አካሂደዋል፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት ጦርነት ይካሄድ የነበረው በፈረስ እና በእግረኛ ጦር ነበር፡፡ ለጦርነት ተመራጭ የሚሆነው ደግሞ ተራራማ ቦታዎች ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት አርጐቦች እራሳቸውን ከጠላት ለማዳን የሚሰፍሩት በተራራማ ቦታዎች ላይ ነበር (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሠላሳ ስድስት

አባቶቻችን እንደሚሉት የአርጐባ ማኅበረሰብ ሜዳ ሜዳውን ቢያርሱም ቤታቸው የሚሰሩት በተራራ ላይ ነው፡፡ ተራራ ላይ የሚኖሩበት ምክንያት ጦርነት ስለሚበዛባቸው ነው፡፡ እራሳቸውን ለመከላከል ተራራ የተሻለ ቦታ በመሆኑ ነው (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሠላሳ ሰባት

አርጐቦች ቤታቸውን በተራራ ላይ በድንጋይ ይሰራሉ፡፡ መንደራቸውንም ሁለት በር እንዲኖራቸው በማድረግ በድንጋይ ያጥሩታል፡፡ አንደኛው የውሀ በር ሲሆን ሌላው የገበያ በር ይባላል፡፡ ቤታቸውን በዚህ መልኩ የሚሰሩት ከአደጋ ለመዳን ነው፡፡ ጠላት በቀላሉ ወደ ወደ ተራራ መውጣት አይችልም፡፡ ቤቶችን በሰደድ እሳትም ማቃጠል አይችሉም፡፡ ሌላው ቤታቸውን በድንጋይ የሚሰሩበት ምክንያት በአረብ እያሉ ቤታቸውን በድንጋይ ይሰሩ ስለነበር፣ ከዚያ በለመዱት መሠረት ከዚህ ከመጡ በኋላም ቤታቸውን የሚሠሩት በድንጋይ ነው፡፡ ቤታቸውን ከድንጋይ መሥራታቸው ከሙቀት ይከላከልላቸዋል (አሚኑ እድሪስ ፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሠላሳ ስምንት

የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የምንኖረው በተራራ ላይ ነው፡፡ በተራራ ላይ የምንኖረው ከኦሮሞዎች ጥቃት ራሳችንን ለመከላከል ነው፡፡ ኦሮሞዎች አርጐቦችን እየፈለጉ ይገድሏቸዋል፡፡ ምክንያቱም በርካታ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች የእስልምናን ኃይማኖት እንዲቀበሉ ያደረጉ አርጐቦች ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ኦሮሞዎች አይወዱንም፡፡ በተራራ ላይ የምንኖረውም ኦሮሞዎች ሊያጠቁን ሲመጡ በቀላሉ

ለመከላከልና ድል ለማድረግ ስለሚያስችለን ነው፡፡ ኦሮሞዎች የሰፈሩት ሜዳ ሜዳውን ስለሆነ የሚያደርሱብንን ጥቃት በቀላሉ ለመከላከል ተራራ ላይ መስፈር ማለፊያ ነው፡፡ (ሼህ አህመድ አባቡሽ፣ ሾንኬ፣ ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሠላሳ ዘጠኝ

## አርጐቦች የብረታ ብረትና የሸክላ ሥራ ስለአለመስራታቸው

በአርጐባ ማኅበረሰብ ውስጥ የከሰል መሬት የሚባል ተሰጥቷቸው የእደ ጥበብ ውጤቶችን የሚሠሩ አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት አይደሉም፣ ይሁን እንጂ፣ ከአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ጋር ይኖራሉ፡፡ የእርሻ መሬታቸውን የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች አርሰው፣ አርመው፣ አጭደውና ወቅተው ምርታቸውን ጐተራ ያስገቡላቸዋል፡፡ አንድ ጥማድ በሬ ያለው ሰው 50 ኪሎ ግራም እህል ይሰጣቸዋል፡፡ አጥራቸውም ይታጠርላቸዋል፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ የተከበሩ ባይሆኑም ለሚሰጡት ጥበባዊ አገልግሎት ምላሽ የሚሆን እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡ እነርሱም ለአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ማረሻ፣ ማጭድ፣ ምሳር፣ ቢላዋ እና የሸክላ ውጤቶችን ይሠራሉ (ሼህ ዩሱፍ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.)።

## ተረክ አርባ

የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ሆኖ ብረታብረትና ሸክላ የሚሠራ ሰው የለም፡፡ ምክንያቱን በትክክል ባላውቀውም ብርት ቀጥቃጭ ነው፣ ሸክላ ሰሪ ነው የሚባል ነገር አለ፡፡ እንደዚያ መባል ስለማይፈልጉ ነው (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.፤መሀመድ ሰይድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 16 ቀን 2005 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ አርባ አንድ

አርጐቦች ብረታ ብረትና ሸክላ አይሰሩም፡፡ እነዚህን ተግባራት የሚያከናወኑ ሰዎች በዘራቸው ነው፡፡ በዘራቸው አይነ ወጊነት አለባቸው ይባላል፡፡ ይህም የሚመጣው በዘራቸው ነው፡፡ አዝመራ በሚደርስበት ወቅት "እኔምሁን (አይናችሁን) ሰብስቡልን" ተብሎ ማኅበረሰቡን በሚያስተዳድረው ቃዲ ወይም ተወካይ አማካይነት ይነገራቸዋል፡፡ እነሱም አዝመራው ጥሩ ምርት እንዲሰጥ አይናቸውን ይሰበስባሉ (አሚኑ እንድሪስ፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ አርባ ሁለት

እርግጥ ነው የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የብረታብረትና የሸክላ ሥራ አይሰሩም። ብረት የሚሰሩ ፈላሻዎች ናቸው። "የከሰል መሬት" ተሰጥቷቸው ከአርጐቦች ጋር ይኖራሉ። ለአርጐቦችም በእጅ በእጅ ክፍያ ወይም በዱቤ ማረሻ፣ ማጭድ፣ ምሳርና የመሳሰሉትን ይሰሩላቸዋል። በዱቤ የሰሩላቸው ከሆነ ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት ገንዘቡን ይሰጧቸዋል። 'ከፈላሻ ጋር ያደረች ሴት ሰውነቷን ያሳክካታል፣ ጤነኛ አትሆንም' ይባላል። በዚህ ምክንያት የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ከእነሱ(ከፈላሻዎች) ጋር አንጋባም። አይን አለባቸው። በሚበላ ምግብ ላይ አይናቸው ካረፈ የሚመገበው ሰው ይታመማል። አይን የሚባለው ነገር የማይካድም የማይዋጥም ነው። ውሸት ነው እንዳንል 'እከሌ መጣብኝ' ወይም 'እከሊት መጣችብኝ' እያሉ ሲሞቱ ይታያል። እውነት ነው እንዳንል የሚወረወር የሚታይ ነገር የለም። በላ የተባለውን ሰው አግኝተን 'እንደዚህ አድርገሀል?' ስንለው ይደነግጣል። እሱ ራሱ ያደረገውን ነገር አያውቀውም። ይህ በጣም አስቸጋሪ የሆነ ነገር ነው (ሼህ መሀመድ፣ አንኮበር፣ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ አርባ ሦስት

### የእደ ጥበብ ሙያተኞች የአርጐባ ማኅበረሰብ አባል ስለመሆናቸው

ለእኛም ሆነ በአካባቢያችን ለሚገኙ ማኅበረሰቦች የተለያዩ ጌጣጌጦችን የምንሰራው እኛ ነን፡፡ አብዛኛው የአርጐባ ተወላጆች የእደጥበብ ሥራ አይችሉም፡፡ ከብረት የእርሻ መሳሪያዎችን እናበጃለን፣ ከሸክላ አፈር ደግሞ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን እንሰራለን፡፡ በዚህ ሙያችን የተከበርን ነን፡፡ ለዚህ ነው በብሔረሰባችን ሆነ በሌሎች ማኅበረሰቦች ዘንድ ተከብረን የምንኖረው (አቶ ከማል ሁሴን፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 14 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ አርባ አራት

### አርጐቦች ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር ስለአለመጋባታቸው

የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር አንጋባም፡፡ እኛ የቁረይሽ ጐሳ አባል ነን እንላለን፡፡ የእኛ ዘር ከሌላ ዘር ጋር አይገጥምም የማለት አስተሳሰብ አለን፡፡ በአንድ ወቅት አንድ የሚያምር የአርጐባ ተወላጅ ለአንድ ንጉስ ግንብ ሲገነባ የንጉሱ ልጁ አይታው ወደደችው፡፡ ለአባቷም አግብታው ከእሱ ጋር መኖር እንደምትፈልግ

ትገልጽላቸዋች፡፡ ንጉሱም ልጁን እንዲያገባት ይጠይቁታል፡፡ የአርጐባ ተወላጁም ከሠለመች አገባታለሁ ይላል፡፡ እስልምናን ካልተቀበለች ግን አላገባትም ይላል፡፡ እሷም እስልምናን ተቀብላ አገባችውና ልጅ ወለዱ፡፡ የልጁን ስምም ወርቅ ኸሰር ብሎ ጠራው፡፡ ወርቅ ኸሰር ማለት ወርቅ ከሰረ እንደማለት ነው (ሼህ መሀመድ ያሲን፣ ሸዋሮቢት፣ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ አርባ አምስት

የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር አይጋቡም፡፡ አርጐባ የሚኖረው ዘሩን ጠብቆ ነው፡፡ ዘሩ ከሌላ ዘር ጋር እንዲበረዝ አይፈልግም፡፡ ሰው የገዛ ዘመዱን ሲያገባ መተዛዘንና መከባበር ይኖራል፡፡ "አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ" መባባልን ይፈጥራል፡፡ ይህም ዝምድናን የበለጠ ያጠናክራል፡፡ አንድ የአርጐባ ተወላጅ ከማኅበረሰቡ ውጪ ቢያገባ ይገለላል፡፡ ለምሳሌ ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ የአርጐባ ተወላጅ ከማኅበረሰቡ ውጪ የሆነች ልጅ አገባ፡፡ ከማግባቱ በፊት ከወንድሙ ጋር በአንድ ግቢ ውስጥ ቤታቸውን ፊት ለፊት ሰርተው ይኖሩ ነበር፡፡ ጋብቻ ከመሠረተ በኋላ ግን ወንድሙ ቀደም ሲል ይገለገልበት የነበረውን የቤት በር በመዝጋት እና የግቢውን በር በመተው ሌላ በር ከፈተ፡፡ ይህም ለወንድሙ ያለውን ጥላቻ ለመግለጽ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ተግባራት መፈፀማችን ለረጅም ጊዜ ማንነታችንን ጠብቀን እንድንኖር አስችሎናል (መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም)።

## ተረክ አርባ ስድስት

## ከአርጐቦች የምግብ አዘገጃጀት ጋር የተያያዘ

አርጐቦች ወቃሊሞ፣ አሊጣጦ፣ ገንፎና አብሽ በማዘጋጀት የተካኑ ናቸው፡፡ በየትኛውም አካባቢ የሚኖሬ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች በሚሠሩት ገንፎና ወቃሊሞ፣ በሚያዘጋጁት አብሽ ላይ እንከን አይገኝም፡፡ ዳቦም ቢሆን በደንብ ይጋግራሉ፡፡ ገንፎና ዳቦ የሚዘጋጀው ከማሽላ ነው፡፡ ቢጫ ማሽላ በደንብ ይፈተግና ተሸክሽኮ ፀሐይ እንዲመታው ይደረጋል፡፡ ከዚያም ለቤተሰብ የሚበቃ መጠን ተወስዶ ይቀቀላል፡፡ ሲበስል ውሀው ይደፋና ወተት ይጨመርበታል፡፡ በዚህ መልኩ የተዘጋጀው ገንፎ ተከድኖ ያድራል፡፡ ጠዋት ተበልቶ አይጠገብም፡፡

አሊጣጦ የሚሠራው ከስንዴ ነው፡፡ ማባያው ግን ዶሮ ወጥ ነው፡፡ አሊጣጦ በጣም በስሱ ከተጋገረ በኋላ ቅቤ ይቀባል፡፡ የሚበላው ትኩሱን ሲሆን፣ ከቆየ ይበላሻል፡፡

አሊጣጦም በጣም ተወዳጅ የሆነ የማኅበረሰቡ ምግብ ነው (ሼህ ዩሱፍ አብዱሰመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ አርባ ሰባት
## ከአርጐቦች የግርዘት ስርዓት ጋር የተያያዘ

በአርጐባ ማኅበረሰብ ወንድም ሆነ ሴት ልጆች ይገረዛሉ፡፡ በማኅበረሰቡ የወንድ ልጅ ግርዘት ከሴት ልጅ የግርዘት ሥነ-ስርዓት ለየት ይላል፡፡ ወንድ ልጅ በተወለደ በ7ኛው ቀን እራሱን ተላጭቶ በምላጭ ይገረዛል፡፡ ግርዘቱ ሲካሄድ የአቂቃ ስርዓት ይካሄዳል፡፡ ሞክት ታርዶ ይቀቀላል፡፡ ሲቀቀል ማነኛውም አይነት አጥንት እንዳይሰበር ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡ ከተቀቀለ በኋላ ስጋው ሙለጭ ተደርጐ ተመልምሎ የቅርብ ዘመድና የአካባቢው ሰው ተጠርቶ ይጋበዛል፡፡ አጥንቱ ሳይሰበር በጥንቃቄ ተሰብስቦ በአንድ ላይ ይቀበራል፡፡ አጥንቱ የማይሰበርበት ምክንያት ልጁ መልካም ሥነ-ምግባር እንዲኖረው ነው፡፡ አጥንቱ ከተሰበረ ወይም በተለያዩ ቦታ ከተበተታተነ ልጁ ለቤተሰቦቹ ታዛዥና ሙሉ ጤናማ አይሆንም፡፡ የወደፊት ተስፋውም የጨለመ ይሆናል ተብሎ በማኅበረሰቡ ዘንድ ይታመናል፡፡ (ይህ ከእስልምና እምነት ጋር የተያያዘ ይመስላል)፡፡ አጥንቱ ከተሰበረና ከተበታተነ ጥሩ አይደለም (ሼህ ዩሱፍ አብዱሰመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ አርባ ስምንት
## ከመውሊድ በዓል አከባበር ጋር የተያያዘ

የመውሊድ (የነብዩ መሀመድ የልደት) በዓልን አርጐቦች ከሌሎች ማኅበረሰቦች ለየት ባለ መልኩ ያከብሩታል፡፡ ከሌሎች ለየት የሚያደርጋቸው ለዚህ በዓል ሁሉም የአርጐባ ማኅበረሰብ አባላት ገንዘብ ያዋጣሉ፡፡ ድሀ የሆነ ሰው ግን ገንዘብ እንዲያዋጣ አይገደድም፡፡ ገንዘቡ ይሰበሰብና በሬ ይገዛል፡፡ የተገዛው በሬ በመስጊድ ታርዶ ይቀቀልና ስጋው በደረጃ ይቀመጣል፡፡ ደረጃውም ሹም ገበታ፣ አስከታይ ገበታ፣ ጐበዝ ገበታ፣ ጐልማሳ ገበታና ሲቆ ገበታ በመባል ይታወቃል፡፡ አከፋፈሉ የሰዎችን ዕድሜ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

በህመምና በተለያዩ ምክንያቶች ለመገኘት ያልቻሉ ካለ የእነሱ ድርሻ ይነሳና የነብዩ መሀመድ ታሪክ እየተነበበ ዱኣ ይደረጋል፡፡ ከዚያ በኋላ ሴቶች ከወንዶች ተለይተው ከህፃን እስከ ሽማግሌ ድረስ ያሉት በዕድሜያቸው መሠረት በደረጃቸው ይቀመጣሉ፡፡

በዕድሜ ደረጃቸው መሠረት ምግቡ ይታደላል፡፡ ምግቡ ሲታደል ጩኸራ የሚባል ከስናፍጭ ከተለያዩ ነገሮች የሚዘጋጅ ማባያ አብሮ ይቀርባል፡፡ በዚህ በዓል ላይ ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ያጋጠመው ሰው ካልሆነ በስተቀር አንድም ሰው አይቀርም፡፡ ከቀረ ተወግዞ ከማኅበረሰቡ ይገለላል፡፡ መገለል በጣም ከባድ በመሆኑ ይህ ችግር እንዳይደርስባቸው በማሰብ ሁሉም የማኅበረሰቡ አባላት ይገኛሉ (ሼህ አህመድ አባቡሽ፣ ሾንኬ፣ ግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ አርባ ዘጠኝ

## አርጐቦች ቡዳ ከመባላቸው ጋር የተያያዘ

የአርጐባ ማኅበረሰብ ባህሉንና ሐይማኖቱን ጠብቆ ለረጅም ዘመናት የቆዬ ነው፡፡ በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢ የሚኖሩ አርጐቦች ከራሳቸው ማኅበረሰብ ውጭ አያገቡም፡፡ በዚህ ምክንያት በሐረር አካባቢ የሚገኙ የኦሮሞ ብሔር ሽማግሌዎች አንድ ቀን ተሰባስበው አርጐቦችን "ለምንድን ነው ከእኛ ጋር የማትጋቡት? በዘራችሁ ወይስ በመልካችሁ ወይስ በሀብታችሁ ኮርታችሁ ነው?" የሚል ጥያቄ ያቀርቡላቸዋል፡፡

አርጐቦችም "ከእናንተ ጋር የማንጋባው ዘራችንንና ሐይማኖታችንን ጠብቀን ለመኖር ስለምንፈልግ እንጂ፣ እናንተን ጠልተናችሁ ወይም ለእናንተን ዘር ዝቅ ያለ አመለካከት ኑሮን አይደለም" ይሏቸዋል፡፡

ሽማግሌዎችም "ለእኛ ዘር ጥሩ የሆነ አመለካከት ካላችሁ ታዲያ ለምን እየተጋባን አንኖርም?" በማለት ደግመው ይጠይቋቸዋል፡፡

አርጐቦችም "መጋባት አንፈልግም" የሚል ምላሽ ይሰጧቸዋል፡፡

የኦሮሞ ሽማግሌዎች በዚህ ተናደው ከእኛ ጋር መጋባት የማትፈልጉት ቡዳ ስለሆናችሁ ነው፡፡ መልካችሁም የሚያምረው ቡዳ በመሆናችሁ እንጂ፣ በሌላ ምክንያት አይደለም" አሏቸው፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ አርጐቦች ቡዳ ናቸው የሚል ቅስቀሳ ተደረገባቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ የሀረር ግንብ ካሉት አምስት በሮች መካከል አንዱን ቡዳ በር በማለትም ሲጠሩት ቆይተዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ቡዳ በር የሚለው ስያሜ ተለውጦ አርጐባ በር ተብሎ በመጠራት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ ምክንያት በሀረር አካባቢ ለሚገኙ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የአካባቢው ማኅበረሰብ ጥሩ የሆነ አመለካከት የላቸውም፡፡ በሌሎች አካባቢ ለሚገኙ የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች የሚታወቁት በኃይማኖት መሪነታቸው፣ በአገር ሽማግሌነታቸውና በአስተማሪነታቸው ነው፡፡

በተለይም በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ እና ደቡብ ወሎ አካባቢ የሚገኙ ማኅበረሰቦች አርጐቦችን የሚጠሯቸው ሸሆቻችን በማለት ነው (ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሃምሳ

## አርጐቦች ሰይድ አሊይን የገደሉ ከመባላቸው ጋር የተያያዘ

የአርጐባን ታሪክ በቅጡ የማያውቁ ሰዎች አርጐባ ሰይድ አሊይን ገድለው ተሰደው የመጡ ናቸው ይላሉ፡፡ ሰይድ አሊ ከነብዩ መሀመድ ቀጥሎ የመጡ ሱሐባ ናቸው፡፡ መሳሪያ ተተኩሶባቸው ህይወታው አልፋል፡፡ የእሳቸው ገዳይ ከራሳቸው ወገን ከ "በኒ ኡመያ" ዘሮች መካከል አንዱ ነው፡፡ እሱም በሸሪዓ ህግ መሠረት ወዲያውኑ እንዲገደል ተደርጓል፡፡ በኒ ኡመያ የነብዩ መሀመድ የአጐታቸው ቤተሰብ ናቸው፡፡

አርጐቦች የሰይድ አሊይ ገዳዮች ናቸው የሚሉ ሰዎች በምቀኝነት ወይም በቅናት መንፈስ ተነሳስተው ነው፡፡ ምክንያት ሌሎች ማኅበረሰቦች ዘንድ በሐይማት መሪነታችን ተቀባይነት ስላለን ነው፡፡ የእኛ ሰፊ የሆነ ተቀባይነት ማግኘት ያልተዋጠላቸው አንዳንድ ሰዎች የሰይድ አሊይ ገዳዮች ናቸው ይሉናል፡፡ እነሱ እንደዚህ የሚሉን፣ የእስልምና ተከታይ ወንድሞቻችን በኃይማኖት አብረውን እንዳይሰለፉ እና እኛን ለማስጠላት የተሸረበብን ሴራ ነው (ሼህ ዩሱፍ አብዱሰመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሃምሳ አንድ

## የአርጐባ ማኅበረሰብ እስላም አይደሉም ስለመባላቸው

የአርጐባ ማኅበረሰብ ታሪክ የማያውቁ አንዳንድ ሰዎች አርጐባ ማለት ወላስማ ማለት ነው ይላሉ፡፡ ወላስማ ወይም ኡመር ወላስማ ማለት ወላ እስላም ለማለት ሲሆን፣ እስላም ያልሆነ እንደማለት ነው፡፡ እንደዚህ የሚሉት ታሪካችንን ለማጣመም ነው፡፡ ይህ ስህተት ነው፡፡ ከአርጐባ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለውም፡፡ ታሪካችን ሲፃፍ ተስተካክሎ መፃፍ አለበት፡፡ አርጐቦች ከአርብ ምድር የመጡና የእስልምናን ኃይማኖት ያስተማሩ፣ ያስፋፉ ማኅበረሰቦች ናቸው፡፡ የእስልምና አባት ናቸው (ሼህ ዩሱፍ አብዱልሰመድ፣ መዲና፣ ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሃምሳ ሁለት

ወላስማ ማለት አስተዳዳሪ ማለት ነው፡፡ ከአርጐቦች መካከል ለመሪነት የሚታጨው ከወላስማ ዘር ብቻ ነው፡፡ በተለያዬ ወቅት የነበሩ ገዥዎች ሀገሪቱን ያስተዳደሩት ወላስሞችን ይዘው ነው፡፡ ካለወላስሞች እገዛ መምራት አይችሉም ነበር (ሐጅ ኡመር መሀመድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም.)

## ተረክ ሃምሳ ሦስት

## ከረከቦት ስርዓትን ጋር የተያያዙ

አርጐቦች በሌላው ኅብረተሰብ ዘንድ ከሚታወቁባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የረከቦት ሥርዓታቸው ነው፡፡ አንድ ማኅበረሰብ ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር ሲጋጭ ለአስታራቂነት የሚመረጡት አርጐቦች ናቸው፡፡ አፋር፣ ኦሮሞና አማራ ሲጋደሉ ተው ባዮች የአርጐባ ማኅበረሰብ ተወላጆች ናቸው፡፡

ሰው ተጋደለብን ወይም ተጋጨብን የሚል መልዕክት ሲደርሳቸው ሰይፍ ወይም ሙስብሀ (አንካሴ) ለሁለቱም ወገን ይላካል፡፡ መልዕክቱ እንደደረሳቸው ግጭቱ ይቆማል፡፡ ዳስ ይጣልና ከሁለቱም ወገን ሽማግሌዎች ይመረጣሉ፡፡ ደም አድራቂዎቹም ይዘዋቸው የሚሄዱን ሽማግሌዎችን ይመርጣሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ቀጠሮ ይያዛል፡፡ በቀጠሮው ቀን ሁለቱም ወገኖች ከነቤተሰቦቻቸው ይገኛሉ፡፡ በቀጠሮው ቀን የሚቀር አይኖርም፡፡ ምክንያቱም የሚቀሩት ሰዎች ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሽምግልናው ይደረጋል፡፡ ጠቡን ማን እንዳስነሳው፣ የጠቡ መነሻ ምን እንደሆነ፣ የጠፋው ንብረትና ህይወት ምን ያህል እንደሆነ ያጣራሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ሚዛናዊ ፍርድ ይሰጣሉ፡፡ በፍራቻ ወይም በጥቅም ተደልለው የተዛባ ፍርድ አይሰጡም፡፡ በዚህ ምክንያት ተቀባይነት ለማግኘት ችለዋል፡፡ ከእርቅ በኋላ እርቁን አፍርሶ ያልተገባ ነገር የሚፈጽም ሰው ችግር ይገጥመዋል፡፡ ለአላህ ቅርብ በመሆናቸው ተአምራቸው በጣም ፈጣን ነው፡፡ ፀሎት ሲያደርጉ አላህም ፀሎታቸውን ሰምቶ የእርቅ ስርዓቱን ባፈረሰው ሰው ላይ አንዳች መአት ያወርዳል፡፡

ለምሳሌ አንዴ የጉሳ ግጭት ተነሳና ወደ 17 ሰዎች ሞቱ፡፡ የተጐጅ ወገኖች መልዕክት ላኩ፡፡ "ግጭቱን አቁሙ እናስታርቃችሁ፣ ለሞተው የደም ዋጋ እናስከፍላለን፡፡ የጠፋውን ንብረት እናስመልሳለን" ብለው ላኩባቸው፡፡ ግጭቱ ቆመና የጠፋው ህይወትም ታወቀ፡፡ የወደመው ንብረት ተቆጠረ፡፡ ከዚህ በኋላ ቀጠሮ ተያዘ፡፡

በቀጠሮው ቀን የሚች ወገኖች በገዳይ ወገን ላይ አደጋ ለመጣል ለሁለት ተከፍለው ያደፍጣሉ፡፡ የገዳይ ወገን ግን በሌላ መንገድ ሄደው ኖሮ ከሽምግልናው ቦታው በሰዓቱ ይደርሳሉ፡፡ የተበዳይ ወገኖች በመቅረታቸው ሽማግሌዎች ምክንያቱን ሲያጣሩ ደፈጣ ማድረጋቸውን ይደርሱበታል፡፡ "ለምን እንደዚህ አይነት ሥራ ትሰራላችሁ?" ብለው መልእክት ላኩባቸው፡፡ በዚህን ጊዜ በአንደኛው ቦታ ላይ ያደፈጡት "ባላንጣዎቻችን ከሽምግልናው ቦታ ከደረሱ እኛም ወደዚያው እንሂድ" ብለው መንገድ ይጀምራሉ፡፡ በጉዞ ላይ እያሉ የገዛ ዘመዶቻቸው የገዳይ ወገን የመጣ መስሏቸው ተኮሱባቸው፡፡ እነርሱም የጠላት ወገኖች መስለዋቸው መሬት በመያዝ ተታኮሱ፡፡ በተካሄደው ተኩስ ሦስት ሰዎች ሞተው ሦስት ደግሞ ቆሰሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ የአካባቢው ማኅበረሰብ ከብቦ በመያዝ ከሽማግሌዎች ፊት አቀረባቸው፡፡ ይህ ችግር የደረሰባቸው የደም አድራቂዎችን ቃል በማፍረሳቸው ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ችግር ስለሚያጋጥም ከሽማግሌዎች ቃል የሚወጣ የለም (ሼህ ዩሱፍ ፣ መዲና፣ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

## ተረክ ሃምሳ አራት

በአርጐባ ማኅበረሰብ በታላላቅ ሰዎች የማስታረቅ ልማድ ረከቦት ይባላል። ረከቦቱ የሚፈፀመው ልምድ ባላቸው ሰዎች ነው፡፡ ልምድና እውቀቱ የወላጅ ውርስ ሆኖ የሚያገኙት ሲሆን ልጅ ከአባቱ ተጠግቶ እየተማረ ለልጁ በማውረስ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው፡፡ የሽምግልና እውቀቱና መነሻ የእስልምና አስተምህሮው መሪና አርአያ የሆነው ኡላማ ነው። ለኡላማው ከአላህ የሚሰጠው ኢጃዛ (ፈቃድ) ነው የኢጃዛ ባህርይ የነብዩ መሀመድ ባህርይ ነው፣ የነብዩ ባህርይ ደግሞ ቅዱስ ቁርዓንን ይመስላል። በዚህ ምክንያት ሰዎች ከረከቦቱ ፈቃድ አይወጡም። ከእሱ ፈቃድ የሚወጡትን ፈጣሪ ይቀጣዋል፡፡ በዚህ ሞንያትም ከአርጐባ ማኅበረሰብ ውጭ የሆኑትን ጭምር የሚያስታርቁ አርጐቦች ለመሆን ችለዋል (ሼህ መሀመድ አወል፣ አንኮበር፣ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡

## ተረክ ሃምሳ አምስት

ረከቦት ማለት ትልቅ ቤተሰብ ማለት ነው። ረከቦቶች የወልይዎች፣ የሼሆች (የትልልቅ ሰዎች)ልጆች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ልመናቸው የፈጣሪን ፊጣን ምላሽ የሚያስገኝላቸው፣ ሌላው ቀርቶ ግደል ካሉት የሚገድልላቸው፣ አድርግ ያሉትን በሙሉ የሚያደርግላቸው ናቸው።

ልጆቹ ወይም ከቤተሰቤ አንዱ ከሰው ጋር ከተጋጨ ወይም ከተበደለ ወደ ረከቦቶች በመሂድ ሙስባህ (አንካሴ) በመቀበል ወስጀ እሰጣቸዋለሁ። በዚህን ጊዜ በዳዩ እነሱ ጋ ይቀርባል። እምቢ ብሎ የሚቀር የለም። ከቀረ አንዳች ችግር ያጋጥመዋል። በዳይ እንደቀረበ እነሱም ነገሩን አጣርተው ቀላል ከሆነ ያስታርቁናል። ከባድ ከሆነ ቀጠሮ በመስጠት እያንዳንዳችን ሁለት ሁለት ሽማግሌ ይዘን እንድንመጣ ያደርጋሉ። በቀጠሮው ቀን በዳይና ተበዳይን ፊት ለፊት እንድንከራከር ያደርጋሉ። እኔ ተበድዩ የደረሰብኝን በደል ስናገር በዳይ መልስ ይሰጣል። ከክርክሩ በኋላ ሁለታችንም ተከራካሪዎች እንድንወጣ ይደረጋል። ከዚያም ከሽማግሌዎች ጋር በመነጋገር ፍርድ ይሰጣሉ። የተጋጨነው ወገኖች እንጠራና "እንደዚህ አይነት በደል አይተናል። በበዳዩ ላይም እንዲህ ወስነናል። ስለዚህ በዳይ እንደዚህ ያለ ካሳ ትክሳለህ" ይላሉ። የተወሰነበትም 'ከእናንተ አልወጣም እክሳለሁ' ይላል። በዚህም እርቅ ይወርድና እንዘያየራለን። ነገሩ በዚህ መልኩ ይቋጫል (ሼህ አረቡ፣ ከሚሴ፣ ግንቦት 8 ቀን 2004 ዓ.ም )።

## ተረክ ሃምሳ ስድስት

## ከወቃሊሞ አጀማመርን ጋር የተያያዘ

ከሌላው አካባቢ ይልቅ የወቃሊሞ አሰራር በስፋት የሚታወቀው ይፋት ላይ ነው፡፡ ወቃሊሞ የአርጎባ ማኅበረሰብ የክብር ምግብ ሲሆን፣ ምግቡ የሚዘጋጀው በበዓል፣ በሠርግ እና በተለያዩ ሥነ-ስርዓቶች በሚፈፀሙበት ወቅት ነው፡፡ ወቃሊሞ የሚዘጋጀው ከስጋ ነው፡፡ በቅድሚያ በሬ ወይም በግ ይታረዳል፡፡ ቀይ ስጋ ብቻ ተመርጦ ከአንጀቱ ጋር ለሴቶች ይቀርባል፡፡ ሴቶቹም ስጋውን እንደ ክትፎ ድቅቅ አድርገው ይከትፉና በልዩ ልዩ ቅመሞችና በበርበሬ ያሹታል፡፡ አንጀቱን ደግሞ በውስጡ ያለውን እበት (ቆሻሻ) አልበው በማውጣት ሙልጭ አድርገው ያጥቡታል፡፡ በመቀጠልም የበሬው ሥጋ በሬው አንጀት ወይም የበጉ ስጋ በበጉን አንጀት ውስጥ ይጨመሩትና በገመድ ላይ ይሰቅሉታል፡፡ የአንዱን በሬ ስጋ የበሬው አንጀት፣ የበጉን ሥጋ ደግሞ የበጉ አንጀት ይይዘዋል፡፡ ስጋው በአንጀቱ ውስጥ ከተጨመረ በኋላ ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት ይቆያል፡፡

ይህ የምግብ አይነት የተጀመረው ጥንት በአባቶቻችን ጊዜ ነው፡፡ ያኔ የአርጎባ ማኅበረሰብ ለጦርነት ወይም ለንግድ ከቤታቸው ወጥተው ለረጅም ጊዜ ሳይመለሱ ይቆዩ ነበር፡፡ የአርጎባ ሴቶች ባላቸው ከቤት ወጥቶ ለረጅም ጊዜ እንደሚቆይ ሲያውቁ የሚያዘጋጁላቸው ስንቅ ወቃሊሞን ነበር፡፡ ይህ በደቃቁ ተከትፎ በአንጀት ውስጥ ደርቆ

የተቀመጠው ሥጋ ወንዶች ጠብሰው ወይም ወጥ ሰርተው ይመገቡታል (ሼህ አህመድ፣ አባቡሽ፣ ግንቦት፣ 16 ቀን 2004 ዓ.ም፤ መሀመድ ሰይድ፣ አልዩ አምባ፣ የካቲት 16 ቀን 2005 ዓ.ም.)፡፡

ይህ የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት በማሟያነት የቀረበው ጥናት የእኔ መሆኑንና ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎች በሙሉ በተገቢው ሁኔታ የገለጽኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም አዲሱ ጴጥሮስ

ፊርማ________

ቀን ሰኔ 2005 ዓ.ም.